# 7

# ወንጌላት፡ ብዙ አቅጣጫዎች ያሉት አንድ ታሪክ

እንደ መልእክቶች ሁሉ ወንጌላትም መጀመሪያ ስናያቸው ለመተርጎም ቀላሎች ይመስላሉ። በወንጌላት ውስጥ የሚገኙ ነገሮች አባባሎችና ትረካዎች፥ ማለትም የክርስቶስ ትምህርቶችና ስለ ክርስቶስ የተነገሩ ታሪኮች ተብለው በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ። ስለሆነም ለአንደኛው ወገን መልእክቶችን፥ ለሌላው ደግሞ ትረካዎችን ለመተርጎም የተሰጡትን መርሆዎች መከተል እንደሚቻል በአሳብ ደረጃም መግለጽ ይቻላል።

ይህ በመርህ ደረጃ እውነት ቢሆንም፥ ያን ያህል ቀላል አይደለም። በአራቱ ወንጌላት ውስጥ የተለየ ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጽ የሚታይ ሲሆን፥ ብዙም እውነተኛ ምስያዎች የሉትም። አብዛኛው ሐቲታዊ ችግር የሚፈልቀው ወረድ ብለን ከምንመለከተው ልዩ ገጽታቸው ነው። ከእነዚህም አንዳንዶቹ በወንጌላት ውስጥ የሚገኙትን «ከባባድ አባባሎች» የሚመስሉ ናቸው። ዋንኛው ሥነ አፈታታዊ ችግር የሚመጣው ግን «የእግዚአብሔር መንግሥት» ከተባለው ሐረግ ነው። ይህ ሐረግ ለጠቅላላው የክርስቶስ አገልግሎት ወሳኝ ሲሆን፥ በመጀመሪያው ምእተ ዓመት የይሁዲነት ቋንቋና ጽንሰ አሳብ ውስጥም የነበረ ነው። ችግሩ እነዚህን አሳቦች እንዴት ወደ ራሳችን ባሕላዊ መቼቶች እንለውጣቸዋለን? የሚለው ነው።

## የወንጌላት ባሕርይ

ወንጌላትን በመተርጎሙ ሂደት ውስጥ የሚያጋጥሙ ችግሮች ሙሉ በሙሉ ማለት ይቻላል ከሁለት ግልጽ ሐቆች የሚመነጩ ናቸው። (1) ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ወንጌላትን ስላልጻፈ ያገኘናቸው ከእርሱ ሳይሆን ከሌሎች ነው። (2) አራት ወንጌላት ናቸው ያሉት።

ወንጌላት በራሱ በክርስቶስ አለመጻፋቸው አጽንኦት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ነው። ክርስቶስ አንድ ነገር ጽፎ ቢሆን ኖሮ ጽሑፉ አሁን ያሉንን ወንጌላት ሳይሆን እንደ አሞጽ ዓይነት የብሉይ ኪዳን ትንቢታዊ መጻሕፍትን ይመስል ነበር። ይህም በቃል የተላለፉ ንግግሮችና አጭር ግላዊ ትረካዎች የሚገኙበት ነው (ልክ እንደ አሞጽ 7፡10–17)። ወንጌላት አባባሎችን ያካትታሉ። እነዚህ ግን ከኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወትና አገልግሎት ጋር የተሳሰሩ ታሪካዊ ትረካዎች ናቸው። ስለሆነም በክርስቶስ የተጻፉ ሳይሆኑ ስለ ክርስቶስ የተጻፉ

መጻሕፍት ናቸው። እግረ መንገዳቸውን ከትምህርቱ ብዙ ይዘው እናገኛቸዋለን።

ይህም በእኛ ግንዛቤ ላይ የሚያስከትለው ችግር አለው። የዚህን ችግር ባሕርይ በሐዋርያት ሥራና በመልእክቶች ውስጥ ካለው የጳውሎስ ምስያ መመልከት ይቻላል። ለምሳሌ፥ የሐዋርያት ሥራ ባይኖረን ኖሮ ከመልእክቶች ውስጥ በምናገኛቸው አንዳንድ አላባውያን አማካኝነት የጳውሎስን ሕይወት ለማጥናት እንገደድ ነበር። እንዲህ ዓይነቱ አቀራረብ ደግሞ የተሟላ እንደማይሆን ግልጽ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ መልእክቶቹ ባይኖሩን ስለ ሥነ መለኮታዊ አስተሳሰቡ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ባቀረባቸው ንግግሮች ላይ ተመሥርተን የምንወስደው ግንዛቤ ውጤታማ አይሆንም ነበር። ይህም ሚዛናዊነቱን ያዛባው ነበር። ስለሆነም በጳውሎስ ሕይወት የሚገኙትን ቁልፍ ነገሮች ለማግኘት የሐዋርያት ሥራን እናነብና በመልእክቶች ውስጥ የሚሰጠንን መረጃ እዚያው ውስጥ እንጨምራለን። ትምህርቶቹን ለማግኘት ግን መጀመሪያ ወደ መልእክቶቹ እንሄድና ለተጨማሪ ማብራሪያ ወደ የሐዋርያት ሥራ እንመለሳለን።

ወንጌላት ግን እንደ የሐዋርያት ሥራ አይደሉም። ምክንያቱም ወንጌላት ውስጥ የክርስቶስ ሕይወት ትረካና የዚያ ሕይወት መሠረታዊ አካል የሆኑ የክርስቶስ አባባሎች (ትምህርቶች) አብረው ስለሚገኙ ነው። ነገር ግን መልእክቶች በጳውሎስ እንደተጻፉት አባባሎቹ በክርስቶስ የተጻፉ አይደሉም። ክርስቶስ ያስተማረው በአረማይክ ቋንቋ ሲሆን፥ ለእኛ የደረሰው ግን በፅርዕ ቋንቋ ነበር። በተጨማሪም፥ አንዱ አባባል በሁለት ወይም ሦስት ወንጌላት ውስጥ ይደጋገማል። አባባሉ በተመሳሳይ የጊዜ ቅደም ተከተል ወይም ታሪካዊ መቼት በሚመጣበት ጊዜ እንኳ በእያንዳንዱ ወንጌል ውስጥ የሚቀርብበት አገላለጽ እምብዛም ተመሳሳይ አይደለም።

ይህ ለአንዳንዶች አስጊ ሊሆን ቢችልም፥ አስጊነቱ ያን ያህል የሚጎዳ አይደለም። በርግጥ አንዳንድ ምሁራን ይህንን እውነታ በማዛባት በወንጌላት ውስጥ የሚታመን ነገር እንደሌለ ገልጸዋል። እንዲህ ዓይነቱ ድምዳሜ ግን አስፈላጊ አይደለም። በተመሳሳይ ሁኔታ ጥሩ ጥናት ያካሄዱ ምሁራን በወንጌላት ውስጥ የሚገኙትን አሳቦች ታሪካዊ ተአማኒነት አስረድተዋል።

በዚህ ክፍል ዋናው ነጥባችን አንድ ነው። እግዚአብሔር ስለ ክርስቶስ ምድራዊ አገልግሎት መረጃ የሰጠን፥ አንዳንድ ሰዎች እንደሚፈልጉት በተወሳሰበ መንገድ ሳይሆን በዚህ መልኩ ነው። ወንጌላት በክርስቶስ ሳይሆን ስለ ክርስቶስ መጻፋቸው ደግሞ

የድክመታቸው ሳይሆን የጥንካሬአቸው አካል እንደሆነ ለመግለጽ እንፈልጋለን።

ወንጌላቱ አራት የሆኑትስ እንዴትና ለምን ነበር? አራት የሐዋርያት ሥራዎች የሉንም? በተጨማሪም፥ በመጀመሪያዎቹ ሦስት ወንጌላት ውስጥ የሚገኙ አሳቦች ብዙውን ጊዜ ተመሳሳይ በመሆናቸው «ሲኖፕቲክ» («የጋራ እይታ») ብለን እንጠራቸዋለን። በማርቆስ ወንጌል ውስጥ ብቻ የሚገኘው አሳብ ሁለት ገጽ የማይሞላ ሆኖ ሳለ ለምን ራሱን የቻለ መጽሐፍ እንደ ተጻፈ ራሱ ሊያስገርም ይችላል። ይሁን እንጂ፥ አሁንም አራትነታቸው የጥንካሬያቸው አካል ነው እንላለን።

እንግዲህ፥ የወንጌላት ባሕርይ ምንድን ነው? ልዩ ባሕርያቸው የጥንካሬያቸው አካል የሚሆነውስ ለምንድን ነው? መጀመሪያ ለምን አራት እንደሆኑ በመናገር ይህንን ጥያቄ ደህና አድርገን መመለስ ይቻላል። ለዚህ ጥያቄ ፍጹም ትክክለኛ ምላሽ ለመስጠት ባንችልም፥ አንደኛው መልስ ግን ቀላልና በጠቀሜታ ላይ ያተኮረ ነው። የተለያዩ ክርስቲያን ማኅበረሰቦች ስለ ክርስቶስ መጻፍ ይፈልጉ ነበር። በተለያዩ ምክንያቶች ለአንድ ማኅበረሰብ ወይም የአማኞች ቡድን የተጻፈ ወንጌል፥ የሌላውን ማኅበረሰብ ፍላጎቶች ሁሉ ሊያሟላ አልቻለም ነበር። ስለሆነም መጀመሪያ የተጻፈው የማርቆስ ወንጌል (አብዛኞቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን እንደሚስማሙት) በተለያዩ ምክንያቶች የተለያዩ ፍላጎቶችን ለማሟላት ሁለት ጊዜ (ማቴዎስና ሉቃስ) ተደጋግሞ ተጻፈ። ከዚህ ውጭ ዮሐንስ (አሁንም አብዛኞቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን እንደሚስማሙት) ለሌሎች ምክንያቶች የተለየ ወንጌል ጻፈ። መንፈስ ቅዱስ ይህንን ሁሉ እንዳስተባበረ እናምናለን።

ለኋለኛዋ ቤተ ክርስቲያን የትኛውም ወንጌል ሌላውን አይተካውም። ነገር ግን እያንዳንዱ ወንጌል እኩል ጠቀሜታና እኩል ሥልጣን ይዞ ከሌላው ጋር ጎን ለጎን ይቆማል። ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? ምክንያቱም በእያንዳንዱ ወንጌል ለክርስቶስ የተሰጠው ትኩረት ሁለት ደረጃዎችን ያካተተ ነበር። በመጀመሪያ፥ የክርስቶስን ማንነትና የተናገራቸውን ነገሮች ለማሳየት የተደረገ ሙሉ ለሙሉ ታሪካዊ ትኩረት ነበር። በመስቀል ላይ የተሰቀለውና ከሞት የተነሣው፥ አሁን ደግሞ ከሙታን እንደ ተነሣና እንደ ከበረ አምላክ የምናመልከው ክርስቶስ ይህ ነው። ሁለተኛ፥ ፅርዕን እንጂ አረማይክ ለማይናገሩ ሰዎች ታሪኩን እንደገና ለመተረክ ጥረት ተደርጎ ነበር። ወንጌሉ ገጠርማ፥ በእርሻ በሚተዳደርና አይሁዳዊ መቼት ካለው ስፍራ ወጥቶ በሮም፥ በኤፌሶን፥ በአንጾኪያና በሌሎችም ከተማ ነክ የአረማውያን መናኸሪያዎች እንዲዳረስ ተፈልጎ ነበር።

ስለሆነም፥ በተወሰነ መልኩ ወንጌላት ለእኛ እንደ ታሪካዊ ሞዴሎች እያገለገሉ ነበር። ይኸውም በባሕርያቸው እኛም ያንኑ ተመሳሳይ ታሪክ በሃያኛው ክፍለ ዘመን ዓውዳችን እንድንናገር የሚገፋፉ ነው።

ስለሆነም ስለ ክርስቶስ የምናውቀውን ሁሉ የሚነግሩን እነዚህ መጻሕፍት የሕይወት ታሪክ ዘገባዎች አይደሉም። ምንም እንኳ ከሁሉም ስለሚበልጠው ሰው ታሪክ ቢናገሩም፥ የታላላቅ ሰዎችን «ሕይወት» እንደሚነግሩን ዘመናዊ መጻሕፍት አይደሉም። በሁለተኛው ክፍለ ዘመን የነበረው የቤተ ክርስቲያን አባት ጃስቲን ማርቲር እንደተናገረው፥ «የሐዋርያት መታሰቢያዎች» ናቸው። አራት የሕይወት ታሪክ ዘገባዎች እኩል እሴት እንዳላቸው ጎን ለጎን ሊቆሙ አይችሉም። ነገር ግን እነዚህ መጻሕፍት በተመሳሳይ ጊዜ ስለ ክርስቶስ እውነተኛ ነገሮችን ስለሚናገሩ፥ የክርስቶስን ትምህርቶች ስለሚያስታውሱና እያንዳንዳቸው ስለ ክርስቶስ ምስክርነት ስለሚሰጡ ተደጋግፈው ይኖራሉ። ጥንካሬያቸውም ባሕርያቸውም ይኸው ነው። ይህ ደግሞ ለሐቲትም ሆነ ለአፈታት ጥበብ ጠቃሚ ነው።

ስለሆነም የወንጌላት ሐቲት የክርስቶስን ታሪካዊ መቼትና የደራሲያኑን ታሪካዊ መቼት እንድናስብ ያስገድደናል።

## ታሪካዊ ዓውድ

የመጀመሪያው የሐቲት ተግባር ስለ ታሪካዊ ዓውድ ማወቅ እንደሆነ ታስታውሳለህ። ይህም ማለት ታሪካዊ ዓውዱን ጠቅለል ባለ መልኩ ማወቅ ብቻ ሳይሆን፥ ደራሲው የሚያቀርበውን ሁኔታ በተገኙት መረጃዎች ላይ ተመሥርቶ በጊዜያዊነት መልሶ ማዋቀር ጭምር ነው። ወንጌላት የሁለት ደረጃ ሰነዶች በመሆናቸው አንዳንድ ጊዜ ይህ ውስብስብ ሊሆን ይችላል። ታሪካዊ ዓውድ ከሁሉም በፊት ክርስቶስን የሚመለከት መሆን አለበት። ይህም ክርስቶስ የኖረባትንና ያስተማረባትን የመጀመሪያይቱን ክፍለ ዘመን ፓለስታይን የአይሁድ ሃይማኖትና ባሕል ማወቅን ይጨምራል። እንደዚሁም እያንዳንዱ አባባል ወይም ምሳሌ የተነገረበትን ውስን ዓውድ ማወቅን ይጠይቃል። በተጨማሪም ታሪካዊ ዓውድ የወንጌላት ደራሲዎችን (ወንጌላውያን) እና የጻፉባቸውን ምክንያቶች ማወቅንም ያካትታል።

ስለ እነዚህ የተለያዩ ዓውዶች ለማሰብ መሞከሩ ለተራ አንባቢ ሥራ ማብዛት እንደሆነ ይገባናል። እንዲሁም ደግሞ ከየትኛውም የአዲስ ኪዳን ጥናት በላይ በዚህ አካባቢ የሚቀርበው ምሁራዊ ግምት እንደሚበዛም እንገነዘባለን። ነገር ግን የወንጌላትን ባለ ሁለት ደረጃ ባሕርይ ልንለውጠው የማንችለው ነው። በእነዚህ ነገሮች አንተን

ኤክስፐርት እናደርግሃለን ባንልም፥ አንዳንድ ጊዜ ግን ስለ ኤክስፐርቶች እናስባለን። እዚህ ላይ ተስፋ የምናደርገው የግንዛቤ ደረጃህን በማሳደግ ለወንጌላት አድናቆት እንዲኖርህና ወንጌላትን በምታነብበት ጊዜ የሚያጋጥሙህን ጥያቄዎች እንዴት ማስተናገድ እንዳለብህ መንገድ ለማሳየት ነው።

*የክርስቶስ ታሪካዊ ዓውድ በአጠቃላይ*

ክርስቶስን ለመረዳት ከፈለግህ እርሱ በኖረበት የአንደኛው ምእተ ዓመት የአይሁድ እምነት ውስጥ ዘልቀህ መግባትህ የግድ አስፈላጊ ነው። ይህም ሰዱቃውያን በትንሣኤ እንደማያምኑ ከማወቅ ያለፈ ነው። ለምን እንደማያምኑና ክርስቶስም ከእነርሱ ጋር ለምን ብዙ ግንኙነት እንዳልነበረው መገንዘብን ይጠይቃል።

ለዚህ ዓይነት የመሠረት መረጃ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ የሚገኙትን ጥሩ ምንጮች ከመሻት የተሻለ አማራጭ የለንም። በዚህ ረገድ ከሚከተሉት መጻሕፍት አንዱን ወይም ሦስቱንም ማንበቡ ጠቃሚ ይሆናል። «Joachim Jeremias, *Jerusalem in the Time of Jesus* (Philadelphia: Fortress, 1969); Eduard Lohse, *The New Testament Environment* (Nashville: Abingdon, 1976), pp. 11-196; J. Duncan M. Derrett, *Jesus's Audience* (New York: Seabury, 1973).»

የዚህ ታሪካዊ ዓውድ አቅጣጫ ጠቃሚ ገጽታ የሆነውና ብዙውን ጊዜ ቸል የሚባለው ደግሞ የክርስቶስ የማስተማሪያ ቅርጽ (ዘዴ) ነው። ክርስቶስ ብዙውን ጊዜ በምሳሌ እንደሚያስተምር ማንም ያውቀዋል። ሰዎች የማያውቁት የዚህ ዓይነቱን ዘዴ በተለያዩ መንገዶች መጠቀሙን ነው። ለምሳሌ፥ ሆን ብሎ ግነትን (hyperbole) በመጠቀም የታወቀ ነበር። በማቴዎስ 5፡29–30 (እና ተመሳሳይ ክፍል በማርቆስ 9፡43–48) ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱ ዓይኖቻቸው ቢያሰናክሏቸው እንዲያወጧቸውና እጆቻቸው ቢያሰናክሏቸው እንዲቆርጧቸው ተናግሯል። ሁላችንም ክርስቶስ ይህንን ትምህርት ቃል በቃል እንዲወስዱ እንዳልፈለገ እንገነዘባለን። ሊያስተላልፍ የፈለገው መልእክት ቢኖር ሰዎች ወደ ኃጢአት የሚመሯቸውን ነገሮች ሁሉ እንዲያስወግዱ ነበር። መልእክቱ ቃል በቃል እንዳልተላለፈ ግን እንዴት እናውቃለን? ምክንያቱም ግነት በጣም ውጤታማ የማስተማሪያ መሣሪያ እንደሆነና በዚህ ጊዜ አስተማሪው ሊያስተላልፍ የፈለገውን መልእክት እንጂ ቃል በቃል የተናገረውን መውሰድ እንደማይገባ በቀላሉ መለየት የሚቻልበት ነው።

ክርስቶስ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን በውጤታማነት ይጠቀም እንደነበረ የሚቀጥሉት ማስረጃዎች ያረጋግጣሉ (ለምሳሌ፥ ማቴ. 6፡21፤ ማር. 3፡24)፥ ዘይቤዎችን (ለምሳሌ፥ ማቴ. 10፡16፤ 5፡13)፥ ግጥሞችን (ለምሳሌ፥ ማቴ. 7፡6–8፤ ሉቃስ 6፡27–28)፥ ጥያቄዎችን (ምሳሌ፥ ማቴ. 17፡25) እና ምፀቶችን (ለምሳሌ፥ ማቴ. 16፡2–3) ይህንንና ሌሎችንም በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተነሡትን አሳቦች ለማዳበር የሚከተለውን መጽሐፍ ብታነብ መልካም ነው። «Robert H. Stein, *The Method and Message of Jesus' Teaching* (Philadelphia: Westminster, 1978).»

## *የክርስቶስ ታሪካዊ ዓውድ በከፊል*

የክርስቶስን ታሪካዊ ዓውድ መልሶ ለማዋቀር በሚደረግ ጥረት ውስጥ ይህ ይበልጥ አስቸጋሪ ነው። በተለይም በወንጌላት ውስጥ ያለ ብዙ ዓውድ የቀረቡትን ብዙ ትምህርቶቹን አስመልክቶ የዓውድ ጉዳይ በቀላሉ የምንገነዘበው አይደለም። ለዚህም ምክንያቱ የክርስቶስ ቃላትና ድርጊቶች ምናልባትም በሠላሳ ዓመታት ጊዜ ውስጥ በቃል የተላለፉ መሆናቸው ነው። በዚህም ጊዜ ጠቅላላው የወንጌል ዜና አልተላለፈም ነበር። በአንዳንድ ታሪኮችና አባባሎች የሚተላለፈው የወንጌላት ይዘት ብቻ ነበር። ከእነዚህ አባባሎች አብዛኞቹ የሚተላለፉት ከቀድሞው ዓውዳቸው ጋር ነበር። ትረካው የሚያገለግለው አባባሎቹን ለማስተላለፍ በመሆኑ፥ ምሁራን እነዚህን *የእወጃ ታሪኮች* ይሏቸዋል። ለዚህ በአብነት የሚጠቀስ የእወጃ ታሪክ ማርቆስ 12፡13–17 ሲሆን፥ ዓውዱም ለሮማውያን ግብር ስለ መክፈል የቀረበ ጥያቄ ነው። ታሪኩ የሚቋጨው «የቄሣርን ለቄሣር፥ የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር ስጡ» በሚለው የክርስቶስ ታዋቂ አባባል ነው። ይህ አባባል ከቀድሞው ዓውዱ ጋር ባይተላለፍልን ኖሮ የቀድሞ ዓውዱን መልሶ ለማዋቀር ምን ልናደርግ የምንችል ይመስልሃል?

ችግሩ የመነጨው ብዙዎቹ የክርስቶስ አባባሎችና ትምህርቶች ያለ ዓውዶቻቸው የተላለፉ ከመሆናቸው ነው። ጳውሎስ ራሱ ይህንን እውነታ ይመሰክራል። የቀድሞ ታሪካዊ ዓውዶችን ሳይገልጽ ሦስት ጊዜ (1ኛ ቆሮ. 7፡10፤ 9፡14፤ የሐዋ. 20፡35) የክርስቶስን አባባሎች ጠቅሷል። እኛም ብንሆን ዓውዶቹን እንዲገልጽ አንጠብቅበትም። ከእነዚህ አባባሎች በ1ኛ ቆሮንቶስ ውስጥ የሚገኙት ሁለቱ በወንጌላትም ውስጥ አሉ። ስለ ፍች የሚናገረው አሳብ ደግሞ በሁለት የተለያዩ ዓውዶች ውስጥ ይገኛል (በማቴዎስ 5፡31–32 ደቀ መዛሙርቱን ባስተማረበት ክፍልና በማቴዎስ 10፡1–19 እና ማርቆስ 10፡1–12 በተጠቀሰው ውዝግብ ውስጥ)። ስለ ክፍያ የሚናገረው አባባል በማቴዎስ 10፡10 የተጠቀሰ ሲሆን፥ ይኸው ተመሳሳይ አሳብ

በሉቃስ 10:7 አሥራ ሁለቱ ልዑካን በተላኩበት (ማቴዎስ) እና ሰባ ሁለቱ ልዑካን በተላኩበት (ሉቃስ) ዓውድ ውስጥ ቀርቧል። ነገር ግን በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የተገለጸው የክርስቶስ አባባል በወንጌላት ውስጥ ስለማይገኝ፥ ለእኛ ሙሉ በሙሉ መነሻ ዓውድ የሌለው ነው።

ስለሆነም፥ ወንጌላውያኑ እንዲህ ዓይነት ብዙ አባባሎች (ዓውድ የሌላቸው) ያውቁ እንደነበርና ወንጌላውያኑ ራሳቸው በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ለአባባሎቹ ዓውዶችን እንዳዘጋጁላቸው መገንዘቡ ሊያስደንቀን አይገባም። በወንጌላት ውስጥ አንዱን አባባል ወይም ትምህርት በተለያዩ ዓውዶች ውስጥ የምናገኝባቸው ምክንያቶች አንዱ ይኼ ነው። ተመሳሳይ ጭብጦች ወይም ርእሰ ጉዳይ ያሏቸው አባባሎች በወንጌላት ውስጥ በርእሰ ጉዳያዊ (topical) መንገድ የሚቧደኑትም (grouped) ለዚሁ ነው።

ለምሳሌ ማቴዎስ አምስት ሰፋፊ የሆኑ ርእሰ ጉዳያዊ ስብስቦች አሉት። (እነዚህም በአብዛኛው «ኢየሱስም ይህን ሁሉ በፈጸመ ጊዜ--- » በሚሉ ዓረፍተ ነገሮች የሚጠቃለሉ ናቸው።) ርእሰ ጉዳያዊ ስብስቦቹም፥ የእግዚአብሔር መንግሥት አኗኗር (የተራራው ስብከት፥ ምዕራፍ 5-7)፥ ለመንግሥቱ አገልጋዮች የተሰጡ ትምህርቶች (10:5-42)፥ በዓለም ስላለው የእግዚአብሔር መንግሥት የሚናገሩ ምሳሌዎች (13:1-52)፥ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ስለሚገኙ ግንኙነቶችና ሥርዓት የተነገሩ ምሳሌዎች (18:1-35)፥ ፍጻሜ፥ ወይም የእግዚአብሔር መንግሥት መመሥረት (23-25) ናቸው።

እነዚህ ማቴዎስ የሰበሰባቸው አሳቦች በምዕራፍ 10 ውስጥ ከሚገኘው ስብስብ እንደሚከተለው በሁለት መንገዶች ሊብራሩ ይችላሉ። (1) ዓውዱ የአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ታሪካዊ ተልእኮና ለአገልግሎት በሚሰዳቸው ጊዜ ክርስቶስ የሰጣቸው ትምህርት ነው (ቁ. 5-12)። በቁጥር 18 ከእስራኤል ወደ ጠፉት በጎች ብቻ እንዲሄዱ የተነገራቸው ሲሆን፥ ቁጥር 18 በገዥዎች፥ ነገሥታትና አሕዛብ ፊት እንደሚቆሙ ስለሚተነብይና ከእነዚህም መካከል የትኞቹም በአሥራ ሁለቱ የመጀመሪያ አገልግሎት ውስጥ ስላልተካተቱ ከቁጥር 16-20 ያለው ለኋለኛው ዘመን የሚያገለግል ነበር። (2) እነዚህ በግሩም ሁኔታ የተሰደሩት አባባሎች በዚህ ቅደም ተከተል በሉቃስ ወንጌል ውስጥ ሰፍረዋል፤ 9:2-5፤ 10:3፤ 21:12-17፤ 12:11-12፤ 6:40፤ 12:2-9፤ 12:51-53፤ 14:25-27፤ 17:33፤ 10:16። ይህም ሉቃስ እነዚህን የተለያዩ አባባሎች ለየብቻቸው እንዳገኘና በተለያዩ ዓውዶች ውስጥ እንዳኖረ ያመለክታል።

ስለሆነም ወንጌላትን በምታነብበት ጊዜ ቁርጥ ያለ ምላሽ ባታገኝለትም እንኳ ልትጠይቃቸው ከሚገቡህ ጥያቄዎች አንዱ ኢየሱስ የሚያቀርበውን ትምህርት የተከታተሉት ሰዎች የቅርብ ደቀ መዛሙርቱ፥ ብዙ ሕዝብ፥ ወይስ ተቃዋሚዎች እንደሆኑ ነው። የክርስቶስን ታሪካዊ ዓውድ ወይም ትምህርቱን የተከታተለው ማን እንደነበር ማወቁ የአንድን አባባል መሠረታዊ ትርጉም አይለውጠም። ነገር ግን ብዙውን ጊዜ ግንዛቤህን በማስፋት ክርስቶስ የተናገረውን አሳብ በትክክል ለመረዳት ያስችልሃል።

## የወንጌላዊው ታሪካዊ ዓውድ

በዚህ ነጥብ ላይ የምንነጋገረው ወንጌላዊው ስለ ኢየሱስ ያዘጋጃቸውን ማቴሪያሎች ስላስቀመጠበት ሥነ ጽሑፋዊ ዓውድ ሳይሆን፥ እያንዳንዱን ወንጌላዊ በመጀመሪያ ደረጃ ወንጌሉን እንዲጽፍ ስላነሣሣው ታሪካዊ ዓውድ ነው። እዚህ በታም የተወሰኑ ምሁራዊ ግምቶችን እንደምንሰጥ መግለጽ ይኖርብናል። ለዚህም ምክንያቱ የወንጌላቱ ጸሐፊዎች በስም አለመታወቃቸውና ከየት እንደ መጡ በትክክል ለማረጋገጥ አለመቻላችን ነው። ነገር ግን ማቴሪያሎቹን ከመረጠበት፥ ከቀረጸበትና ካደራጀበት ሁኔታ እያንዳንዱ ወንጌላዊ ምን ዓይነት ፍላጎቶችና ሸክሞች እንደ ነበሩት ለመረዳት ይቻላል።

ለምሳሌ፥ የማርቆስ ወንጌል የክርስቶስን መሢሕነት ለማብራራት ይፈልጋል። ማርቆስ መሢሑ በኃይልና በርኅራኄ በገሊላ መካከል የተመላለሰ (1፡1–8፡26) የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ቢያውቅም (1፡1)፥ ክርስቶስ መሢሕነቱን ለሰዎች ለመግለጽ እንደማይፈልግም ያውቅ ነበር (ለምሳሌ፥ 1፡34፤ 1፡43፤ 3፡12፤ 4፡11፤ 5፡43፤ 7፡24፤ 7፡36፤ 8፡26፤ 8፡30 አንብብ)። ለዚህም ዝምታ ምክንያቱ መሢሐዊ ፍጻሜውን የሚያውቀው ራሱ ክርስቶስ ብቻ በመሆኑ ነው። በሞት አማካኝነት የሚያሸንፍ መከራ ተቀባይ መሢሕ መሆኑን ከእርሱ በቀር የሚያውቅ አልነበረም። ምንም እንኳ ክርስቶስ ሦስት ጊዜ ለደቀ መዛሙርቱ ስለዚህ ጉዳይ ያብራራላቸው ቢሆንም (8፡27–33፤ 9፡30–32፤ 10፡32–45) ሊገነዘቡት አልቻሉም። ሁለት ጊዜ እጅ እንደ ተጫነበት ዓይነ ስውር (8፡22–26) በግልጽ ለማየት ሁለተኛውን ማረጋገጫ ማለትም ትንሣኤውን ማግኘት ነበረባቸው።

ማርቆስ ክርስቶስ መከራን የሚቀበል ባሪያ መሆኑን ለመግለጽ ጥንቃቄ በማድረጉ ምክንያት በ8፡31–33 ስለ ተቀበለው መከራ ከማብራራቱ በፊት ስለ ክርስቶስ የደቀ መዝሙርነት ትምህርት የተናገረው አልነበረም። የዚህ ድርጊት አንድምታም ሆነ ቀጥተኛ መልእክት በግልጽ የሚታይ ነው። በክርስቶስ ሕይወት ውስጥ ያለፈው

የመስቀል ላይ ሥቃይም ሆነ ባርነት የእውነተኛ ደቀ መዝሙር መለያዎች ናቸው። አንድ ባለ ቅኔ እንዳለው፥ «ይህ ጌታው የሄደበት መንገድ ነው። ባሪያውስ መሄድ የለበትም?»

የማርቆስን ወንጌል በጥንቃቄ ስናነብ ይህንን ሁሉ ልንመለከት እንችላለን። የማርቆስ ታሪካዊ ዓውድ ይሄ ነው። ከዚህ በበለጠ ማጥበቡ ግምታዊ ሥራዎችን የሚያበዛ ይሆናል። ነገር ግን ጥንታዊውን ትውፊት የማንከተልበት ምክንያት የለም። በዚህ ትውፊት መሠረት፥ የማርቆስ ወንጌል የጴጥሮስን «ትውስታዎች» የሚያንጸባርቅ ሲሆን፥ ጴጥሮስ በሰማዕትነት ከሞተ በኋላ ብዙም ሳይርቅ በሮም በከፍተኛ ስደት በሚሠቃዩ ክርስቲያኖች መካከል ታይቷል። ያም ሆነ ይህ፥ እንዲህ ዓይነቱ ዓውዳዊ ንባብ ለመልእክቶች የሚያስፈልገውን ያህል ለወንጌላትም አስፈላጊ ነው።

## ሥነ ጽሑፋዊ ዓውድ

«የክርስቶስ ታሪካዊ ዓውድ በከፊል» በሚለው ክፍል ውስጥ ይህንን አሳብ ቀደም ብለን አንሥተነዋል። ሥነ ጽሑፋዊ ዓውድ በወንጌላት ውስጥ በሚገኝ የትኛውም ዓውድ ውስጥ አንድ አባባል የሚኖረውን ስፍራ የሚመለከት ነው። ይህ ዓውድ ምናልባትም ወንጌላዊው ከሚያውቀው የመጀመሪያ ታሪካዊ ዓውድ ጋር በተወሰነ ደረጃ የሚያያዝ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ቀደም ብለን እንደተመለከትነው፥ አሁን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙት አብዛኞቹ የወንጌላት ዓውዶች ደራሲያኑ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ያዘጋጁቸው ናቸው።

እዚህ ላይ የሚያሳስቡን ነገሮች ሁለት ናቸው። እነዚህም፥ (1) አንድን አባባል ወይም ትረካ በወንጌላት ውስጥ አሁን ባለበት ዓውድ ለማንበብም ሆነ ሐቲታዊ ጥናት ለማካሄድ እንድትችልና (2) ወንጌላት ስለ ክርስቶስ ሕይወት የሚናገሩ የተለያዩ እውነታዎች ብቻ ሳይሆኑ የወጥነት ባሕርይ እንዳላቸው እንድትገነዘብ መርዳት ናቸው።

### *ግለሰብ አባባሎችን መተርጎም*

መልእክቶችን እንዴት መተርጎም እንደሚቻል በምንነጋገርበት ጊዜ አንቀጽ በአንቀጽ ማሰብ እንደሚገባ ገልጸናል። የዚህ ዓይነቱ አሠራር በተለይ ሰፋፊ ትምህርቶች በሚያጋጥሙበት ወቅት ከጊዜ ወደ ጊዜ ጠቃሚ ሆኖ ቢገኝም ለወንጌላት እምብዛም አያገለግልም። ገና ከመጀመሪያው ላይ እንደተገለጸው፥ እነዚህ የማስተማሪያ ክፍሎች ከመልእክቶች ጋር የሚመሳሰሉባቸው አንዳንድ ሁኔታዎች አሉ። ይሁንና፥ ከወንጌላት ልዩ ባሕርይ ሳቢያ እዚህ ላይ ሁለት ነገሮችን

ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል። ይኸውም የአግድም (horizontal) እና የላይ (ላዕላይ) (vertical) አስተሳሰቦች ናቸው።

ይህም ማለት ከወንጌላት አንዱን በምታነብበት ወይም በምታጠናበት ጊዜ ከላይ የቀረቡትን ሁለት አሳቦች መገንዘብ አለብህ ማለት ነው። ይኸውም በቁጥር አራት መሆናቸውንና «ባለ ሁለት ደረጃ» መሆናቸውን ነው።

*አግድማዊ አስተሳሰብ።* በአግድም ማሰብ ማለት አንድ ሰው ከወንጌላት ውስጥ አንድን አባባል በሚያጠናበት ጊዜ በሌሎች ወንጌላት ስለዚያ ተመሳሳይ አባባል የተጻፈውን አሳብ ማንበብ አለበት ማለት ነው። ነገር ግን የትኛውም ወንጌላዊ ወንጌሉ ከሌሎች ጋር በትይዩነት እንዲጠና አስቦ ስላልጻፈው ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ይሆናል። ይህም ሆኖ፥ እግዚአብሔር አራት ወንጌላትን በቀኖና ውስጥ ማካተቱ አንዱ ከሌላው ጋር በማይዛመድ መንገድ እንዲነበብ ስለፈለገ አልነበረም።

*መጀመሪያ* በዚህ ጉዳይ ላይ ማስጠንቀቂያ ለመስጠት እንፈልጋለን። ወንጌላትን እያመሳከሩ በትይዩ የማጥናቱ ዓላማ በአንዱ ውስጥ የሌሉትን ከሌላው እያመጡ ዝርዝር ጉዳዮችን መሙላት አይደለም። ብዙውን ጊዜ እንዲህ ዓይነቱ አሠራር ዝርዝሮችን ሁሉ ወደ አንድነት በማምጣት መንፈስ ቅዱስ በእያንዳንዱ ወንጌል ውስጥ እንዲኖር የፈለገውን ልዩ ገጽታዎች ያደበዝዛል። ያገኘነውን ዝርዝር ሁሉ መሙላቱ ስለ ክርስቶስ ታሪካዊነት ለማወቅ የምንፈልገውን ሁሉ ሊገልጽልን ቢችልም፥ ቀዳሚ ትኩረታችን ሊሆን የሚገባው ቀኖናዊ ደረጃ ግን ይኼ አይደለም።

አግድማዊ አስተሳሰብን እንድናካሄድ የሚያደርጉን መሠረታዊ ምክንያቶች ሁለት ናቸው። <u>አንደኛ</u>፥ ትይዩ የወንጌላት ምዕራፎች በሌሎች ወንጌላት ውስጥ ያሉትን ልዩ አቀራረቦች እንድናደንቅ ያደርጉናል። በመጀመሪያ ደረጃ የአራት ወንጌላት መኖር ያስፈለገውም በእነዚህ ልዩነቶች ምክንያት ነበር። <u>ሁለተኛ</u>፥ ትይዩዎች አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ማቴሪያሎች የተቀመጡባቸውን የተለያዩ ዓውዶች እንድንመለከት ይረዱናል። እነዚህን ነጥቦች ወረድ ብለን የምናብራራ ሲሆን፥ አሁን ግን ስለ ቅድመ ግንዛቤ (presuppositions) አንድ አስፈላጊ ነገር መግለጹ የግድ ይመስለናል።

አስበህበት ባታውቅም እንኳ ወንጌላትን በምታነብበት ጊዜ ስለ ግንኙነቶቻቸው አንድ ዓይነት ቅድመ ግንዛቤ ሊኖርህ እንደሚችል ግልጽ ነው። ብዙ ሰዎች የሚይዙትና ሊሆን የማይችለው አንድ ቅድመ ግንዛቤ ወንጌላት ሁሉ እርስ በርሳቸው ምንም ዓይነት ግንኙነት

ሳይኖራቸው ተጽፈዋል የሚለው ነው። ይህንን አማራጭ እንዳትወስድ የሚከላከሉ በጣም ብዙ ግልጽ መረጃዎች አሉ።

ለምሳሌ፥ ማቴዎስ ማርቆስና ሉቃስ በቃላት አጠቃቀማቸውም ሆነ የክርስቶስን አባባሎች በሚያሰፍሩባቸው ሁኔታዎች በጣም ይመሳሰላሉ። ከሰዎች በተለየ መንገድ ሲናገር ስለነበረው ክርስቶስ የቀረቡ ተመሳሳይ ቃላዊ አገላለጾች ሊያስደንቁን አይገባም። ነገር ግን ይህ በትረካዎችም ውስጥ መከሰቱ ሌላ ነገር ነው። በተለይም የሚከተሉትን ነጥቦች ስትገነዘብ፤ (1) እነዚህ ታሪኮች መጀመሪያ በአረማይክ የተነገሩ ሁነው አሁን የምንነጋገረው ስለ ፅርዕ ቃላት መሆኑን፥ (2) የግሪክ የቃላት አደራደር በጣም ነፃ ሆኖ ሳለ ተመሳሳይነቶቹ በቃላት ቅደም ተከተል ደረጃ ሳይቀር ተግባራዊ ሲሆኑና (3) በተለያዩ ሦስት የሮም ግዛቶች ውስጥ የሚኖሩ ሦስት የተለያዩ ሰዎች አንድን ታሪክ በተመሳሳይ መንገድ መናገራቸው ተአማኒነት የሚጎድለው ይሆናል። ተመሳሳይነቶቹም ከግለሰብ ግለሰብ የሚለያዩ እንደ መስተዋድድና መስተፃምር የመሳሰሉትን የሚጨምር ነው። በመጀመሪያዎቹ ሦስት ወንጌላት ውስጥ የሚታየው ሁኔታ ይህንን የሚመስል ነው።

ይህንን በአራቱም ወንጌላት ውስጥ ከሚገኙ ጥቂት ታሪኮች አንዱ በሆነውና ክርስቶስ አምስት ሺህ ሰዎችን እንደመገበ በሚያስረዳው ታሪክ አማካይነት እናብራራለን።

1. ታሪኩን ለመናገር ያገለገሉ የቃላት ብዛት

| | |
|---|---|
| ማቴዎስ | 157 |
| ማርቆስ | 194 |
| ሉቃስ | 153 |
| ዮሐንስ | 199 |

2. በመጀመሪያዎቹ ሦስት ወንጌላት ውስጥ በጋራ ያገለገሉ የቃላት ብዛት 53።

3. ዮሐንስ ከሌሎች ወንጌላት የተጋራቸው የቃላት ብዛት 8። (አምስት፥ ሁለት፥ አምስት ሺህ፥ እንጀራውን ወሰደ፥ አሥራ ሁለት መሰብ ትርፍራፊ)

4. የወንጌላቱ ስምምነት በመቶኛ ሲተመን

| | |
|---|---|
| ማቴዎስ ከማርቆስ ጋር | 59% |

| | |
|---|---|
| ማቴዎስ ከሉቃስ ጋር | 44 |
| ሉቃስ ከማርቆስ | 40 |
| ዮሐንስ ከማቴዎስ | 8.5 |
| ዮሐንስ ከማርቆስ | 8.5 |
| ዮሐንስ ከሉቃስ | 6.5 |

ከዚህ ስንነሣ ቀጣዩ ድምዳሜ አማራጭ የሌለው ይመስላል። ዮሐንስ ታሪኩን የተናገረው ከሌሎቹ ወንጌላት ነፃ በሆነ ሁኔታ ነው። ከሌሎቹ ጋር የተጋራው አንዱን ታሪክ ለመናገር ፍጹም አስፈላጊ የሆኑትን ቃላት ብቻ ሲሆን፥ ዓሣ ለሚለውም ቃል ሳይቀር የተጠቀመው የዕርዕ ቃል ከሌሎቹ የተለየ ነው። ሌሎች ሦስቱ በሆነ መንገድ ተደጋግፈው የቀረቡ ናቸው። የዕርዕ ቋንቋ የሚያውቁ ሰዎች ሁለት ግለሰቦች አንድን ተመሳሳይ ታሪክ ለየብቻቸው ቢናገሩ በተጠቀሟቸው ቃላትና ብዙውን ጊዜ ደግሞ በተመሳሳይ ቃላት በመገልገል 60 በመቶ ስምምነት ሊኖራቸው እንደማይችል ይገነዘባሉ።

በማርቆስ 13፡14 እና በትይዩ ምንባብ በማቴዎስ 24፡15 («አንባቢው ያስተውል») የቀረበውን ዓረፍተ ነገር ተጨማሪ ምሳሌ አድርገህ ውሰድ። በዚህ ዓረፍተ ነገር ውስጥ የሚገኙ ቃላት የሥነ ቃል አካላት አይመስሉም። (አንባቢ እንጂ ሰሚ አይልም። ቀደም ብሎ በተጻፈበት መልኩ [ማርቆስ] የዳንኤል ስም ስላልተጠቀሰ፥ ክርስቶስ ዳንኤልን የሚያመለክት አይመስልም)። ስለሆነም እነዚህን ቃላት ለአንባቢዎቹ ለማስማማት ሲል በክርስቶስ አባባል ውስጥ የጨመረው ከወንጌላውያኑ አንዱ ነበር ማለት ነው። በራሳቸው መንገድ የሚጽፉ ሁለት ደራሲያን በተመሳሳይ መንገድ አንድ ቦታ ላይ የማሳሰቢያ መልእክት ያሰፍራሉ ብሎ ማሰብ አይቻልም።

ለዚህ ከሁሉም የሚሻለው ማብራሪያ ቀደም ሲል ያቀረብነው ነው። ማርቆስ በከፊልም ቢሆን ምናልባት ከጴጥሮስ ስብከትና ትምህርት የሚያስታውሰውን በማቀነባበር መጀመሪያ ወንጌሉን ጻፈው። ሉቃስና ማቴዎስ ደግሞ የማርቆስን ወንጌል አግኝተው የራሳቸውን ወንጌል ለመጻፍ እንደ መሠረታዊ ምንጭ ተጠቀሙበት። ነገር ግን ስለ ክርስቶስ የሚናገሩ ሌሎች ታሪኮችንም ያውቁ ነበር። ከእነዚህም አንዳንዶቹን በጋራ ያውቋቸው ነበር። ነገር ግን ይህ በጋራ የሚያውቁት ማቴሪያል በሁለቱ ወንጌላት ውስጥ እምብዛም በተመሳሳይ ቅደም ተከተል አልቀረበም። ይህም ከሁለቱ አንዱ የሌላውን ጽሑፍ

እንዳላገኘ የሚጠቁም ነው። በመጨረሻም፥ ዮሐንስ ከሌሎቹ በተለየ መንገድ የጻፈ ሲሆን፥ የእርሱ መጽሐፍ ከሦስቱ ጋር ብዙም ተመሳሳይ ማቴሪያሎች የሉትም። መንፈስ ቅዱስ የወንጌላትን አጻጻፍ የመራው በዚህ መንገድ እንደነበር እንገነዘባለን።

ይህ አሳብ ወንጌላትን ለመተርጎም የሚረዳህ መሆኑ ከሚከተለው አጭር ምሳሌ ሊታይ ይችላል። በትይዩ ዓምዶች በምናነብበት ጊዜ ክርስቶስ ስለ «ጥፋት ርኩሰት» የተናገረው ምን እንደሚመስል ተመልከት።

| ማቴዎስ 24:15–16 /ከአ.መ.ት./ | ማርቆስ 13:14 | ሉቃስ 21:20–21 |
|---|---|---|
| እንግዲህ | የጥፋት ርኩሰት | ኢየሩሳሌም በጦር ሠራዊት ተከባ በምታዩበት ጊዜ፣ ጥፋቷ መቃረቡን ዕወቁ። |
| በነቢዩ በዳንኤል የተነገረው፥ የጥፋት ርኩሰት በተቀደሰው ስፍራ ቆሞ | ስፍራው ባልሆነ ቦታ ቆሞ | |
| ስታዩ | በምታዩበት ጊዜ | |
| አንባቢው | አንባቢው | |
| ያስተውል | ያስተውል | |
| በዚያን ጊዜ | በዚያን ጊዜ | በዚያን ጊዜ |
| በይሁዳ የሚገኙ | በይሁዳ ያሉ | በይሁዳ ያሉ |
| ወደ ተራራዎች | ወደ ተራሮች | ወደ ተራራዎች |
| ይሽሹ | ይሽሹ | ይሽሹ |

በመጀመሪያ ደረጃ ይህ አባባል በሦስቱም ወንጌላት ውስጥ ክርስቶስ በደብረ ዘይት ተራራ ባቀረባቸው ትምህርቶች ውስጥ በተመሳሳይ ቅደም ተከተል እንደቀረበ መገንዘቡ ተገቢ ነው። ማርቆስ እነዚህን ቃላት ሲያሰፍር ክርስቶስ የጥፋት ርኩሰት የእርሱ ባልሆነ ቦታ እንደ ቆመ ሲናገር ምን ማለቱ እንደሆነ አንባቢያዎቹ እንዲገነዘቡለት ይፈልግ ነበር። ማቴዎስ ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት

ትንሽ ነገር በመጨመር ለአንባቢያኑ አሳቡን ግልጽ ለማድረግ ሞክሯል። «የጥፋት ርኩሰት» በዳንኤል የተገለጸ መሆኑን ለአንባቢዎቹ በማስታወስ፥ ክርስቶስ ሊሆን በማይገባው ስፍራ ሲል «የተቀደሰ ስፍራ» (ማለትም በኢየሩሳሌም የሚገኘው ቤተ መቅደስ) ማለቱ እንደሆነ ገልጾአል። ሉቃስም በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ለአሕዛብ አንባቢያዎቹ ጠቅላላውን መልእክት ተርጉሟል። በዚህም ሊተላለፍ የተፈለገውን መልእክት እንዲጨብጡ ረድቷቸዋል። ክርስቶስ በዚህ ሁሉ ለማስተላለፍ የፈለገው መልእክት ቢኖር፥ «ኢየሩሳሌም በጦር ሠራዊት ተከብባ በምታዩበት ጊዜ፥ ጥፋቷ መቃረቡን እወቁ» የሚል ነበር።

ከዚህም አግድም ማሰብና ማቴዎስና ሉቃስ የማርቆስን ወንጌል በማጣቀሻነት እንደ ተጠቀሙ መገንዘብ ወንጌላትን ለመተርጎም እንዴት እንደሚጠቅም መረዳት ይቻላል። በተጨማሪም የወንጌልን ትይዩ ምንባቦች ማወቁ አንድ ማቴሪያል እንዴት በተለያዩ ዓውዶች ውስጥ ሊያገለግል እንደሚችልም ለመገንዘብ ያስችላል።

ለምሳሌ፥ በማቴዎስና ሉቃስ ውስጥ የሰፈረ ሆኖ ሳለ በማርቆስ ውስጥ የሌለውን ክርስቶስ ለኢየሩሳሌም ያለቀሰበትን ታሪክ ውሰድ። ይህ ታሪክ በሁለቱ ወንጌላት ውስጥ የቃል በቃል ምስስሎሽ ያለው ይመስላል። በሉቃስ 13፡34–35 ይህ ታሪክ ክርስቶስ ወደ ኢየሩሳሌም እየሄደ ሳለ ስላቀረበው ትምህርት በሚናገር ረዥም ትረካ ውስጥ ሰፍሯል (9፡51–19፡10)። ይህም ክርስቶስ ምላሹን፥ «ነቢይ ከኢየሩሳሌም ውጭ ይሞት ዘንድ አይገባምና» በማለት የደመደመበትን የሄሮድስን ማስጠንቀቂያ ተከትሎ የሚመጣ ነው።

በማቴዎስ 23፡27–39 ሙሾው በፈሪሳውያን ላይ የቀረቡትን ሰባት ወዮዎች የሚደመድም ሲሆን፥ የመጨረሻው ወዮ ነቢያት በኢየሩሳሌም መሞታቸውን ያስረዳል። ስለሆነም ምንም እንኳ በተለያዩ ዓውዶች ውስጥ ቢቀመጥም የሙሾው ታሪክ በሁለቱም ወንጌላት ውስጥ የሚያስተላልፈው መልእክት ተመሳሳይ ነው።

የሌሎችም ብዙ አባባሎች ሁኔታ እንደዚሁ ነው። ምንም እንኳ የሁለቱም ክፍሎች ዋንኛ ትኩረት የተለያየ ቢሆንም፥ የጌታ ጸሎት በሁለት ወንጌላት ውስጥ (ማቴ. 6፡7–13፤ ሉቃስ 11፡2–4) የቀረበው ስለ ጸሎት ትምህርት በሚሰጥባቸው ዓውዶች ውስጥ ነው። በማቴዎስ «እንዲህ ጸልዩ» ተብሎ በሞዴልነት እንዲያገለግል እንደታሰበ አስተውል። በሉቃስ «እንዲህ በሉ» በሚል ድግግሞሽ ተፈቅዷል። የብፅዕና ምንባቦችንም እንዲሁ ተመልከት (ማቴ. 5፡3–11፤ ሉቃስ 6፡20–23)። ማቴዎስ በመንፈስ ድሆች ስለሆኑት ሲናገር ፥ ሉቃስ ግን

ከባለጠጎች በተቃራኒ ጎራ የሚገኙትን ድሆች ይጠቅሳል (6፡24)። በእንዲህ ዓይነት ነጥቦች ላይ ብዙዎቹ ሰዎች ከፊል ቀኖና ብቻ ወደ መያዙ ያዘነብላሉ። ትውፊታዊ የወንጌል አማኞች «በመንፈስ ድሆች» ስለሆኑት የሚናገረውን ብቻ ወደ መውሰዱ ያዘነብላሉ። በማኅበራዊ ተሐድሶ ላይ የሚያተኩሩ ወገኖች ደግሞ «ድሆች» በሚለው ላይ ያተኩራሉ። እኛ ግን ሁለቱም ቀኖናዊ ነው ብለን እናምናለን። ከመሠረታዊ ግንዛቤ አንጻር ትክክለኞቹ ድሆች በእግዚአብሔር ፊት ምስኪኖች መሆናቸውን የሚገነዘቡ ሰዎች ናቸው። ነገር ግን በናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ሥጋ የለበሰው የመጽሐፍ ቅዱሱ አምላክ የተጨቆኑትንና መብታቸውን ያጡትን ወገኖች ሙግት የሚሟገት ነው። ለዚሁ የመለኮታዊ መገለጥ ገጽታ የሰጠውን ትኩረት ሳይገነዘቡ የሉቃስን ወንጌል ማንበብ አይቻልም። (14፡12-14ን አንብብ። 12፡33-34ን ከማቴዎስ ትይዩ ምንባብ ከ6፡19-21 ጋር አነጻጽር።)

እዚህ ጋ አንድ የመጨረሻ ቃል መናገሩ ተገቢ ይሆናል። ጠንከር ያለ የወንጌላት ጥናት ለማካሄድ ከፈለግህ፥ ወንጌላት በትይዩነት የቀረቡበትን ዓምድ (synopsis) ማጣቀስ ይኖርብሃል። ከእነዚህ መካከል በጣም ጥሩው መጽሐፍ በካርት አላንድ ኤዲተርነት የቀረበው *Synopsis of the Four Gospels* (New York: United Bible Societies, 1975) መሆኑን ልንጠቁምህ እንሻለን።

*የላይ (ላዕላይ) አስተሳሰብ፦* ይህ ማለት በወንጌላት ውስጥ የቀረበውን ትረካ ወይም ትምህርት በምታነብበት ወይም በምታጠናበት ጊዜ የክርስቶስንም ሆነ ወንጌሉን የጻፈውን ወንጌላዊ ታሪካዊ ዓውድ ለማወቅ መጣር አለብህ ማለት ነው።

እዚህ ላይ በመጀመሪያ ደረጃ ማስጠንቀቂያ መስጠት ይኖርብናል። የላዕላይ አስተሳሰብ ቀዳማይ ዓላማ ታሪካዊ ስለሆነው የክርስቶስ ሕይወት ለማጥናት አይደለም። ያ ሁልጊዜም ለሁላችንም አስደሳች ነገር ነው። ይሁንና፥ ወንጌላት አሁን ባሉበት ቅርጽ ለእኛ የእግዚአብሔር ቃል ናቸው። ራሳችን ስለ ክርስቶስ ሕይወት መልሰን የምናዋቅረው አሳብ ግን የእግዚአብሔር ቃል ሊሆን አይችልም። አሁንም እንዲህ ዓይነቱን አሳብ ማጋነን የለብንም። በወንጌላት ውስጥ የቀረቡት ማቴሪያሎች ዓውዳቸውን ከወንጌላውያኑ ያገኙ ሲሆን፥ ጥሩ የተዋጣ አተረጓጎም አንድ አባባል አሁን ያለበትን ቀኖናዊ ዓውድ ከመገንዘቡ በፊት ኦሪጂናል ታሪካዊ ዓውዱን ለመመልከት ሊፈልግ ይችላል።

ይህንን ክርስቶስ ስለ ወይን ሠራተኞች በተናገረው (ማቴዎስ 20፡1-16) ዓይነት ምንባባ ልናብራራው እንችላለን። ትኩረታችን ይህ

አሳብ አሁን በማቴዎስ ውስጥ ባለው ዓውድ የሚያስተላልፈው መልእክት ምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ መመለስ ነው። መጀመሪያ አግድማዊ አስተሳሰብ ብንወስድ፥ በየትኛውም የምሳሌው ወገን ማቴዎስ ማርቆስን በቅርብ ተከትሎ የጻፋቸው ሰፊ አሳቦች እንዳሉት እንገነዘባለን (ማቴ. 19:1–30፤ 20:17–34 ትይዩ ምንባብ ማር. 10:1–52)። በ10:31 ማርቆስ፥ «ብዙ ፊተኞች የሆኑ ኋለኞች፤ ኋለኞች የሆኑም ፊተኞች ይሆናሉ» የሚል አባባል ነበረው። ማቴዎስ ምሳሌውን ከተናገረ በኋላ ይህንኑ የማርቆስን አባባል ቅደም ተከተሉን ለውጦ በማስገባት ያጠቃልላል (20:16)። እንግዲህ በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ለምሳሌው የቅርብ ዓውድ ስለ ነገሮች የቅደም ተከተል ልውውጥ የሚናገረው አባባል ነው ማለት ነው።

ምሳሌው (20:1–15) ባለቤቱ ትክክለኛ የልግስና ተግባር እንዳከናወነ ያስረዳል። ክርስቶስ እንደሚለው፥ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ለሰዎች ክፍያ የሚሰጠው ትክክል በሆነው አሠራር ሳይሆን በእግዚአብሔር ጸጋ ነው። በመጀመሪያ ዓውዱ ይህ ምሳሌ ክርስቶስ የፈሪሳውያንን ተቃውሞ ጥሶ ኃጢአተኞችን የመቀበሉን ተግባር የሚያጸድቅ ነበር። ስለ ራሳቸው ቀኑን ሁሉ እንደ ሠሩና የበለጠ ክፍያ እንደሚገባቸው አስበው ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ቸር ስለሆነ፥ «ጻድቃንን» እንደሚቀበል ሁሉ ኃጢአተኞችንም በነፃ ይቀበላል።

ከዚህ የመጀመሪያ ዓውድ ስንነሣ፥ ምሳሌው አሁን በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ የሚያገለግለው እንዴት ነው? እግዚአብሔር ለማይገባቸው ሰዎች ቸርነቱን እንደሚያደርግ የሚያስረዳው የምሳሌው መልእክት አሁንም እንዳለ ነው። አሁን ግን ያ አሳብ ያገለገለው የክርስቶስን ተግባር ለማጽደቅ አይደለም። የማቴዎስ ወንጌል ያንን በሌላ ስፍራ በሌሎች መንገዶች ያከናውናል። እዚህ ላይ ምሳሌው ያገለገለው በደቀ መዝሙርነት ዓውድ ሲሆን፥ ክርስቶስን ለመከተል ሁሉን የተዉት ኋለኞች ፊተኞች ሊሆኑ እንደቻሉ ያስረዳል። (ይህ ምናልባትም ማቴዎስ በተደጋጋሚ ከሚያነሣው የአይሁድ መሪዎች ጉዳይ ጋር የሚነጻጸር ሊሆን ይችላል።)

የላዕላይ አስተሳሰብ ብዙውን ጊዜ ተመሳሳይ አሳብ በሁለቱም ደረጃዎች እንደሚካሄድ የሚያመለክት ሲሆን፥ እንዲህ ዓይነት አስተሳሰብ ለሐቲት ምን ያህል ጠቃሚ ሊሆን እንደሚችል አሁን የተመለከትነው ምሳሌ ያብራራልናል።

### *ወንጌላትን እንደ ወጥ መተርጎም*

ከሥነ ጽሑፋዊ ዓውድ ጠቃሚ አካላት አንዱ እያንዳንዱን ወንጌል ልዩ የሚያደርጉትን ነገሮች ቅንጅት ማጤን ነው።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ እንደተመለከትነው፥ ወንጌላትን የሚያጠና ሰው ወንጌላውያኑ ክርስቶስ ያደረጋቸውንና የተናገራቸውን ቃላት መውደዳቸውን ብቻ ሳይሆን ለራሳቸው አንባቢዎች የመረጧቸውን ታሪኮች፥ ለምን እንደገና ለመናገር እንደፈለጉም ማወቅ እንዳለበት ተመልክተናል። የተመለከትናቸው ወንጌላውያን ደግሞ አቀናባሪዎች ብቻ ሳይሆኑ ደራሲያንም ጭምር ነበሩ። ደራሲያን ነበሩ ሲባል ግን ያስተላለፉዋቸውን ማቴሪያሎች ፈጥረዋል ማለት አይደለም። እውነታው የዚህ ተቃራኒ ነው። የማቴሪያሉ የተወሰነ መሆንና የመንፈስ ቅዱስን ሉዓላዊ ቁጥጥርን ጨምሮ አያሌ ነገሮች የደራሲያኑን የፈጠራ ክህሎት አግደዋል። ስለሆነም ደራሲነታቸው በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ያገኙትን ማቴሪያል አዋቅረውና የአንባቢዎቻቸውን ፍላጎት በሚያሟላ መልኩ ጽፈው ማቅረባቸውን የሚያመለክት ነው። እዚህ ላይ የሚያሳስበን ወንጌላትን በምታነብበት ጊዜ እያንዳንዱ ወንጌላዊ ለማቀናጀት የፈለጋቸውን አሳቦች መገንዘብህ ነው።

በወንጌላት ቅንጅት ውስጥ ሦስት መርሆዎች ተግባራዊ ድርሻ ነበራቸው። እነዚም ምርጫ፥ ማደራጀትና ማስማማት ናቸው። በአንድ በኩል መለኮታዊ የመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ እንደ ተሰጣቸው ደራሲያን ወንጌላውያኑ ለራሳቸው ዓላማ የሚመጥቸውን መልእክቶች መርጠዋቸዋል። በእርግጥ ከእነዚያ ዓላማዎች አንዱ የሚያውቋቸውን መልእክቶች ለትውልድ ማስተላለፍ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ጥቂትና በሰፊው የተገለጹ ትረካዎችንና ትምህርቶችን ያቀረበው ዮሐንስ ለዓላማው የሚስማሙትን ማቴሪያሎች መርጦ እንዳሰፈረ ይነግረናል (20፡30–31፤ 21፡25)። በግንት የተነገረው የመጨረሻው ቃል (21፡25) ሌሎችም እንደዚህ ዓይነት አመለካከቶች እንደ ነበራቸው የሚያሳይ ሊሆን ይችላል። ሉቃስ ለምሳሌ ከማርቆስ ወንጌል ብዙ አሳቦችን ላለማካተት መርጧል (6፡45–8፡26)።

ወንጌላውያኑና አብያተ ክርስቲያኖቻቸው ልዩ ፍላጎት የነበራቸው መሆኑ ደግሞ የተመረጠውን ማቴሪያል እንዲያደራጁና ከራሳቸው ሁኔታ ጋር እንዲያስማሙ አድርጓቸዋል። ዮሐንስ ለምሳሌ፥ «ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ፣ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እንድታምኑ» (20፡31) ሲል ሥነ መለኮታዊ ዓላማ እንዳለው ገልጾአል። በሲኖፕቲክስ (ማቴዎስ፥ ማርቆስና ሉቃስ) የገሊላ አገልግሎቱ በሰፊው ተጠቅሶ ሳለ ዮሐንስ በይሁዳና በኢየሩሳሌም ባካሄዳቸው አገልግሎቶች ላይ ያተኮረው ክርስቶስ የአይሁድ መሢሕ መሆኑን ለማሳየት ስለፈለገ ሳይሆን አይቀርም። ለአይሁዶች የመሢሑ እውነተኛ ቤት ኢየሩሳሌም ነበረች። ስለሆነም ክርስቶስ ነቢይ በአገሩ እንደማይከበር መናገሩን ዮሐንስ ያውቅ ነበር። ይህ መጀመሪያ የተነገረው በናዝሬት ተቀባይነት

ባጣበት ወቅት ሲሆን (ማቴ. 13፡57፤ ማር. 6፡4፤ ሉቃ. 4፡24)፥ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ መሚሑ በኢየሩሳሌም ተቀባይነት ያጣበትን ምክንያት ለመግለጽ አገልግሏል (4፡44)። ይህም ዮሐንስ የክርስቶስን አገልግሎት ጠልቆ የተመለከተበት ሥነ መለኮታዊ እይታ ነበር።

በወንጌላት ውስጥ ይታያሉ የሚባሉትን ልዩነቶች የሚያብራራው ደግሞ ከአካባቢው ጋር የማስማማት መርህ ነው። በዚህ ረገድ ትልቅ ትኩረት ከተሰጣቸው መካከል የበለስ ዛፍ መረገም አንዱ ነው (ማር. 11፡12-14፤ 20-25፤ ማቴ. 21፡18-22)። በማርቆስ ወንጌል ታሪኩ ተምሳሌታዊ የሥነ መለኮት አገልግሎት እንዲያበረክት ነበር የተነገረው። ክርስቶስ በለሲቱን በረገመበትና በምትጠወልግበት ጊዜ መካከል ቤተ መቅደሱን በማንጻት በይሁዳ ላይ ፍርድን እንደሚያውጅ አስተውል። ነገር ግን በማጠቃለያው ላይ በቀረበው የእምነት ትምህርት ምክንያት የበለስ ዛፍ ታሪክ ለቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን ትልቅ ፍች ነበረው። በማቴዎስ ወንጌል ታሪኩ ያተኮረው በእምነት ትምህርት ላይ በመሆኑ፥ በዚሁ ነጥብ ላይ አጽንኦት ለመስጠት ሲል መረገሟንና መጠውለጓን አከታትሎ ያቀርባል። በእያንዳንዱ ሁኔታ ውስጥ ታሪኩ በዚህ መንገድ እንዲነገር ያደረገው ሁለቱንም ወንጌላውያን የመራው መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ልብ በል።

ይህንን የቅንጅት ሂደት ሰፋ ባለ መልኩ ለማብራራት እስኪ የማርቆስ ወንጌልን የመጀመሪያ ምዕራፎች እንመልከት (1፡14-3፡6)። እነዚህ ምዕራፎች በሥዕላዊ መልክ የቀረቡ በመሆናቸውና በጥሩ ሁኔታ ስለ ተዋቀሩ፥ ብዙ አንባቢዎቹ እንዴት እንዳደረገው ባያውቁም እንኳ የማርቆስን አሳብ ማግኘታቸው አያጠራጥርም።

ማርቆስ ያተኮረባቸው የክርስቶስ ይፋዊ አገልግሎት አላባውያን ሦስት ሲሆኑ፥ እነዚህም ለብዙ ሕዝብ ማስተማሩ፥ ጥቂቶችን ደቀ መዝሙር ማድረጉና ከባለሥልጣናት የሚደርስበት ተቃውሞ ነበሩ። ማርቆስ በጥበብ ትረካዎችን በመምረጥና በማደራጀት እንዴት እነዚህን ነጥቦች ከፊታችን እንደሚያኖር ተመልከት። ክርስቶስ ይፋዊ አገልግሎቱን ከጀመረ በኋላ (1፡14-15)፥ የመጀመሪያው ትረካ የመጀመሪያዎቹን ደቀ መዛሙርት ጥሪ ያቀርባል። ይህ ጭብጥ በሚቀጥሉት ክፍሎች ውስጥ ይብራራል (3፡13-19፤ 4፡10-12፤ 4፡34-41፥ ወዘተ...)፤ በእነዚህ ሁለት የመጀመሪያ ምዕራፎች ማርቆስ በሁለት ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ትኩረት አድርጓል። ከ1፡21 እስከ 1፡45 ማርቆስ አራት ታሪኮችን ገልጾ መነሣቱ ነበር። እነዚህም የቅፍርናሆም ውሎ (1፡21-28 እና 29-34)፥ በቀጣዩ ዕለት የተደረገ አጭር የስብከት ጉብኝት (1፡35-39) እና የለምጻሙ መፈወስ ናቸው (1፡40-45)። በዚህ ክፍል ከዳር እስከ ዳር የቀረበው ጭብጥ የክርስቶስ ዝናና

ታዋቂነት በፍጥነት መውጣቱ ነው (ቁ. 27–28፥ 32–33፥ 37፥ 45)። ይህ ጭብጥ የተቋጨው፥ «ኢየሱስ ወደ ማንኛውም ከተማ በግልጽ መግባት አልተቻለውም--- ሰዎች ግን ከየአቅጣጫው እርሱ ወዳለበት መምጣት አላቋረጡም» በሚሉ ዓረፍተ ነገሮች ነው። ይህ ሁሉ አስደሳች ይመስላል። ነገር ግን ማርቆስ ገለጻውን ያቀረበው አራት ትረካዎችንና «ወዲያውም» የሚለውን ተደጋጋሚ ቃል በመጠቀም ነው (1፡21፥ 23፥ 28፥ 29፥ 31፥ 42፤ ይህ ቃል በኤን አይ ቪ ውስጥ መጥፋቱ አሳዛኝ ነገር ነው)። በተጨማሪም ሁሉንም ዓረፍተ ነገሮች ማለት ይቻላል «እና» በሚል ቃል ነበር የጀመረው (ይህም ቃል ኤን አይ ቪ ውስጥ አልተጠቀሰም፥)።

ማርቆስ ይህንን ገለጻ በማቅረብ የተቃውሞን ሥዕል በመሣል ምክንያት የሚሰጡትን አምስት የተለያዩ ዓይነት ትረካዎች ይመርጣል። የመጀመሪያው አባባል የጋራ ጭብጥ «ለምን?» የሚል መሆኑን ተመልከት (2፡7፥ 16፥ 18፥ 24)። ተቃውሞ የተነሣው ክርስቶስ ኃጢአትን ይቅር በማለቱ፥ ከኃጢአተኞች ጋር በመብላቱ፥ የጾምን ባሕላዊ ድርጊት በማስወገዱና ሰንበትን ባለማክበሩ ነበር። ማርቆስ በ3፡1–6 ተመሳሳይ ትረካ ማቅረቡ ሰንበትን አለማክበር ለአይሁዶች ምን ያህል ከፍተኛ ነውር እንደሆነ ያመለክታል።

በወንጌላት ውስጥ ከሚገኙት ክፍሎች ሁሉ የወንጌላዊውን መልእክት ቅንጅታዊ ትኩረት በቀላሉ ማግኘት እንደሚቻል ለመግለጽ አንደፍርም። ነገር ግን ከወንጌላት ልትፈልግ የሚገባህ እንዲህ ዓይነቱን ነገር እንደሆነ ልንጠቁምህ እንሻለን።

### አንዳንድ ሥነ አፈታታዊ ምልከታዎች

በአመዛኙ ወንጌላትን ለመተርጎም የሚያግዙ ሥነ አፈታታዊ መርሆች ቀደም ሲል ስለ መልእክቶችና ታሪካዊ ትረካዎች የተገለጹት ናቸው።

### ትምህርቶችና ትእዛዛት

ሐቲቱ በትክክል ከተካሄደ በኋላ በወንጌላት ውስጥ የሚገኙት የክርስቶስ ትምህርቶችና ትእዛዛት ወደ ሃያኛው ክፍለ ዘመን መምጣት አለባቸው። ይህም የጳውሎስን፥ የጴጥሮስን፥ ወይም የያዕቆብን መልእክቶች ከዛሬው ዘመን ክርስቲያኖች ሕይወት ጋር የምናዛምድበት ዓይነት ነው። የክርስቶስ ተከታዮች ለሆኑት ባልና ሚስት ፍች እምብዛም አማራጭ ሊሆን አይችልም። ይህንንም አሳብ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 7፡10–11 ደግሞ ገልጾታል። ነገር ግን ከሁለት አማኞች አንዱ ትዳሩን በሚፈታበት እንደ አሜሪካ ባለ ባሕል ውስጥ የዳግም

ጋብቻን ጉዳይ በቀላሉና ለአዳዲስ አማኞች መፍትሔ ሳይፈልጉ መወሰን አይቻልም። ፍጹም በተለየ ባሕላዊ ዓውድ ውስጥ ስለተነገሩት የክርስቶስ ቃላት ፍች አንድ ሰው የሚኖረው የቀድሞ ግንዛቤ በጥንቃቄ መመርመር አለበት። በተመሳሳይ ሁኔታ በአሁኑ ዘመን አንድ ምዕራፍ እንድንሄድ የሚጠይቅ ሮማዊ ወታደር ሊገጥመን አይችልም (ማቴ. 5፡41)። ነገር ግን ይህ የክርስቶስ ትእዛዝ በሌሎች ክርስቲያናዊ ገጠመኞች ውስጥ ተግባራዊ ሊሆን ይችላል።

እዚህ ላይ አንድ ጠቃሚ አሳብ መግለጽ አለብን። ብዙዎቹ የክርስቶስ ትእዛዛት በብሉይ ኪዳን ዓውድ ላይ ያረፉ በመሆናቸውና ብዙ ሰዎች ደግሞ ለመፈጸም እንደሚያዳግታቸው ፍጹማዊ ተግባራት አድርገው ስለሚመለከቷቸው፥ አያሌ ሥነ አፈታታዊ ዘዴዎች ተቀይሰዋል። እነዚህም ዘዴዎች ትእዛዛቱ ለቤተ ክርስቲያን ሁሉ የሚያገለግሉ የሥልጣን ቃላት እንደሆኑ የሚያስረዱ ናቸው። በዚህ ስፍራ ለእነዚህ የተለያዩ ሙከራዎች ምላሽ ለመስጠት ባንሻም፥ አንዳንድ አሳቦችን ለመሰንዘር እንፈልጋለን። በዚህ ረገድ *"The Method and Message of Jesus' Teaching»* በሚለው የስቴይን መጽሐፍ ውስጥ በምዕራፍ 6 ግሩም አሰሳ ተካሂዷል።

እነዚህ አብዛኞቹ ሥነ አፈታታዊ ዘዴዎች የሚመነጩት ትእዛዛቱ ሕግ ስለሚመስሉ ነው፤ ለዚያውም የማይቀመስ ሕግ! የክርስቲያን ሕይወት ደግሞ በአዲስ ኪዳን መሠረት በሕግ ሳይሆን በጸጋ ላይ የተመሠረተ ነው። ስለሆነም ትእዛዛቱን እንደ ሕግ መውሰዱ መልእክታቸውን በትክክል እንዳንረዳ ያደርጋል። እነዚህ ትእዛዛት አንድ ሰው ክርስቲያን ለመሆን ወይም በክርስትናው ለመሰንበት የሚጠብቃቸው ሕግጋት አይደሉም። ደኅንነታችንን የምናገኘው ሙሉ በሙሉ እነዚህን ትእዛዛት በመጠበቅ አይደለም። ነገር ግን ክርስቶስ አስቀድሞ ስለተቀበለን የክርስትና ሕይወታችን ምን ሊመስል እንደሚገባ የሚያዙን ናቸው። ያለ መበቀል ሥነ ምግባር (ማቴ. 5፡38–42) ለአሁኑ ዘመን የእግዚአብሔር መንግሥት ሥነምግባር ነው። ይህ ምግባር የተተነበየው ግን እግዚአብሔር ለእኛ ባሳየው በቀል በሌለበት ፍቅር ላይ ተመሥርቶ ነው። ስለሆነም በእግዚአብሔር መንግሥት የሚኖረን ግንኙነት «የአባትና የልጅ» ዓይነት መሆን ይኖርበታል። መጀመሪያ የእግዚአብሔርን በምንም ቅድመ ሁኔታ ላይ ያልተመሠረተና ያልተገደበ ይቅርታ እንቀበልና ለሌሎች መልሰን እንሰጣለን። አንድ ሰው እንዳለው፥ በክርስትና ሃይማኖት ጸጋ ነው። ሥነ ምግባርም ብፅዕና ነው። ስለሆነም የክርስቶስ ትእዛዛት ለእኛ የተላለፉ ቃላት ናቸው። ነገር ግን እንደ ብሉይ ኪዳን ሕግጋት አይደሉም። አዲሱን ሕይወት ይገልጹታል። ይህ ሕይወት ግን ሌላ

አማራጭ የለውም። ይኸውም አንድ ሰው በእግዚአብሔር እንደ ተወደደና እንደ ዳነ ልጅ መኖር እንዳለበት ነው።

### *ትረካዎች*

በወንጌላት ትረካዎች ከአንድ በበለጡ መንገዶች ወደ ማገልገሉ ያዘነብላሉ። ለምሳሌ፥ የተአምራት ታሪኮች የተመዘገቡት ሥነ ምግባራዊ ትምህርት ለማስተላለፍ ወይም እንደ ሞዴል ለማገልገል አይደለም። ነገር ግን በክርስቶስ አገልግሎት እየተገለጠ ያለውን የእግዚአብሔርን መንግሥት ኃይል ለማሳየት ያገለግላሉ። በተዘዋዋሪ መንገድ እምነትን፥ ፍርሃትን፥ ወይም ውድቀትን ሊያብራሩ ቢችሉም፥ ቀዳሚው አገልግሎታቸው ግን ይኼ አይደለም። ነገር ግን የወጣቱ ሀብታም (ማር. 10፡17–22 እና ትይዩ ምንባቦች) ወይም ከክርስቶስ በስተቀኝ ለመቀመጥ የቀረበ ጥያቄ (ማር. 10፡35–45 እና ትይዩ ምንባቦች) ዓይነት ታሪኮች ትምህርት በሚሰጥበት ጊዜ ለማብራሪያነት የተጠቀሱ ናቸው። ስለሆነም እነዚህን ትረካዎች በተመሳሳይ መንገድ መጠቀሙ ተገቢ አሁንዚያዊ ተግባር ይመስለናል።

በመሆኑም የወጣቱ ሀብታም ሰውዬ ታሪክ የሚያስረዳው የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት እርሱን ለመከተል ንብረታቸውን ሁሉ መሸጥ እንዳለባቸው አይደለም። ይህ እውነት እንዳልሆነ የሚያሳዩ ምሳሌዎች በወንጌላት ውስጥ አሉ (ሉቃስ 5፡27–30፤ 8፡3፤ ማር. 14፡3–9 አንብብ)። ከዚህ ይልቅ ታሪኩ የሚያስተምረው ሀብታሞች ቅድሚያ ትኩረታቸውን በሀብት ላይ ስለሚያደርጉና ሕይወታቸውንም በገንዘባቸው አማካኝነት አስተማማኝ ቦታ ለማድረስ ስለሚፈልጉ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት እንደሚከብዳቸው ነው። ነገር ግን ለሀብታሞች እንኳ የእግዚአብሔር ፍቅር ተአምራት ሊሠራ እንደሚችል ክርስቶስ አስረድቷል። ለዚህ ዓይነቱ ተአምር የዘኬዎስ ታሪክ ተጠቃሽ ሊሆን ይችላል (ሉቃስ 19፡1–10)።

እንደዚህ ካሉት ትረካዎች የምናገኘው ትምህርት ራሱ በወንጌሉ የተላለፈ መሆኑን ለማረጋገጥ የጥሩ ሐቲትን ጠቀሜታ መመልከት ይቻላል።

### *የመጨረሻው በጣም አስፈላጊ መልእክት*

ይህ መልእክት ቀደም ሲል ከቀረበው የክርስቶስ ታሪካዊ ዓውድ ጋር የሚዛመድ ሲሆን፥ በዚህ ስፍራ የተካተተው ለአፈታት ጥበብ ጥያቄ ወሳኝ በመሆኑ ነው። መልእክቱም ይህ ነው፤ *በክርስቶስ አገልግሎት ውስጥ የእግዚአብሔር መንግሥት ጽንሰ ሐሳብ ምን እንደሆነ ሳትገነዘብ ወንጌላትን በአግባቡ እተረጉማለሁ ብለህ አታስብ።*

ይህንን በተመለከተ የስቴይንን “Method and Message” ብትመለከት አጭር ሆኖ በጥሩ ሁኔታ የቀረበ መግቢያ ታገኛለህ። እዚህ ላይ ይህ እንዴት በሥነ አፈታት ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ከሚያሳይ መልእክት ጋር አጭር አሳብ እናቀርባለን።

በመጀመሪያ ደረጃ፥ የጠቅላላው አዲስ ኪዳን መሠረታዊ የሥነ መለኮት መዋቅር ሥነ ፍጻሜያዊ (eschatological) መሆኑን መገንዘብ ይኖርብሃል። ሥነፍጻሜ እግዚአብሔር ይህንን ዘመን ወደ ፍጻሜ የሚያመጣበት ጊዜ ነው። በክርስቶስ ዘመን የነበሩት አይሁዶች በአብዛኛው ሥነ ፍጻሜያዊ አስተሳሰብ ነበራቸው። ይህም ማለት እግዚአብሔር ወደ ታሪክ ምዕራፍ በመዝለቅ ይህንን ዘመን ከፍጻሜ በሚያደርስበትና መጭውን ዘመን ተግባራዊ በሚያደርግበት የጊዜ ቋፍ ላይ እንደሚገኙ ያስቡ ነበር። የሚጠብቁትን የመጨረሻ ዘመን የሚገልጸው የግሪክ ቃል «ኤስካተን» ( ስቸህ ትሆን) ይባላል። ስለሆነም ኤስካቶሎጂካል አስተሳሰብ መያዝ ማለት የመጨረሻውን ዘመን መጠበቅ ማለት ነው።

## የአይሁዶች የፍጻሜ ተስፋ

ፍጻሜ

| ይህ ዘመን (የሰይጣን ጊዜ) | መጭው ዘመን (እግዚአብሔር የሚገዛበት ጊዜ) |
|---|---|
| ባሕርዩ፥ | ባሕርዩ፥ |
| ኃጢአት | የመንፈስ ቅዱስ መኖር |
| በሽታ | ጽድቅ |
| በአጋንንት መያዝ | ጤና |
| የክፉ ሰዎች ድል ነሺነት | ሰላም |

የቀድሞዎቹ ክርስቲያኖችም እንዲህ ዓይነት ሥነ ፍጻሜያዊ የሕይወት ግንዛቤ ነበራቸው። ለእነርሱ የክርስቶስ መምጣት፥ ሞትና ትንሣኤ፥ ብሎም መንፈስ ቅዱስን ማደሉ ከፍጻሜ ዘመን ከሚጠብቋቸው ነገሮች ጋር የሚዛመድ ነበር። የተፈጸመውም እንደዚህ ነው።

የፍጻሜው ዘመን መምጣት ማለት አዲስ ጅማሬ ማለትም ነበር። ይህም የእግዚአብሔር አዲስ ዘመን፥ መሢሐዊ ዘመን የተጀመረበት ነው። አዲሱ ዘመን የእግዚአብሔር መንግሥት ሲባል፥ ፍችውም

የእግዚአብሔር አገዛዝ ዘመን ማለት ነው። ይህ አዲሱ ዘመን የጽድቅ (ለምሳሌ፥ ኢሳ. 11:4-5) እና ሰዎች በሰላም የሚኖሩበት ነበር (ለምሳሌ፥ ኢሳ. 2:2-4)። ይህ ኤርምያስ የተነበየለት አዲሱ ቃል ኪዳን ተግባራዊ የሚሆንበት (ኤር. 31:31-34፤ 32:38-40) የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ጊዜ ነበር (ኢዩ. 2:28-30)። ኃጢአትና በሽታ የሚወገዱበት ጊዜ ነበር (ለምሳሌ፥ ዘካ. 13:1፤ ኢሳ. 53:5)። ቁሳዊው ፍጥረት ሳይቀር የዚህን አዲስ ዘመን አስደሳች ውጤቶች ይገነዘባል (ለምሳሌ፥ ኢሳ. 11:6-9)።

ስለሆነም መጥምቁ ዮሐንስ ፍጻሜው እንደተቃረበ በመግለጽ የእግዚአብሔርን መሢሕ ሲያጠምቀው ሰዎች ስለ ፍጻሜ የነበራቸው አስተሳሰበ ተጋጋለ። አዲሱን የመንፈስ ዘመን የሚያመጣው መሢሕ በመካከላቸው ነበርና (ሉቃስ 3:7-17)።

ክርስቶስ መጭው መንግሥት በአገልግሎቱ ተግባራዊ እንደተደረገ አወጀ (ለምሳሌ፥ ማር. 1:14-15፤ ሉቃስ 17:20-21)። አጋንንትን በማውጣት፥ ተአምራትን በመሥራት፥ ኅብረተሰቡ ያገለላቸውንና ኃጢአተኞችን በማቀፍ የፍጻሜን መጀመሪያ ደወል አቃጨለ (ለምሳሌ፥ ሉቃስ 11:20፤ ማቴ. 11:2-6፤ ሉቃስ 14:21፤ 15:1-2)። በእርግጥም የሚመጣው መሢሕ እርሱ እንደሆነ ለማረጋገጥ ሰዎች በትኩረት ይከታተሉት ጀመር። መሢሓዊውን ዘመን ከክብሩ ሁሉ ጋር ያመጣው ይሆን? ይሁንና፥ ወዲያውኑ በስቅለት ሲሞት ብርሃናት ሁሉ ጨለሙ።

ይህ ግን አልሆነም! ታሪኩ ግሩም የከበረ ተከታይ ክፍል ነበረው። በሦስተኛው ቀን ከሞት ተነሥቶ ከተከታዮቹ ለብዙዎች ታየ። አሁን አለጥርጥር የእስራኤልን መንግሥት እንደገና ይመሠርታል (የሐዋ. 1:6)። ከዚህ ይልቅ ግን ወደ አባቱ ተመልሶ በመሄድ ተስፋ የተገባለትን መንፈስ ቅዱስ አወረደ። የቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያንና የእኛም ችግር የሚመነጨው ከዚህ ነው። ክርስቶስ ከእርሱ ጋር ይመጣል የተባለው የእግዚአብሔር መንግሥት እንደ መጣ ገልጾ ነበር። ከተአምራትና ምልክቶች ጋር የመንፈስ ቅዱስ በሙላትና በኃይል መምጣትና የአዲሱ ቃል ኪዳን መገለጽ አዲሱ ዘመን እንደ ደረሰ የሚያመለክቱ ምልክቶች ነበሩ። ይሁንና፥ የዚህ ዘመን ፍጻሜ ገና የደረሰ አይመስልም። እንግዲህ፥ ይህንን እንዴት መረዳት ነበረባቸው?

በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 3 ከቀረበው የጴጥሮስ ስብከት መረዳት እንደሚቻለው፥ የቀድሞዎቹ ክርስቲያኖች ክርስቶስ የፍጻሜውን «የመጨረሻ» ሳይሆን የፍጻሜውን «መጀመሪያ» ለማስተዋወቅ እንደ መጣ ተገንዝበዋል። ስለሆነም በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ፥ ብሎም በመንፈስ ቅዱስ መውረድ የወደፊት በረከቶችና ጥቅሞች ከወዲሁ

ተግባራዊ እንደሆኑ ለመረዳት ችለዋል። እንግዲህ፥ በአንድ በኩል ፍጻሜው ደርሷል ማለት ነው። በሌላ በኩል ግን ፍጻሜው ሙሉ በሙሉ አልተከሰተም። በመሆኑም ቀድሞውኑ መጥቷል፤ ዳሩ ግን ገና ነው እንላለን።

የቀድሞዎቹ አማኞች እውነተኛ የፍጻሜ ሕዝብ ለመሆን ችለው ነበር። የኖሩትም በጊዜያት መካከል፥ ማለትም በፍጻሜው መጀመሪያና በፍጻሜው መግቢያ መካከል ነበር። በቅዱስ ቁርባን ፊት እስኪመጣ ድረስ የጌታን ሞት እየተናገሩ (1ኛ ቆሮ. 11፡26) ፍጻሜያዊ ህልውናቸውን አከብረዋል። ቀድሞውኑ የእግዚአብሔርን ነፃና ሙሉ ይቅርታ አግኝተዋል፤ ይሁንና ገና ፍጹማን አልሆኑም (ፊልጵ. 3፡7–14)። ቀድሞውኑ በሞት ላይ ድልን ተቀዳጅተዋል (1ኛ ቆሮ. 3፡22)፤ ይሁንና፥ ገና ሰይጣን ጥቃት ሊሰነዝር በሚችልበት ዓለም ውስጥ ይኖራሉ (ለምሳሌ፥ ኤፌ. 6፡10–17)። ቀድሞውኑ ጻድቀው ከኩነኔ ነፃ ሆነዋል (ሮሜ 8፡1)፤ ይሁንና፥ ገና ወደፊት ፍርድ ይኖራል (2ኛ ቆሮ. 5፡10)። እነዚህ የእግዚአብሔር የወደፊት ሕዝቦች ሲሆኑ፥ ሕይወታቸው በወደፊት ላይ የተመሠረተ ነበር። ጥቅሞቹን ያውቁታል፤ ከእሴቶቹ አንጻር ሕይወታቸውን ይመራሉ። በአሁኑ ዘመን ውስጥ በእነዚህ ጥቅሞችና እሴቶች ላይ ተመሥርተው መኖር ነበረባቸው። እኛም እንደዚሁ። ስለሆነም አዲስ ኪዳንን ለመረዳት የሚያስችለው ወሳኝ ሥነ መለኮታዊ መዋቅር ይህንን ይመስላል።

## የአዲስ ኪዳን የፍጻሜ እይታ

### ፍጻሜ

ይህ ዘመን | ተጀመረ (እያለፈ)

ተግባራዊ ሆነ

መጭው ዘመን | (ፍጹም የማያልፍ)

**መስቀሉና ትንሣኤው**

*ቀድሞውኑ*
ጽድቅ
ሰላም
ጤንነት
መንፈስ ቅዱስ

**ዳግም ምጽአት**

*ገና*
ሙሉ ጽድቅ
ሙሉ ሰላም
የሞት ወይም የበሽታ አለመኖር
ፍጹም ምልዓት

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ለሚገኙ ብዙ ምንባቦችና በተለይም ለክርስቶስ ትምህርት ሥነ አፈታታዊ ቁልፉ በዚህ ዓይነት «ውጥረት» ውስጥ መገኘት ነው። ለዚህም ምክንያቱ እግዚአብሔር የሚገዛበት መንግሥት በክርስቶስ መምጣት ሲመረቅ እኛም ለመንግሥቱ ሕይወት መጠራታችን ነው። ይህም ማለት በእግዚአብሔር ጌትነት ሥር በነፃ ተቀባይነትና ይቅርታን ማግኘት፥ ለአዲሱ ዘመን ሥነ ምግባር ራስን አሳልፎ መስጠት፥ ብሎም በራሳችን ሕይወትና በዚህ ዓለም በአሁኑ ዘመን ተግባራዊ ሲሆኑ መመልከት ማለት ነው።

# ምሳሌዎች፡ መልእክቱን አገኘህ?

በምዕራፍ 7 ክርስቶስ በወንጌላት ውስጥ ስላቀረባቸው ትምህርቶች የተገለጸው አሳብ ሁሉ ለምሳሌዎች እንደሚሠራ በቅድሚያ ልትገነዘብ ይገባል። እንደዚያ ከሆነ፥ ይህን በሚመስል መጽሐፍ ውስጥ ለምሳሌዎች ራሱን የቻለ ምዕራፍ የተሰጠው ለምንድን ነው? እነዚህ ክርስቶስ የተናገራቸው ቀላልና ቀጥተኛ ትናንሽ ታሪኮች በአንባቢው ወይም በተርጓሚው ላይ እንዴት ችግሮችን ሊያስከትሉ ይችላሉ? የርኅሩኁን ሳምራዊ ወይም የጠፋውን ልጅ ታሪክ መልእክት የማይረዳ ሰው የግንዛቤ ችግር ያለበት ሊመስለን ይችላል። እነዚህን ታሪኮች ማንበቡ ልብን ይወጋል፤ አሊያም ያጽናናል።

ይሁንና፥ ከግልጽነታቸውና ማራኪነታቸው ባሻገር ከዮሐንስ ራእይ ቀጥሎ ምሳሌዎችን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተሳሳተ መንገድ መተርጎም የተለመደ መሆኑን በመገንዘብ ራሱን የቻለ ምዕራፍ አዘጋጅተናል።

## ምሳሌዎች በታሪክ

ምሳሌዎች ለረዥም ዘመናት በተሳሳተ መንገድ ሲተረጎሙ የቆዩበት ምክንያት ክርስቶስ ራሱ የተናገረው ሊሆን ይችላል (ማር. 4፡10–12፤ ትይዩ ምንባቦችን ከማቴ. 13፡10–13፤ ሉቃስ 8፡9–10 አንብብ)። በምሳሌ የማስተማሩ ዓላማ ምን እንደሆነ በተጠየቀ ጊዜ፥ ክርስቶስ በውስጥ ላሉት ምሥጢራዊ መልእክቶችን እንደያዙና በውጭ ያሉትን ሰዎች ልብ እንደሚያደነድኑ የሚያመለክት ምላሽ የሰጠ ይመስላል። ከዚያ በኋላ የዘሪውን ምሳሌ ከፊል መንፈሳዊ ፍች ፍለጋ ( ልል ግዡር ች ል) በታከለበት መንገድ መተርጎሙ፥ ልብን ለማደንደኑ ቲዎሪና ፍጻሜ ለሌለው መንፈሳዊ ፍች የሚፈለግበት የአተረጓጎም መንገድ ፈቃድ መስጠቱን የሚያመለክት ይመስላል። ምሳሌዎቹ «እውነተኛ ትርጉሞቻቸው» ማለትም «ምሥጢሮቻቸው» ለተሰወሩባቸው የውጭ ሰዎች ቀላል ይመስላሉ። እነዚህ የቤተ ክርስቲያን ንብረቶች በመሆናቸው መንፈሳዊ ፍችን የሚሰጡ ናቸው።

ስለሆነም፥ እንደ አገስቲን ያለ ታላቅና ብሩህ አእምሮ የነበረው ክርስቲያን ለርኅሩኁ ሳምራዊ ታሪክ የሚከተለውን ትርጉም ሰጥቶታል።

*አንድ ሰው ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ ወረደ = አዳም*

*ኢየሩሳሌም* = አዳም የወደቀባት ሰማያዊቷ የሰላም ከተማ

*ኢያሪኮ* = ጨረቃ፥ የአዳምን ዘላለማዊነት ታመለክታለች

*ሌቦች* = ዲያብሎስና መላእክቶቹ

*ገፈፉት* = ዘላለማዊነቱን ወሰዱበት

*ደበደቡት* = ኃጢአት እንዲሠራ በማግባባት

*በሞትና በሕይወት መካከል ተዉት* = ሰውዬው በሕይወት ቢኖርም መንፈሳዊ ሞትን ሞቶ ነበር። እናም በሞትና በሕይወት መካከል ኖረ።

*ካህኑና ሌዋዊው* = የብሉይ ኪዳን ክህነትና አገልግሎት

*ሰማርያዊው* = ጠባቂ ማለት ነው፤ ስለዚህ ሰማርያዊው ክርስቶስን ይወክላል።

*ቁስሎቹን አሰረለት* = የኃጢአትን ክልከላ ማሰር

*ዘይት* = የመልካም ተስፋ መጽናናት

ወይን = በጥሩ መንፈስ እንድንሠራ የተሰጠ ምክር

*አውሬ /አህያ/* = የክርስቶስ ትስብእት ሥጋ

*ማረፊያ* = ቤተ ክርስቲያን

*ማግሥት* = ከትንሣኤ በኋላ

*ሁለት ዲናሮች* = የዚህና የመጭው ሕይወት የተስፋ ቃል

*ጠባቂው* = ጳውሎስ

ሁሉ መልካምና ደስ የሚያሰኝ ሊሆን ቢችልም፥ ይህ ክርስቶስ ሊያስተላልፍ የፈለገው መልእክት እንዳልሆነ መገንዘብ ይቻላል። ዓውዱ ራሱ የሚያመለክተው ሰው ከሰው ጋር ያለውን እንጂ (ባልንጀራዬ ማን ነው?) ሰው ከአምላክ ጋር ያለውን ግንኙነት አይደለም። ስለሆነም ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንና ጳውሎስን እንደዚህ ስውር በሆነ መንገድ ተንብዮአል ለማለት የሚያስችል ምክንያት የለንም።

እንዲሁም አብዛኞቹ ምሳሌዎች ለውስጥ ሰዎች መታቀዳቸውን ማወቅ አይቻልም። ቢያንስ በሦስት ስፍራዎች ክርስቶስ ምሳሌዎችን

እንዲረዱቸው በማሰብ ለብዙ ሰዎች እንደተናገረ ገልጾአል (15፡3፤ 18፡9፤ 19፡11)። በተጨማሪም ክርስቶስ የርኅሩኁን ሳምራዊ ታሪክ የነበረው የሕግ አዋቂም ምሳሌውን ተረድቷል (ሉቃስ 10፡25-37)። ጻፎችና ፈሪሳውያንም ክርስቶስ በማቴዎስ 21፡45 ስለ መክሊት የተናገረውን ምሳሌ ተረድተዋል።

አንዳንድ ጊዜ ምሳሌዎችን መረዳት የሚቸግረን ከሆነ፥ ለዚህ ምክንያቱ አንዳች የትርጉም ቁልፍ የሚያሻቸው መንፈሳዊ ፍችዎች መያዛቸው አይደለም። ይልቁንም ይህ ቀደም ሲል ስለ ወንጌላት በተነጋገርንበት ምዕራፍ ውስጥ ካቀረብነው አሳብ ጋር የተያያዘ ነው። ምሳሌዎችን ለመረዳት ከሚያስችሉት ቁልፎች አንዱ የመጀመሪያ አድማጮቻቸውን ማወቅ ነው። ቀደም ብለን እንደተመለከትነው፥ ብዙውን ጊዜ ወደ ወንጌላውያኑ የደረሱት ያለ ዓውድ ነበር።

እንግዲህ፥ ምሳሌዎች ለቤተ ክርስቲያን የተሰጡ መንፈሳዊ ምሥጢራት ካልሆኑ፥ ክርስቶስ በማርቆስ 4፡10-12 ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ምሥጢርና ከምሳሌዎች ጋር ስላለው ግንኙነት የተናገረው አሳብ ምንን የሚያመለክት ነው? ምናልባትም ለዚህ ፍንጭ የሚሰጠን የክርስቶስ የመጀመሪያ ቋንቋ የነበረው የአረማይክ የቃላት ጨዋታ ይሆናል። ምሳሌ ተብሎ የተተረጎመው የዕርዕ ቃል «ሜታል» (methal) ሲሆን፥ በአማርኛ «ምሳሌዎች» ለሚባሉት ብቻ ሳይሆን ለእንቆቅልሾችና ለዘይቤያዊ አነጋገሮች ሁሉ የሚያገለግል ነበር። ምናልባትም ቁጥር 11 በውጭ ያሉት የክርስቶስን አገልግሎት ትርጉም (የመንግሥተ ሰማይ ምሥጢር) እንደማያገኙ የሚያስረዳ ይሆናል። ለእነርሱ ልክ እንደ ሜታል፥ ማለትም እንቆቅልሽ ይሆናል። ስለሆነም በምሳሌዎች መናገሩ ለእነርሱ አገልግሎቱ ሁሉ እንቆቅልሽ የመሆኑ አካል ነበር። አዩ፤ ነገር ግን ሊያስተውሉ አልቻሉም። ሰምተው ምሳሌዎቹን መረዳት ችለው ነበር። ነገር ግን በአጠቃላይ የክርስቶስን አገልግሎት ለማድነቅ አልቻሉም።

ስለሆነም፥ የምሳሌዎች ሐቲታችን እስካሁን ለሌሎች ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጾች የወሰድናቸውን እርምጃዎች የሚያካትት መሆን አለበት። ክርስቶስ ድብቅ ለመሆን እየሞከረ አልነበረም። ሙሉ በሙሉ ሰዎች እንዲረዱት ይፈልግ ነበር። ተግባራችን በመጀመሪያ ደረጃ እነርሱ የሰሙትን ቃል ለመስማት መሞከር ነው። ነገር ግን ያንን በብቃት ከመወጣታችን በፊት፥ «ምሳሌ ምንድን ነው?» ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ማግኘት ይኖርብናል።

# የምሳሌዎች ባሕርይ

## *የተለያዩ የምሳሌ ዓይነቶች*

*መጀመሪያ ሊጤን የሚገባው «ምሳሌዎች» የምንላቸው ሁሉ አንድ ዓይነት አለመሆናቸውን ነው።* ለምሳሌ፥ የርኅሩኅ ሳምራዊ (እውነተኛ ታሪክ) እና የምግብ እርሾ (ተነጻጻሪ ዘይቤ) አንድ ዓይነት አይደሉም። ሁለቱም ደግሞ «እናንተ የምድር ጨው ናችሁ» (ተለዋጭ ዘይቤ) ወይም «ከእሾህ ወይን፥ ከኩርንችትስ በለስ ይለቀማልን?» (ምሳሌያዊ አነጋገር) ይለያሉ። ነገር ግን ስለ ምሳሌዎች በምንነጋገርበት ጊዜ እነዚህን ሁሉ ልናገኛቸው እንችላለን።

ርኅሩኅ ሳምራዊ *ለእውነተኛ ምሳሌ* በአብነት ሊጠቀስ ይችላል። ይህ ጅማሬና ፍጻሜ *ያለው ታሪክ* ነው። «ሤራ» *መሳይ* ነገር አለው። የጠፋው በግ፥ የጠፋው ልጅ፥ *ታላቁ* እራት፥ የወይን ሠራተኞች፥ *ሀብታሙ* ሰውዬና አልዓዛር፥ እንዲሁም የአሥሩ ቆነጃጅት *ታሪኮች* ከዚህ ጋር ተመሳሳይነት አላቸው።

በሌላ በኩል የእርሾው ምሳሌ ወደ *ተነጻጻሪ ዘይቤነት* ያደላል። ስለ እርሾ፥ ዘሪ ወይም የሰናፍጭ ዘር የተነገረው አሳብ ሁልጊዜም ስለ እርሾ፥ ዘሪ ወይም የሰናፍጭ ዘሮች እውነት ነው። እንዲህ ዓይነት ምሳሌዎች ክርስቶስ መልእክቱን ለማስተላለፍ ከዕለታዊ የሕይወት ገጠመኞች የወሰዳቸው ናቸው።

«እናንተ የምድር ጨው ናችሁ» የሚሉ ዓይነት ምሳሌዎች ከእነዚህ ከሁለቱም ይለያሉ። እነዚህ አንዳንድ ጊዜ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ናቸው ቢባሉም፥ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን *ተነጻጻሪ* ወይም *ተለዋጭ ዘይቤዎች* ናቸው።

አንዳንድ ጊዜ በተለይም የክፉዎቹ ገበሬዎች ምሳሌ (ማር. 12፡1–11፤ ማቴ. 21፡33–34፤ ሉቃስ 20፡9–18) ስውር መንፈሳዊ ትምህርት የሚያስተላልፍ ይመስላል። በዚህም ጊዜ በታሪኩ ውስጥ የሚገኙ ዝርዝሮች ሌሎች ነገሮችን እንዲወክሉ ይደረጋል። (ይህ ልክ አግስቲን ስለ ርኅሩኅ ሳምራዊ ባቀረበው የተሳሳተ አተረጓጎም ውስጥ የተመለከተው ዓይነት ነው)። ነገር ግን ምንም እንኳ አንዳንድ ጊዜ ለእኛ ስውር መልእክት–አዘል ገጽታዎች ያኋቸው ቢመስሉም፥ *ምሳሌዎች ስውር መንፈሳዊ ፍች* የተገለጠባቸው አይደሉም።

ምሳሌዎች ሁሉ አንድ ዓይነት ባለመሆናቸው ለሁሉም የሚሠራ ደንብ ማውጣት አይቻልም። በዚህ ስፍራ የምናቀርበው አሳብ ለምሳሌዎች የሚሠራ ሲሆን፥ አብዛኛው ለሌሎችም *ሥነ* ጽሑፋዊ ቅርጾችም የሚያገለግል ይሆናል።

## ምሳሌዎች እንዴት እንደሚያገለግሉ

የምሳሌዎችን ምንነት የሚያስረዳው ከሁሉም የተሻለ ፍንጭ የሚገኘው ከአገልግሎታቸው ነው። «ከኩርንችት በለስ ይለቀማልን?» ከሚሉ ዓይነት ምሳሌያዊ አነጋገሮች በተቃራኒ፥ በታሪክነት የቀረቡት ምሳሌዎች የክርስቶስን ትምህርት በሥዕላዊ አገላለጽ ለማብራራት አያገለግሉም። ወይም ደግሞ ወደ እውነት የሚያደርሱ መሣሪያዎች ሆነው እንዲያገለግሉ አይደለም የተነገሩት – ምንም እንኳ ይህንኑ በማድረግ ላይ ቢገኙም። በታሪክነት የቀረቡ ምሳሌዎች የተነገሩት ከአድማጩ ምላሽ ለማግኘት ነው። ማርሻል ምክሉሃን እንዳሉት፥ ምሳሌው ራሱ መልእክት ነው። ምሳሌው የተነገረው የአድማጮችን ትኩረት ለመሳብ፥ ተግባራቸውን ለማሳየትና ወይም በሆነ መንገድ ለክርስቶስና ለአገልግሎቱ ምላሽ እንዲሰጡ ለማድረግ ነው።

አተረጓጎሙን ከአጣብቂኝ ውስጥ የሚከተውም ይኸው የምሳሌዎች ምላሽ የመፈለግ ባሕርይ ነው። ለዚህም ምክንያቱ በአንዳንድ መንገዶች ምሳሌዎችን መተርጎም ማለት የመጀመሪያ ምንነቱን ማጥፋት ስለሚሆን ነው። ይህ ልክ ቀልድን እንደ መተርጎም ነው። የቀልድ ዋናው ቁም ነገር አድማጩ ለሚነገረው ቀልድ ቅርበት ያለው መሆኑ ነው። ቀልዱ ለሰሚው ትርጉም የሚሰጠው ትኩረታቸውን ስለሚስብ ነው። ነገር ግን ትኩረታቸውን የሚስበው በቀልዱ ውስጥ ያሉትን የማጣቀሻ አሳቦች የተረዱ እንደሆነ ብቻ ነው። የማጣቀሻ ነጥቦችን በመተንተን ቀልዱን መተርጎም ካለብህ፥ የአድማጩን ትኩረት ስለማይስብ ብዙውን ጊዜ ያን ያህል ሳቅ አይጭርም። ቀልድ በሚተረጎምበት ጊዜ በጥሩ ሁኔታ መረዳት ይቻላል። አስቂኝነቱም ሊኖር ይችላል። (ቢያንስ ልትስቅ የሚገባህን ነገር ታውቀዋለህ።) የሚያሳድረው ተጽዕኖ ግን አንድ ዓይነት አይሆንም። ይህም ከቀድሞው ጋር አንድ ዓይነት አገልግሎት እንዳይኖረው ያደርጋል።

የምሳሌዎችም ሁኔታ እንደዚሁ ነው። ምሳሌዎቹ በሚነገሩበት ጊዜ አብዛኞቹ አድማጮች አሳቡን እንዲያገኙ ወይም ትኩረታቸውን እንዲሰቡ ካደረጓቸው የማጣቀሻ ነጥቦች (የታሪኩ ባለቤቶች) ጋር ቅርበት እንደነበራቸው እንገምታለን። ለእኛ ግን ምሳሌዎቹ ተጽፈው ተላልፈዋል። እኛ የማጣቀሻ ነጥቦቹን ልንረዳ ወይም ላንረዳ ስለምንችል፥ ምሳሌዎቹ ለእኛ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ሙሉ በሙሉ ከመጀመሪያዎቹ አድማጮች ጋር አንድ ዓይነት ሊሆን አይችልም። ምሳሌዎቹን በመተርጎም ግን ምን እንደያዙ ወይም እዚያ ብንሆን ኖሮ ምን ትኩረታችንን ይስብ እንደነበር ልንረዳ እንችላለን። በሐቲታችንም ማድረግ ያለብን ይህንኑ ነው። ሥነ አፈታታዊ

ተግባራችን ግን ከዚያ ያልፋል፤ በራሳችን ዘመንና ሁኔታ ውስጥ የምሳሌዎቹን «ዓቅም» እንዴት እንደገና ልናገኝ እንችላለን?

## የምሳሌዎች ሐቲት

### *የማጣቀሻ ነጥቦችን (የታሪኩን ባለቤቶች) ማግኘት*

እስኪ ወደ ቀልድ ምሳሌያችን እንመለስ። የአድማጮችን ትኩረት በመሳብ ሳቅ የሚጭሩ ሁለቱ ነገሮች የክርስቶስን ምሳሌዎች የሚሰሙ ሰዎችን ትኩረት የሚስቡ ተመሳሳይ ነገሮች ናቸው። እነዚህም አድማጮቹ የማጣቀሻ ነጥቦችን ማወቃቸውና በታሪኩ ውስጥ ሳይጠበቅ የሚከሰቱ ሁኔታዎች ናቸው። ለማንዛቤ የሚረዱ ቁልፎች ደግሞ ታሪኩ በሚነገርበት ጊዜ አድማጮቹ ራሳቸውን የሚያመሳስሉባቸው የተለያዩ ክፍሎች (የማጣቀሻ ነጥቦች) ናቸው። በአንድ ቀልድ ውስጥ አንድ ሰው እነዚህን ነገሮች ካላገኘ ያልተጠበቀ ነገር የሚከሰትበት ሁኔታ አይኖርም። ይህንን ማድረጉ የማጣቀሻ ነጥቦች ተግባር ነውና። በተመሳሳይ ሁኔታ በምሳሌ ውስጥ አንድ ሰው እነዚህን ነገሮች ካላገኘ ክርስቶስ የተናገረው አሳብ ጉልበትና መልእክት ሊጨበጥለት አይችልም።

«የማጣቀሻ ነጥብ» የምንለው ነገር ከሙሉ የመጀመሪያ ዓውዱ ጋር በሰፈረው የክርስቶስ ምሳሌ ሊብራራ ይችላል (ሉቃስ 7፡40-42)። በዚህ ዓውድ ውስጥ ስምዖን የተባለ ፈሪሳዊ ክርስቶስን እራት ጋብዞት ነበር። ነገር ግን ግብዣው ለዝነኛው ራባይ ክብር የተደረገ አይመስልም። ተራ የመስተንግዶ ነገሮች እንኳ አለመሟላታቸው ፈሪሳዊው ክርስቶስን ለማዋረድ እንዳቀደ የሚያሳይ ነበር። በዚህ ጊዜ በግብዣው ላይ ተገኝታ የክርስቶስን እግሮች በእንባዋ ስታጥብና በፀጉሯ ስታብስ የነበረች አንዲት የከተማ ጋለሞታ የፈሪሳዊውን ጥርጣሬ ከማጠናከር የተሻለ ሚና አልነበራትም። ክርስቶስ ነቢይ ቢሆን ኖሮ እንዲህ ዓይነቱን በሕዝብ ፊት የሚከሰት አሳፋሪ ነገር ሳያወግዝ አይቀርም ነበር ሲል አሰበ።

ክርስቶስ የፈሪሳዊውን አሳብ በመገንዘብ፥ አንድ ቀላል ታሪክ ነገረው። ሁለት ሰዎች ከአንድ ሀብታም ገንዘብ ተበድረው ነበር። አንደኛው አምስት መቶ ዲናር (አንድ ዲናር በዚያን ጊዜ የአንድ ቀን ምንዳ ነበር)፥ ሁለተኛው ሃምሳ ዲናር ተበድረው ነበር። የሚከፍሉት ስላጡ ዕዳውን ሰረዘላቸው። ነጥቡ፣ ከሁለቱ ለአበዳሪው የበለጠ የፍቅር ምላሽ የሚሰጠው የትኛው ይመስልሃል? የሚል ነበር።

ምንም እንኳ ክርስቶስ በሙሉ ኃይሉ ነገሩን ግልጽ ለማድረግ ቢሞክርም፥ ይህ ታሪክ ትርጉም የሚሻ አልነበረም። በዚህ ምሳሌ

ውስጥ ሦስት የማጣቀሻ ነጥቦች አሉ። እነዚህም ገንዘብ አበዳሪውና ሁለቱ ተበዳሪዎች ናቸው። ዝምድናውም ቅርብ ነው። እግዚአብሔር እንደ አበዳሪው ነው። ጋለሞታይቱና ስምዖን እንደ ሁለቱ ተበዳሪዎች ናቸው። ምሳሌው የስምዖንን ምላሽ የሚሻ የፍርድ ቃል ነው። ስምዖን የዚህን ምሳሌ መልእክት ያጣል ማለት አይቻልም። ክርስቶስ መልእክቱን በፈጸመ ጊዜ ስምዖን የሚሰጠው ምላሽ አልነበረውም። ይህ እንግዲህ፥ የምሳሌውን ጥንካሬ የሚያሳይ ነው።

በተጨማሪም፥ ሴቲቱም ምሳሌውን እንደሰማች ማጤን አለብን። እርሷም ከታሪኩ ጋር ራሷን ታዛምዳለች። እርሷ የሰማችው ግን ፍርድን ሳይሆን፥ በክርስቶስና በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዳገኘች ነው።

አሁንም ልብ በል፤ ይህ ስውር መንፈሳዊ መልእክት የሚፈለግበት «አለጎሪ» ሳይሆን ምሳሌ ነው። ስውር መንፈሳዊ ምሥጢር የሚፈለግበት ታሪክ እያንዳንዳቸው የታሪኩ አላባውያን ፍጹም የተለየ ፍች የሚያገኙበት ነው። እንዲህ ዓይነቱ ታሪክ ለአምስት መቶ ዲናር፥ ለሃምሳ ዲናርና ለሌሎችም ዝርዝር ጉዳዮች ፍች ይሰጣል። በተጨማሪም (ይህ በተለይ ጠቃሚ ነው)፥ ስውር ምሥጢር በሚፈለግባቸው እውነተኛ አለጎሪዎች ጊዜ እንደሚሆነው የምሳሌዎች መልእክት/ነጥብ ያለው በማጣቀሻ ነጥቦች ውስጥ አይደለም። የማጣቀሻ ነጥቦች ታሪኩ በሚነገርበት ጊዜ አድማጩን ወደ ታሪኩ የሚስቡና ታሪኩ በሚቀጥልበት ጊዜ በሆነ መንገድ ራሱን እንዲያዛምድ የሚያደርጉ ክፍሎች ናቸው። የታሪኩ መልእክት የሚገኘው በተፈለገው ምላሽ ውስጥ ነው። በዚህ ምሳሌ ውስጥ የታሪኩ መልእክት ለስምዖን ወይም ለጓደኞቹ ፍርድ፥ ወይም ለሴቲቱ የተቀባይነት መግለጫ ነው።

### *አድማጭን መለየት*

የአንድ ምሳሌ ፍች መጀመሪያ ከተደመጠበት ሁኔታ ጋር ስለሚያያዝ፥ ከላይ በቀረበው ማብራሪያ ውስጥ አድማጭን መለየት ጠቃሚ መሆኑን አመልክተናል። ለብዙዎቹ ምሳሌዎች አድማጮቹ በወንጌላት ውስጥ ተጠቅሰዋል። በእንዲህ ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ የአተረጓጎም ተግባር ሦስት ነገሮችን ያካትታል። እነዚህም፥ (1) ምሳሌውን ደጋግሞ መስማት፥ (2) ክርስቶስ የፈለጋቸውንና የመጀመሪያዎቹ አድማጮች ያገኙዋቸውን የማጣቀሻ ነጥቦች መለየትና (3) የመጀመሪያዎቹ አድማጮች ራሳቸውን ከታሪኩ ጋር እንዴት እንዳዛመዱና ምን እንደ ሰሙ ለማወቅ መሞከር ናቸው።

ይህንን እስኪ በሁለት የታወቁ ምሳሌዎች እናብራራው። እነዚህም ርኅሩኅ ሳምራዊ (ሉቃስ 10፡25–37) እና የጠፋው ልጅ (ሉቃስ 15፡11–32) ናቸው። ሉቃስ እንደሚገልጽልን፥ የደጉ ሳምራዊ ታሪክ የተነገረው ራሱን ሊያጸድቅ ፈልጎ፥ «ባልንጀራዬ ማን ነው?» ሲል ለጠየቀው የሕግ አዋቂ ነው። ምሳሌውን ደጋግመህ በምታነብበት ጊዜ የቀረበውን ጥያቄ በቀጥታ እንደማይመልስ ትገነዘባለህ። ነገር ግን ዘወር ባለ መንገድ የሕግ ባለሙያውን ራስን የማጽደቅ አመለካከት ያጋልጣል። ባልንጀራን እንደ ራስ ስለ መውደድ ሕጉ ምን እንደሚል ያውቅ ነበርና «ባልንጀራ» የሚለውን ቃል የራሱን ጽድቅ በሚያመለክት መልኩ ሊተረጉም ተዘጋጅቶ ነበር።

ምንም እንኳ ሌሎች ዝርዝሮች ምሳሌውን ለማነጽ ቢያገለግሉም፥ በዚህ ታሪክ ውስጥ የምናገኛቸው የማጣቀሻ ነጥቦች ሁለት ብቻ ናቸው፤ የተጎዳው ሰውዬና ሳምራዊው። እዚህ ላይ በተለይ ሁለት ነገሮች ሊጤኑ ይገባል። (1) የተጎዳውን ሰውዬ አይተው ዘለል ብለው ያለፉት ሁለት ሰዎች የክህነት አገልግሎቱ አካላት ነበሩ። ይህም ከፍተኛ የሕግ እውቀት በነበራቸው ራባዮችና ፈሪሳውያን ላይ የነበረው ሃይማኖታዊ ሥርዓት ነበር። (2) ምጽዋትን መስጠት ለፈሪሳውያን ትልቅ ነገር ነበር። ባልንጀሮቻቸውን እንደ ራሳቸው የሚወዱት ይህንኑ በማድረግ ነበር።

አሁን እንግዲህ ሕግ አዋቂው በዚህ ምሳሌ እንዴት እንደሚጠመድ ተመልከት። ሰውዬው ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ በመሄድ ላይ ሳለ በወንበዴዎች እጅ ወደቀ። ይህ ተራ ክስተት ሊባል የሚችል ነው። ሁለት የክህነት አገልግሎት ተካፋዮች በዚያ ግድም ሲያልፉ መንገድ ሰብረው አለፉ። ታሪኩ የሚነገረው ከተጎዳው ሰውዬ አንጻር በመሆኑ፥ የሕግ አዋቂው ስፍራውን መያዝ ጀምሯል። «ከካህናት ማን ከዚህ የተሻለ ነገር ሊጠብቅ ኖሯል? ቀጣዩ ፈሪሳዊ ስለሆነ ሰውዬውን መርዳቱ አይቀርም» እያለ ማሰቡ አይቀርም። ይህ ግን አልሆነም። ሰውዬውን የረዳው ሳምራዊ ነበር። እርሱ የሰማውን ለመስማት ከፈለግህ ፈሪሳውያን ሳምራውያንን ምን ያህል ይጠሏቸው እንደነበር መገንዘብ ይኖርብሃል። በመጨረሻው ላይ እንኳ «ሳምራዊ» የሚለውን ቃል ለመጥራት አይፈልግም።

ክርስቶስ ለዚህ ሰውዬ ምን እንዳደረገ ታያለህ? ሁለተኛው ታላቅ ትእዛዝ ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ የሚል ነው። የሕግ አዋቂው በተወሰኑ የድርጊት ክልሎች ውስጥ ይህንን ሕግ እንዲፈጽም የሚያደርጉ ትናንሽ ሥርዓቶች ነበሩት። ክርስቶስ ያደረገው ነገር ቢኖር የልቡን ጥላቻና አድልዎ በማጋለጥ ለዚህ ትእዛዝ ተገዥ አለመሆኑን ማሳየት ነበር። ከዚያ ወዲያ «ባልንጀራ» በገደብ መተርጎሙ ያበቃል።

ፍቅር እንደሌለው የሚታየው የተጎዳውን ሰውዬ ባለመርዳቱ ሳይሆን ሳምራውያንን በመጥላቱ (እና ካህናትን በመናቁ) ነበር። ይህ ምሳሌ ጥያቄውን ከመመለስ ይልቅ እስከናካቴው ያጠፋዋል ማለቱ ይቀላል።

የጠፋው ልጅ ታሪክም እንደዚሁ ነው። የምሳሌው ዓውድ ክርስቶስ ትክክለኛ አይደሉም የተባሉትን ሰዎች በመቀበሉና ከእነርሱ ጋር በመብላቱ ምክንያት፥ ፈሪሳውያን ማጉተምተማቸው ነበር። በሉቃስ 15 ስለ ጠፉት ዕቃዎች የሚናገሩ ሦስት ምሳሌዎች ክርስቶስ የተግባራቱን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የተጠቀመባቸው ናቸው። በጠፋው ልጅ ታሪክ ውስጥ ሦስት የማጣቀሻ ነጥቦች ብቻ የሚገኙ ሲሆን፥ እነዚህም አባትና ሁለት ልጆቹ ናቸው። እዚህም አንድ ሰው የሚሰማው መልእክት የሚወሰነው ከተቀመጠበት አቅጣጫ ነው። ይህም ሆነ ያ ነጥቡ አንድ ዓይነት ነው፤ ይኸውም እግዚአብሔር የጠፉትን ኃጢአተኞች ይቅር ማለቱ ብቻ ሳይሆን በደስታ ይቀበላቸዋል የሚል ነው። ራሳቸውን እንደ ጻድቅ የሚቆጥሩ ሰዎች የጠፋውን ልጅና የአባቱን ደስታ ካልተጋሩ ጻድቃን አለመሆናቸውን ያረጋግጣሉ።

ከክርስቶስ ጋር የሚመገቡ ሰዎች ከጠፋው ልጅ ጋር ራሳቸውን እንደሚያዛምዱ ጥርጥር የለውም። ይህ እኛም ልናደርገው የሚገባን ነው። ይህ ግን በሁለተኛው ልጅ አመለካከት ላይ የሚንጸባረቅ ሲሆን፥ የምሳሌው እውነተኛ ጥንካሬ አይደለም። ይህ ልጅ ሁልጊዜም ከአባቱ ጋር የነበረ ሲሆን፥ ነገር ግን በራሱ ፈቃድ ወደ ውጭ ወጥቷል። አባቱ ለጠፋው ልጅ ካሳየው ፍቅር ጋር ደስ ሊሰኝ አልቻለም። አንድ ሰው እንደተናገረው፥ ወደ ቤት መጥቶ በታላቅ ወንድሙ እጅ ከመውደቅ የከፋ ነገር የለም።

በእነዚህና በሌሎችም ሁኔታዎች ውስጥ የሚያጋጥሙህ ያኔዚያዊ ችግሮች የሚመነጩት፥ አብዛኛውን ጊዜ በአንተና በክርስቶስ የመጀመሪያ አድማጮች መካከል ከሚገኘው ባሕላዊ ክፍተት ነው። ይህም አንዳንድ ጊዜ ጠቅላላውን ታሪክ የሚያዋቅሩትን ነጥቦች እንድትስት ሊያደርግህ ይችላል። ምናልባትም የውጭ እርዳታ የሚያስፈልግህ በዚህ ጊዜ ነው። ነገር ግን ለመጀመሪያዎቹ ታሪኮች ተወዳጅነታቸውን የሰጡት ባሕላዊ ጉዳዮች ስለሆኑ፥ እነዚህን ነገሮች ቸል ልትላቸው አይገባም።

### «ዓውድ አልባ» ምሳሌዎች

ነገር ግን የመነሻ ታሪካዊ ዓውድ ሳይኖራቸው በወንጌላት ውስጥ የሰፈሩት ምሳሌዎችስ? ይህንን ባለፈው ምዕራፍ ውስጥ በወይን ሠራተኞች ምሳሌ (ማቴ. 20፡1–16) ስላብራራን፥ እዚህ ላይ በመጠኑ ብቻ እንከልሰዋለን። አሁንም ሥራው የማጣቀሻ ነጥቦችንና

የመጀመሪያ አድማጮችን የመለየት ጉዳይ ነው። ለዚህም ቁልፉ የማጣቀሻ ነጥቦቹ በግልጽ እስከሚታዩበት ጊዜ ድረስ በተደጋጋሚ ማንበብ ነው። ይህም በበኩሉ የመጀመሪያ አድማጮቹ እነማን እንደ ነበሩ ፍንጭ ይሰጠናል።

በወይኑ ሠራተኞች ምሳሌ ውስጥ የሚገኙ የማጠቀሻ ነጥቦች ሦስት ብቻ ናቸው። እነዚህም የመሬቱ ባለቤት፥ ቀኑን ሙሉ የሠሩና ለአንድ ሰዓት ብቻ የሠሩ ሰዎች ናቸው። ታሪኩ በሚቋጭበት ጊዜ በድጋሚ ትኩረት የሚሰጠው በእነዚህ ሰዎች ላይ በመሆኑ የማጣቀሻ ነጥቦቹን መለየቱ አስቸጋሪ አይሆንም። የመጀመሪያ አድማጮችንም በቀላሉ መለየት ይቻላል። በዚህ ዓይነት ታሪክ የሚያዙት እነማን ናቸው? ሙሉ ቀን ከሠሩት ጋር ራሳቸውን የሚያዛምዱ ሰዎች መሆናቸው ግልጽ ነው። በመጨረሻው ላይ ትኩረት የተሰጠው በእነርሱ ላይ ነውና።

መልእክቱ ከጠፋው ልጅ ታሪክ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን፥ እግዚአብሔር ቸር እንደሆነና ጻድቃን በልግስናው ቅር ሊሰኙ እንደማይገባቸው ያስረዳል። በዚህ የማቴዎስ ዓውድ ውስጥ ግን ተመሳሳይ ይዘት ለአዲስ አድማጭ ሲቀርብ እንመለከታለን። ይህ ምሳሌ በደቀ መዝሙርነት ዓውድ ውስጥ ከሰዎች ማጉረምረም ወይም ጥላቻ ባሻገር እግዚአብሔር ቸር መሆኑን የሚያመለክት ነው።

ይህንኑ ተመሳሳይ ነገር ከጠፋው በግ ታሪክ መረዳት ይቻላል (ማቴ. 18፡12–14)። በሉቃስ ወንጌል ውስጥ ይህ ምሳሌ ከጠፋው ሣንቲምና ከጠፋው ልጅ ጋር ተያይዞ በመቅረብ ለፈሪሳውያን ጠቃሚ መልእክት ያስተላልፋል። የጠፋው በግ ኃጢአተኛ ሲሆን፥ የእርሱ መገኘት በመንግሥተ ሰማይ ደስታን ይፈጥራል። አሁንም ለፈሪሳውያን እንደተነገረው ቃል ክርስቶስ ማኅበረሰቡ የተፋቸውን ሰዎች መቀበሉ ትክክል እንደሆነ ያስረዳል። ማኅበረሰቡ የተፋቸው ሰዎች ራሳቸው ሲሰሙት ግን አፍቃሪው እረኛ እነርሱን እንደሚፈልጋቸው ያስገነዝባቸዋል። በማቴዎስ ወንጌል ምሳሌው በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ የሚኖረውን ግንኙነት ከሚያመለክቱት የተለያዩ አባባሎች ጋር ተሰልፎ እናገኘዋለን። በዚህ አዲስ ዓውድም መልእክቱ ተመሳሳይ ሲሆን፥ እግዚአብሔር ለጠፉትም ግድ እንደሚለው ያስገነዝባል። እዚህ ግን «የጠፉት» የሚለው አሳብ የተቅበዘበዙትን በጎች የሚያሳይ ነው። በማቴዎስ ዓውድ ምሳሌው ምላሽ የሚሰጠው ለእነዚያ ለታናናሾችና ለሚቅበዘበዙት ምን እናድርግ? ለሚለው ጥያቄ ነው። ከቁጥር 6–9 ማንም ከእነዚህ ከታናናሾች አንዱን እንኳ እንዳያስናክል ተገልጾአል። ከቁጥር 10–14 ደግሞ የጠፋው በግ ምሳሌ የጠፋውን ፈልገው በፍቅር እንዲመልሱት ይነግራቸዋል። ይህም

ምሳሌውና መልእክቱ አንድ ሆኖ ሳለ ለሌላ አድማጭ እንዳገለገለ ያስረዳል።

## የእግዚአብሔር መንግሥት ምሳሌዎች

እስካሁን የተጠቀምንባቸው ምሳሌዎች በክርስቶስና በፈሪሳውያን መካከል የነበሩትን ግጭቶች የሚያሳዩ ነበሩ። ይሁንና፥ በተለየ ሁኔታ ሊጠቀሱ የሚገባቸው የእግዚአብሔር መንግሥት ምሳሌዎችም እንዳሉ መገንዘቡ ተገቢ ነው። በእርግጥ ቀደም ብለን የተመለከትናቸውም የእግዚአብሔር መንግሥት ምሳሌዎች ናቸው። እነዚህ ምሳሌዎች ከክርስቶስ ጋር የደኅንነት ዘመን መምጣቱን ያሳያሉ። ነገር ግን በዚህ ስፍራ የምንመለከታቸው ምሳሌዎች በግልጽ «የእግዚአብሔር መንግሥት--- ትመስላለች» የሚሉ ናቸው።

በመጀመሪያ፥ «የእግዚአብሔር መንግሥት--- ትመስላለች» የሚለው መግቢያ በምሳሌው ውስጥ በተጠቀሰው የመጀመሪያው አላባዊ መወሰድ የለበትም። ይህም ማለት የእግዚአብሔር መንግሥት እንደ ሰናፍጭ ዘር፥ እንደ ነጋዴ፥ ወይም በእርሻ ውስጥ እንደተሰወረች መዝገብ አይደለችም። ምሳሌዎቹ፥ «በእግዚአብሔርም መንግሥት እንዲሁ ነው--- » የሚል መልእክት እንደሚያስተላልፉ ማስተዋል ይኖርብሃል። ስለሆነም ከማጣቀሻ ነጥቦቹ ወይም ከዝርዝሮቹ አንዱ ሳይሆን ጠቅላላው ምሳሌ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ባሕርይ አንድ ነገር ይነግረናል።

ሁለተኛ፥ እነዚህን ምሳሌዎች ቀደም ብለን ካየናቸው በተለየ መንገድ ማጥናቱ ፈታኝ ነው። ምላሽን የሚሹ ታሪኮች ሳይሆኑ የማስተማሪያ መሣሪያዎች አድርገን ልንወስዳቸው እንችላለን። ይህ ግን የምሳሌዎቹን አቅጣጫ ማዛባት ይሆናል። በማርቆስ 4 እና በማቴዎስ 13 ውስጥ የሚገኙና መለኮታዊ እስትንፋስ ያረፈባቸው ታሪኮች አሁን ባሉበት ሁኔታ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት እንዲያስተምሩን የታሰቡ ናቸው። መጀመሪያ ግን ከእርሱ መምጣት ጋር የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ ሰዎች እንደቀረበ ክርስቶስ ያስተማረባቸው ናቸው። እነዚህ ክርስቶስ ለደቀ መዝሙርነት ላቀረበው ጥሪ ምላሽ የሚሹ የመልእክቱ መሣሪያዎች ናቸው።

ለምሳሌ፥ ማርቆስ ለሌሎቹ ቁልፍ አድርጎ የወሰደውንና ክርስቶስም የተረጎመውን የዘሪውን ምሳሌ (ማር. 4፡3-20፤ ማቴ. 13፡3-23፤ ሉቃስ 8፡5-15) ልንመለከት እንችላለን። በዚህ ምሳሌ ውስጥ ክርስቶስ የተረጎማቸው ነገሮች የማጣቀሻ ነጥቦች እንደሆኑ ትገነዘባለህ። አራቱ ዓይነት መሬቶች ስለ እግዚአብሔር መንግሥት በሚሰበከበት ጊዜ እንደሚሰጡ አራት ዓይነት ምላሾች ናቸው። የምሳሌው መልእክት ግን

የጊዜው መድረስ ነው፤ «እንዴት እንደምትሰማ ተጠንቀቅ። ቃሉ እየተዘራ ነው። የእግዚአብሔር መንግሥት መልካም የምሥራች፥ የይቅርታ ሐሤት፥ የደቀ መዝሙርነት ጥያቄና ስጦታ ቀርቦልሃል። ይህ ለሁሉም ሰው ስለቀረበ አስተውለህ ስማ፤ ፍሬ የሚሰጥ መሬት ሁን።» ከእነዚህ ምሳሌዎች አብዛኞቹ ወደፊት ደቀ መዛሙርት ለሚሆኑ ብዙ ሰዎች እንደቀረቡ መገንዘብ ይቻላል።

እነዚህ የእግዚአብሔር መንግሥት ምሳሌዎች በመሆናቸው፥ የእግዚአብሔር መንግሥት «ቀድሞውኑ እንደ መጣና ዳሩ ግን ገና እንዳልተመሠረተ» ሲያውጁ እናያለን። ዋና ትኩረታቸው ግን «ቀድሞውኑ» የመምጣቱ አሳብ ነው። የእግዚአብሔር መንግሥት አስቀድሞ መጥቷል፤ የእግዚአብሔር ሰዓት ደርሷል። ስለሆነም አሁን ያለው ጊዜ በጣም አጣዳፊ ነው። በክርስቶስ ስብከት ውስጥ እንዲህ ዓይነቱ ጥድፊያ ሁለት ገጽታዎች አሉት፤ (1) ፍርድ እየመጣ ስለሆነ፥ አደገኛ ሁኔታዎች ከደጅ ቀርበዋል። (2) ነገር ግን ደኅንነት ለሁሉም በነፃ ስለተሰጠ፥ መልካም የምሥራች አለ።

1. በሉቃስ 12፡16–20 የሀብታሙ ሞኝ ምሳሌ ከእግዚአብሔር መንግሥት መቅረብ አንጻር፥ በሀብት ላይ የሚኖረውን አመለካከት በሚያሳይ ዓውድ ተገልጾአል። ምሳሌው ቀላል ነው። ሀብታሙ ሰውዬ ተግቶ በመሥራቱ ምክንያት ሕይወቱን ከአስተማማኝ ደረጃ ላይ እንዳደረሰና በእርካታ ለማረፍ እንደተዘጋጀ ያስባል። ነገር ግን ክርስቶስ በሌላ ስፍራ እንደገለጸው፥ «ነፍሱን ለማዳን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታል» (ማር. 8፡35 እና ትይዩ ምንባቦች)። ስለሆነም ሰውዬው እግዚአብሔርን ከጉዳዩ ውስጥ ሳያስገባ ለመኖር ስላሰበ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው «ሞኝ» ነው። ቅጽበታዊ ጥፋት ሊደርስበት ነውና።

የምሳሌው መልእክት ሞት ሳይጠበቅ እንደሚመጣ ማስተማር አይደለም። ይልቁንም የጊዜውን ጥድፊያ ማሳየት ነው። የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለች። ፍጻሜው በደጅ ቀርቦ ሳለ ለሀብትና ለጊዜያዊ ዋስትና መሯሯጡ ሞኝነት ነው። ይህ እንዴት በዓውዱ እንደተደገፈ ተመልከት። አንድ ሰውዬ ከወላጆቹ የወረሰውን ሀብት ከወንድሙ ጋር ሊካፈል ሲፈልግ፥ ክርስቶስ የዳኝነቱን ሚና ላለመጫወት ይወስናል። ይህንንም ያደረገው ከጊዜው አንጻር የሀብት ጉዳይ ትኩረት የማይሰጠው እንደሆነ ለማሳየት ነው።

ከሁሉም በላይ አስቸጋሪ የሆነውን ፍትሕ የጎደለው መጋቢ ምሳሌ ልንተረጉም የሚገባንም በዚሁ መንገድ ነው (ሉቃስ 16፡1–8)። አሁንም ታሪኩ ቀላል ነው። አንድ መጋቢ የጌታውን ገንዘብ ይሰርቅ ወይም ያባክን ነበርና ለጥፋቱ ምላሽ እንዲሰጥ ተጠየቀ። በዚህ ጊዜ

ቀኑ እንደቀረበ በመገንዘብ ሌላ ግዙፍ የማጭበርበር ተግባር ፈጸመ። ምናልባትም በውጭ ያሉት ወዳጆቹን ሁኔታ አስተማማኝ ለማድረግ የሂሳብ መዝገቡን ያስተካክል ጀመር። ብዙዎቻችን ለመረዳት የምንቸገርበት የዚህ ምሳሌ መልእክት የመጀመሪያዎቹ አድማጮች የመጋቢው ድርጊት እንደሚኮነን እያሰቡ ሳለ በማወደሱ ላይ ያተኩራል።

ክርስቶስ እንዲህ ያለ ታሪክ ሲናገር ለማስተላለፍ የፈለገው መልእክት ምን ይሆን? ምናልባትም ጊዜው እንደ ደረሰ በማሳየት አድማጮቹን ለመፈታተን ፈልጎ ይሆናል። በዚህ ታሪክ ላይ ተገቢ የቁጣ ስሜት ከተሰማቸው ትምህርቱን ምን ያህል ከራሳቸው ጋር ያዛምዱት ይሆን? ጥፋት እየመጣበት እንዳለ ከተገነዘበው መጋቢ ጋር የሚመሳሰል ሁኔታ ላይ የሚገኙ ሲሆን፥ በእነርሱ ላይ የሚመጣው አደጋ ከእርሱ ጋር ሲነጻጸር እጅግ ከፍተኛ ነበር። መጋቢው እርምጃ ወስዷል (ክርስቶስ ተግባሩን እንደማያጸድቅለት ልብ በል)፤ ስላለበት ሁኔታ አንድ ነገር አድርጓል። ክርስቶስ እናንተም እርምጃ ትወስዱ ዘንድ የጊዜው አጣዳፊነት ይጠይቃል የሚል ይመስላል። ሁሉም ነገር በአደጋ ላይ ነው።

2. የንስሐን ተግባር የሚጠይቀው የጊዜው ጥሪ ደግሞ ደኅንነት ነው። ስለሆነም የእግዚአብሔር መንግሥት በሰዎች ፊት እንደቀረበ ስጦታ ነው። በማቴዎስ 13፡44-46 ላይ የቀረጡ መንታ ምሳሌዎች (በእርሻ ውስጥ የተደበቀው መዝገብና ታላቅ ዋጋ ያለው ዕንቁ) ትኩረት የተሰጠው ነገሮቹን ማግኘት በሚያስከትለው ደስታ ላይ ነው። የእግዚአብሔር መንግሥት አንዱን ይማርከዋል፤ በሌላውም ይፈለጋል። ከደስታቸው የተነሣ ያካበቱትን ለሀብቱና ለዕንቁው ይሰጣሉ። የእግዚአብሔር መንግሥት ሀብት ወይም ዕንቁ አይደለም። የእግዚአብሔር መንግሥት የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። የእግዚአብሔርን መንግሥት ማግኘት ሊገለጽ የማይችል ደስታን ያጎናጽፋል። ይኸው ተመሳሳይ ጭብጥ በሉቃስ 15 ውስጥ ጠፍተው በተገኙት ሦስት ነገሮች ውስጥ እንዴት እንደሚንጸባረቅ ልትመለከት ትችላለህ።

አንድ ሰው ምሳሌዎችን ሊማርና ሊያጠና የሚገባው እንደዚህ ነው። ምሳሌዎች ሊደመጡ የሚገባቸው ናቸው። ለክርስቶስና ለአገልግሎቱ ምላሽ እንደሚሹ ጥሪዎች ሊደመጡ ይገባቸዋል።

## ሥነ አፈታታዊ ጥያቄ

የምሳሌዎች ሥነ አፈታታዊ ተግባር ለየት ያለ ነው። ይህም መጀመሪያ በተነገሩበት ጊዜ ብዙውም ትርጉም የማያስፈልጋቸው

ካለመሆናቸው ጋር የተያያዘ ነው። ብዙዎቹ ለአድማጮቻቸው ቅርብ ነበሩ። የብዙዎቹ ውጤታማነት ደግሞ የአድማጩን ትኩረት ለመሳብ መቻላቸው ነበር። ነገር ግን እኛ ጋ የደረሱት በጽሑፍ መልክ በመሆኑ የመጀመሪያዎቹ አድማጮች ያገኙዋቸውን የማጣቀሻ ነጥቦች ለማግኘት ስንል የግድ መተርጎም አለብን። ለዚህም የሚከተሉትን ሁለት ነገሮች ማድረጉ ጠቃሚ ነው።

*1.* እንደ ሁልጊዜው ምሳሌዎቹ አሁን ባሉባቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዓውዶች መርካት አለብን። ምሳሌዎቹ የሚገኙት በጽሑፍ ዓውድ ውስጥ በመሆኑ፥ አሁን በተገለጸው ሐቲታዊ ሂደት አማካኝነት ትርጉማቸውንና መልእክታቸውን በትክክል ልንረዳ እንችላለን። ስለሆነም ልናደርግ የሚገባን ማቴዎስ ያደረገውን ነው (ለምሳሌ፥ 18፡10–14፤ 20፡1–16)። ይኸውም *ያንኑ መልእክት ወደ ራሳችን ዓውድ መመለስ ነው።*

የታሪክ ምሳሌዎችን አስመልክቶ ከአዲስ የማጣቀሻ ነጥቦች ጋር በመናገር አድማጭህ የመጀመሪያዎቹ አድማጮች ላይ የታየውን ስሜት በመላበስ እንዲቆጣ ወይም እንዲደሰት ልታደርግ ትችላለህ። ስለ ርኅሩኁ ሳምራዊ በሚከተለው መልኩ ተለውጦ የቀረበው ታሪክ መንፈሳዊ እስትንፋስ ያረፈበት ነው ብለን የምንከራከርለት አይደለም። ነገር ግን እንደ ሥነ አፈታታዊ አማራጭ ሊታይ ይችላል። ታሪኩ የቀረበው በጥሩ ሁኔታ ለለበሱ አሜሪካውያን የመካከለኛ መደብ አባላት ይመስላል።

> አንድ እሑድ ጠዋት እንክብካቤ የማይደረግላቸው ግለሰቦች ከዋናው መንገድ ዳር ተጥለው ነበር። ሁኔታቸው እጅግ ያሳዝናል። እናት በተቀደደ ሻንጣ ላይ ተቀምጣለች። ልብሶቿ በወጉ አልተለበሱም። ዓይኖቿ ቦዘው በጥሩ ሁኔታ ያልተያዘ ሕጻን ልጅ ታቅፋ ተቀምጣለች። አባት ጺሙን አልተላጨም። ጭንቀት ከፊቱ ላይ እየተነበበ እናት ከታቀፈችው ውጭ ያሉትን ሁለት ወጣት ልጆች ለማቀፍ ይሞክራል። ከአጠገባቸው አገልግሎቱን የጨረሰ አሮጌ መኪና ቆሟል።
>
> ከታች በኩል አንድ የዚያ አካባቢ ጳጳስ መኪና እየነዳ መጣ። በዚያ በኩል ያለፈው ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ ሲል ነበር። ምንም እንኳ የእነዚህ በመንገድ ዳር ያሉት ልጆች አባት እርዳታ መሻቱን በሚያሳዩ መልኩ እጆቹን ቢያውለበልብም፥ አይቶ እንዳላየ አለፈ።

ትንሽ ቆይቶ ሌላ መኪና መጣ። አባትም በትጋት እጁን አወዛውዞ እርዳታ ጠየቀ። ነገር ግን መኪናይቱን የሚያሽከረክረው የኪዋኒስ ክለብ ፕሬዚዳንት ለስብሰባ ቸኩሎ ነበር። (የኪዋኒያንስ ክለብ አባላት በፍትሕና በወርቃማው ሕግ ላይ ጠበቅ ያለ መርህ የሚከተሉ ሰዎች ናቸው።) እርሱም ሰዎቹን እንዳላየ በማስመሰል መንገድ መንገዱን እያየ በፍጥነት ነድቶ አለፈ።

ቀጣዩ ባለ መኪና በሕይወት ዘመኑ ቤተ ክርስቲያን ሄዶ በማያውቅ ከሃዲ (atheist) የሚነዳ ነበር። የቤተሰቡን ችግር በተመለከተ ጊዜ በመኪናው ውስጥ አሳፈራቸው። ችግራቸውን ጠይቆ ከተረዳ በኋላ በአካባቢው ወደሚገኝ አንድ ሆቴል ይዟቸው በመሄድ የቤተሰቡ አባወራ ሥራ እስኪያገኝ ድረስ ለአንድ ሳምንት የሚቆዩበትን ክፍል ተከራየላቸው። በተጨማሪም፥ አባወራው ሥራ ፍለጋ የሚዘዋወርበትን መኪና እንዲከራይና እናትም ለምግብና ለልጆች ልብስ መግዣ እንዲሆናት ተጨማሪ ገንዘብ ሰጣቸው።

ከዚህ መጽሐፍ ደራሲያን መካከል አንዱ አንድ ጊዜ ይህንኑ ሙከራ አድርጎ ነበር። ምእመናኑ ግራ መጋባትና ቁጣ የተቀላቀለበት ምላሽ በመስጠታቸው በሕይወታቸው ለመጀመሪያ ጊዜ ይህንን ምሳሌ እንደ ሰሙ ለማወቅ ተችሏል። ይህ ለመጀመሪያው ዓውድ ምን ያህል እንደሆነ ትገነዘባለህ። ወንጌል አማኙ ፕሮቴስታንት ስለ ጳጳስና የኪዋኒስ ፕሬዚዳንት ሲነገር፤ «ኋላስ» እያለ ሲያስብ ነበር። ቀጥሎ የሚመጣውና ሰዎቹን የሚረዳቸው አንድ ፕሮቴስታንት እንደሆነ ሲያስብ ነበር። ሳምራውያን እጅግ የተከበሩ ሰዎች ይመስል ሁልጊዜም ስለ ርኅሩኁ ሳምራዊ ስንናገር ኖረናልና። ነገር ግን ለአንድ ቤተ ክርስቲያን አዘውታሪ የአንድን ከሀዲ ድርጊቶች ከማወደስ የበለጠ አስቀያሚ ነገር የለም። መጀመሪያ ምሳሌው በተነገረበት ጊዜ ሕግ አዋቂው እንደዚህ ዓይነት አመለካከት ነበር የያዘው።

ይህ ምናልባትም ለአንዳንዶች ትንሽ ከበድ ሊል ይችላል። ነገር ግን የራስህን ሙከራ በምታደርግበት ጊዜ ሐቲትህን በከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለብህ ልናሳስብህ እንሻለን። ከራሳችን ተሞክሮ እንደምንገነዘበው አንዳንዶቻችን ለራሳችን የተሻለ አመለካከት ስላለን ከክርስቶስ ምሳሌዎች አንዳንዶቹን እንደገና ላለንበት ዓውድ በሚስማማ መልኩ በምንናገርበት ጊዜ፥ የራሳችንን ይቅር ያለማለት (ማቴ. 18:23–35)፥ እግዚአብሔር ትክክል መሆን አለበት እያልን በጸጋ ላይ መቆጣታችንን (ማቴ. 20:1–6)፥ ወይም ከእነዚያ «መጥፎ ሰዎች» ራሳችንን በማነጻጸር በክርስቶስ ባገኘነው ነገር መኩራታችንን (ሉቃስ 18:9–14) እንድንገነዘብ ይረዱናል። በዚህ የመጨረሻው ምሳሌ

ላይ ለአንድ ሰዓት ያህል ግሩም ማብራሪያ ሲሰጥ ከቆየ በኋላ በመጨረሻ ጸሎቱ፥ «ጌታ ሆይ፥ በዚህ ታሪክ ውስጥ እንዳሉት ፈሪሳውያን ስላልሆንን እናመሰግንሃለን!» ያለውን የሰንበት ትምህርት አስተማሪ ታሪክ ሲነግሩን መሳቅ ወይ ማልቀስ እንዳለብን አልገባንም ነበር። በእርግጥም በዚህ ጉዳይ ላይ ብዙም መሳቅ አያስፈልግም። ሳቃችን፥ «ጌታ ሆይ፥ እንደዚያ የሰንበት ትምህርት ቤት አስተማሪ ስላልሆንሁ አመሰግናለሁ» የሚል መልእክት ሊያስተላልፍ ይችላልና።

2. ሌላው ሥነ አፈታታዊ አሳባችን የክርስቶስ ምሳሌዎች ሁሉ በሆነ መንገድ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት የሚያስተምሩ መማሪያዎች ከመሆናቸው ጋር የተዛመደ ነው። ስለሆነም በክርስቶስ አገልግሎት ውስጥ የእግዚአብሔር መንግሥት ምን ትርጉም እንዳለው በጥልቀት ልትገነዘብ ይገባል። በዚህ ረገድ ጆርጅ ኢ. ላድን የጻፋትን “The Presence of the Future” (Grand Rapids: Eerdmans, 1974) መጽሐፍ እንድታነብ አጥብቀን እንመክርሃለን።

የእግዚአብሔር መንግሥት አሁን እንዳለና በቅርቡ ከሥራ ላይ እንደሚውል ማሰቡ በራሳችን ዘመን አስፈላጊ ነው። በሀብት ሕይወታቸውን ከአስተማማኝ ደረጃ ላይ ለማድረስ የሚሞክሩ ሰዎች እየቀረበ ያለውን የፍርድ መልእክት ሊሰሙና የጠፉት ኃጢአተኞች ደግሞ መልካሙን የምሥራች የሚያበስረውን ወንጌል ሊቀበሉ ይገባል። ጆአኪም ጄርማያ በግሩም ሁኔታ እንዳስቀመጡት፡—

> «ሁሉም አጽንኦት የሚሰጡት የእርካታ ዘመን ደርሷል። ጠንካራው ትጥቁን ፈትቷል፤ የክፉ ኃይላት እጃቸውን ሊሰጡ ይገባል፤ ሐኪሙ ወደ በሽተኛው መጥቷል፤ ለምጻሞች ነጽተዋል፤ የበደለኛነት ሸክም ተወግዷል፤ የጠፋው በግ ተገኝቷል፤ የአባታችን በር ተከፍቷል፤ ድሆችና ለማኞች ለግብዣ ተጠርተዋል፤ ለጋሹ ጌታ ለሠራተኞቹ ሙሉ ደመወዝ ይከፍላል፤ የሰዎች ሁሉ ልብ በደስታ ይሞቃል። እግዚአብሔር የሚቀበለው ዓመት መጥቷል። የተሸፈነው የአዳኛችን ግርማ በእያንዳንዱ ቃልና ምሳሌ በኩል ያበራልና።» (*Rediscovering the Parables* [New York: Scribner, 1996], p. 181).

# 9

# ሕግ (ሕግጋት)፡ የእስራኤል የቃል ኪዳን ትእዛዛት

በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከስድስት መቶ የሚበልጡ ትእዛዛት አሉ። እነዚህም እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር ታማኞች መሆናቸውን ለማሳየት የሚፈጽሟቸው ናቸው። ከሠላሳ ዘጠኝ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት መካከል እነዚህ ትእዛዛት የሚገኙት በአራት፥ ማለትም በዘጸአት፥ ዘሌዋውያን፥ ዘኍልቁና ዘዳግም ውስጥ ብቻ ነው። ምንም እንኳ ከትእዛዛት ዝርዝሮች በተጨማሪ በእነዚህ መጻሕፍት ውስጥ አንዳንድ ሌሎች ቁም ነገሮች ቢኖሩም፥ የሕግ መጻሕፍት በመባል ይታወቃሉ። ከእስራኤላውያን ሕጋዊ ሥርዓቶች መካከል አንድ ሕግ እንኳ የሌለበት የዘፍጥረት መጽሐፍም በልማድ የሕግ መጽሐፍ በመባል ይታወቃል። ስለሆነም እኛ «ሕግጋት» በምንላቸውና በብሉይ ኪዳን «የሕግ መጻሕፍት» በሚባሉት መካከል ትክክለኛ ተዛማጅነት እንደሌለ መገንዘብ እንጀምራለን።

ለብዙ ክርስቲያኖች ጉዳዩን የበለጠ ውስብስብ የሚያደርገው ደግሞ ከዘፍጥረት እስከ ዘዳግም ያሉት የመጀመሪያዎቹ አምስት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አንዳንድ ጊዜ እንደ አንድ «መጽሐፍ» መጠቀሳቸው ነው። ለምሳሌ፥ ከሙሴ ሞት በኋላ ኢያሱ፥ «ይህ የሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ፥ በውስጡ የተጻፈውን ሁሉ በጥንቃቄ እንድትፈጽመውም ቀንም ሆነ ሌት ከሐሳብህ አትለየው፤ ይህን ካደረግህ አሳብህ ይቀናል፤ ይሳካልም» (ኢያሱ 1፡8) በማለት ሕዝቡ ለእግዚአብሔር በታማኝነት እንዲኖሩ ያበረታታል። በተጨማሪም አንዳንድ ጊዜ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ጠቅላላውን የብሉይ ኪዳን በሚያመለክት መልኩ «ሕግ» ተጠቅሶ ይገኛል። ይህም የአብዛኛዎቹ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አገልግሎት በፔንታቱክ የሚገኘውን ሕግ ማብራራትና ከአማኞች ሕይወት ጋር ማዛመድ ከመሆኑ ጋር የተያያዘ ነው (ለምሳሌ፥ ማቴ. 5፡17-18፤ ሉቃስ 16፡17፤ ቲቶ 3፡9)።

ነገር ግን ብዙውን ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሕግ ሲናገር፥ ከዘጸት 20 ጀምሮ እስከ ዘዳግም መጨረሻ ድረስ የሚዘልቀውን ርእስ ጉዳይ ማለቱ ነው። ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ገረፍ ገረፍ አድርገህ ብታነብ እንኳ፥ በዚያ ውስጥ የተጠቀሰው ሁሉ በትእዛዝ መልክ እንዳልቀረበ ትመለከታለህ። ነገር ግን ከዘጸአት 20 ዘዳግም 33 ያለው አሳብ በአብዛኛው ሕጋዊ ይዘት ስላለው የብሉይ ኪዳን ሕግ ነው እንላለን።

እነዚህን ትእዛዛት አስመልክቶ ለአብዛኞቹ ክርስቲያኖች እጅግ አስቸጋሪው ነገር የሥነ አፈታት ጉዳይ ነው። እነዚህ ሕጋዊ ድንጋጌዎች ከእኛ ጋር የሚዛመዱት እንዴት ነው? ቀድሞስ ነገር ከእኛ ጋር የሚዛመዱበት መንገድ አለ ወይ? ይህ ዋንኛው ጉዳይ ስለሆነ፥ ምዕራፉን ስለ ክርስቲያኖችና ሕግ (ሕግጋት) ግንኙነቶች በመግለጽ እንጀምራለን። ይህም ያኔዚያዊ ውይይታችንን የሚያዳብረው ይሆናል።

## ክርስቲያንና የብሉይ ኪዳን ሕግ

ክርስቲያን ከሆንህ፥ የብሉይ ኪዳንን ሕግ መጠበቅ አለብህ? ይህን ማድረግ ካለብህ ታዲያ የእንስሳን ሥጋ መሥዋዕት ለማቅረብ እንስሳውን የምትሠዋበት መሠዊያ ወይም ማዕከላዊ የማምለኪያ ስፍራ ሳይኖር እንዴት ሕጉን የመጠበቁን ተግባር ልትወጣ ትችላለህ? (ዘሌ. 1–5)። እንዲያውም የብሉይ ኪዳን ሕግ እንደሚደነግገው እንስሳትን አርደህ የምታቃጥል ከሆነ በተለይ በምዕራቡ ዓለም ተከሰህ ወኅኒ መውረድህ የማይቀር ነው። ነገር ግን ከእንግዲህ የብሉይ ኪዳን ሕግ መጠበቅ ከሌለብህ፥ ክርስቶስ፥ «እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ ሕግ ሁሉ ይፈጸማል እንጂ ከሕግ አንዲት ፊደል ወይም አንዲት ቃል እንኳ አትሻርም» (ማቴ. 5፡18) ሲል ምን ማለቱ ነው? ይህ ጥያቄ ምላሽ ይሻል። ምላሹም የብሉይ ኪዳን ሕግ አሁንም በክርስቲያኖች ሕይወት የሚሠራበትን መንገድ ያሳየናል። (ይኸውም ከዘጸአት 20 እስከ ዘዳግም 33 የሚገኙትን ሕግጋት በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ መጠበቅ ስለሚገባን መንገዶች ያሳየናል።)

ክርስቲያን ከብሉይ ኪዳን ሕግ ጋር ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ስድስት የመነሻ መርሆዎች ለመስጠት እንፈልጋለን። እነዚህ መርሆዎች ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸው ሲሆኑ፥ ለአንዳንዶች እዚያ በመስጠት የሌሎቹን ማብራሪያዎች ለኋላ አቆይተናል። እነዚህ መርሆዎች ሕግን በትክክል ተገንዝበህ እንድታደንቅ የሚያደርጉህ ናቸው።

1. *የብሉይ ኪዳን ሕግ ቃል ኪዳን ነው።* ቃል ኪዳን በውስጡ የተካተቱትን ግዴታዎች ለመፈጸም በተስማሙ ሁለት ወገኖች (ተዋዋዮች) መካከል የሚካሄድ ነው። በብሉይ ኪዳን ውስጥ ብዙ ቃል ኪዳኖች ሁሉን ቻይ ከሆነው አምላክ ባሪያዎችና (አገልጋዮች) እና ጥገኞች ለሆኑት እስራኤላውያን በቸርነት ተሰጥተዋል። ቃል ኪዳኖቹ የአገልግሎት ጥቅሞችንና ጥበቃዎችን ያስገኛሉ። ነገር ግን አገልጋዩ ለጌታ ሙሉ በሙሉ ታማኝ መሆን ይጠበቅበታል። አንዳች የታማኝነት ጉድለት ቢገኝበት የሚደርስበት ቅጣት በቃል ኪዳኑ ውስጥ ሰፍሯል። አገልጋዩ ታማኝነቱን የሚገልጸው እንዴት ነበር? በቃል ኪዳኑ ውስጥ

የሰፈሩትን ደንቦች በመታዘዝ ነበር። አገልጋዩ ደንቦቹን ተግባራዊ እስካደረገ ድረስ ጌታው ታማኝ እንደሆነ ይገነዘባል። ደንቦቹ በሚጣሱበት ጊዜ ግን ጌታው የቅጣት እርምጃ ለመውሰድ በቃል ኪዳኑ መሠረት ይገደዳል።

እግዚአብሔር ብሉይ ኪዳንን ያዋቀረው በዚህ የጥንታዊ ቃል ኪዳኖች ምስያ ላይ ሲሆን፥ ጌታ በሆነው ያህዌና አገልጋዩ በሆነው የእስራኤል ሕዝብ መካከል ተግባራዊ የሚሆን ስምምነት መሥርቷል። በመሆኑም ከዘጸአት 20 እስከ ዘዳግም 33 እንደምንመለከተው፥ ከእግዚአብሔር ለሚያገኙት ጥቅምና ጥበቃ በቃል ኪዳን ሕግ ውስጥ የሚገኙትን ከስድስት መቶ በላይ ደንቦች መጠበቅ ነበረባቸው።

ይህ የቃል ኪዳን ሰነድ ስድስት ክፍሎችን ያካትታል። እነዚህም መግቢያ፥ ቅድመ ቃል ኪዳን፥ ደንቦች፥ ምስክሮች፥ ማዕቀቦችና የሰነድ ክለሳ ናቸው። መግቢያው ቃል ኪዳን አድራጊዎቹን ያስተዋውቃል («እኔ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ---»)። ቅድመ ቃል ኪዳን ተቀባዮቹ እርስ በርስ የታሳሰሩበትን አጭር ታሪክ ያስረዳል። («ከግብፅ ምድር አመጣኋችሁ---»)። ደንቦች ደግሞ ቀደም ብለን እንደገለጽነው ሕግጋቱ ራሳቸው ናቸው። ምስክሮች ደግሞ ቃል ኪዳኑን የሚያጠናክሩ ናቸው። (ሰማይና ምድር ወይም እግዚአብሔር ራሱ፤ ይህም የቃል ኪዳኑ መፈጸም፥ ፍጥረትን ሁሉ እንደሚመለከት የሚያስረዳ ነው። ለምሳሌ፥ ዘዳግም 4፡26፤ 30፡19)። ማዕቀቦች ለቃል ኪዳኑ መፈጸሚያ እንደማበረታቻ የቀረቡ በረከቶችና መርገሞች ናቸው (ለምሳሌ፥ ዘሌ. 26 እና ዘዳ. 28-33)። የሰነድ ክለሳውም ደግሞ ቃል ኪዳኑ እንዳይዘነጋ በመደበኛነት የሚከለስበት ነው (ለምሳሌ፥ ዘዳ. 17፡18-19፤ 31፡9-13)። የመጀመሪያው (ዘዳ. 20-ዘሌ. 27 በዘኁልቁ ከቀረበው ተጭማሪ ጋር) እና ሁለተኛው የሕግ መግለጫ (በዘዳግም ውስጥ እንደተገለጸው የተስፋይቱን ምድር ከመያዛቸው በፊት) ይህንኑ ባለ ስድስት ክፍል ሰነድ ያመለክታሉ።

2. *ብሉይ ኪዳን ለእኛ የተሰጠ ቃል ኪዳን አይደለም።* ክርስቲያኖች የጥንቱን ብሉይ ኪዳን የመታዘዝ ግዴታ የለባቸውም። ስለሆነም በአዲሱ ኪዳን እስካልታደሱ ድረስ የትኞቹም የብሉይ ኪዳን ሕግጋት ለክርስቲያኖች ተፈጻሚነት እንደማይኖራቸው ልናስብ እንችላለን። ይህም ማለት አንድ የብሉይ ኪዳን ሕግ በአዲስ ኪዳን ውስጥ በሆነ መንገድ እንደገና ካልተገለጸ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ተፈጻሚ አይሆንም ማለት ነው (ሮሜ 6፡14-15 አንብብ)። በብሉይና በአዲስ ኪዳን መካከል ለውጦች አሉ። ሁለቱ አንድ ዓይነት አይደሉም። እግዚአብሔር ከእኛ የሚጠብቀው የታማኝነት መረጃ ከቀድሞዎቹ እስራኤላውያን የጠበቀው ዓይነት አይደለም። ታማኝነቱ

እንዳለ ቢሆንም፥ ይህንኑ ታማኝነት የምናሳይበት መንገድ በመጠኑ ተለውጧል።

3. *አንዳንድ የብሉይ ኪዳን ሕግጋት አልተለወጡም።* ጠቅላላዎቹን የብሉይ ኪዳን ሕግጋት ሰፋ አድርጎ ለመመልከት ራሱን የቻለ መጽሐፍ የሚጠይቅ ቢሆንም፥ ዐበይት ሕግጋትን በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች መክፈል ይቻላል። ከእነዚህ ሁለት ክፍሎች የትኞቹም ክርስቲያኖች እንዲፈጽሙ የታዘዟቸው አይደሉም። እነዚህም (1) የእስራኤላውያን ማኅበራዊ ሕግጋትና (2) የእስራኤላውያን ሥርዓታዊ ሕግጋት ናቸው። ማኅበራዊ ሕግጋት ለተለያዩ (ዐበይትና ንዑሳን) ወንጀሎች የሚበየኑትን ቅጣቶች የሚዘረዝሩ ናቸው። እንዲህ ዓይነት ሕግጋት የሚያገለግሉት ለጥንታዊቷ እስራኤል ዜጎች ሲሆን፥ በአሁኑ ዘመን የጥንታዊቷ እስራኤል ዜጋ የሆነ ሰው በዓለም ላይ የለም። የሥርዓት ሕግጋት ከብሉይ ኪዳን ሕግጋት እጅግ ብዙውን ክፍል የሚሸፍኑ ሲሆን፥ በዘሌዋውያን ውስጥ በስፋት ተጠቅሰዋል። በብዙ የዘጸአት፥ የዘኁልቁና የዘዳግም ክፍሎችም ተጠቅሰው እናገኛቸዋለን። እነዚህ ሕግጋት የአምልኮ ዕቃዎችን ከመሥራት አንሥቶ እስከ ካህናት ኃላፊነቶች፥ ሊሠዉ ስለሚገባቸው እንስሳትና እንዴትስ ይህንኑ ማድረግ እንደሚገባ እስራኤላውያን እንዴት አምልኮውን ማካሄድ እንዳለባቸው የሚደነግጉ ናቸው። እንስሳትን መሠዋት (መግደል፥ ማብሰልና መብላት) የብሉይ ኪዳን አምልኮ ማዕከል ነበር። ደም ሳይፈስ ኃጢአት አይሰረይም ነበር (ዕብ. 9፡22)። ክርስቶስ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ራሱን በሠዋ ጊዜ ግን ይህ የብሉይ ኪዳን የአሠራር ሥርዓት አበቃ። ምንም እንኳ አምልኮው በአዲስ ኪዳን አቀራረብ የቀጠለ ቢሆንም፥ አሮጌው አሠራር በክርስቲያናዊ ልምምድ የአምልኮ ሥርዓት ውስጥ ቦታ የለውም።

እንደዚህ ላሉት የኪዳን ለውጦች ብዙ ዘመናዊ ምስያዎች ( ን ልዠግ ስ) አሉ። ለምሳሌ ያህል በሥራ ስምምነቶች ረገድ በሥራ ሁኔታዎች፥ በሠራተኞች መዋቅሮች፥ በደመወዝ መጠን፥ ወዘተ... ለውጦች ሊታዩ ይችላሉ። በዚህ ላይ ግን እንደ የሥራ ልምድ፥ ዕረፍት፥ ዘፈቀዳዊ የሠራተኛ ቅነሳን የሚከላከሉ ደንቦችን የመሳሰሉ አንዳንድ የቀድሞ የሥራ ስምምነት ገጽታዎች ሊታከሉ ይችላሉ። ምንም እንኳ የሥራ ስምምነት በእግዚአብሔርና በእስራኤል መካከል ከነበረው የቃል ኪዳን ደረጃ የሚታይ ባይሆንም፥ *አዲሱ ቃል ኪዳን ከአሮጌው የተለየና ቢሆንም ሙሉ በሙሉ የተለየ አለመሆኑን* ለማብራራት ይረዳል ብለን እናስባለን። የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ኪዳኖች ሁኔታ ይህንን የሚመስል ነው።

አንድ ሰው ምናልባት፥ «ክርስቶስ ከሕግ አንዲት ነጥብ እንኳ አትወድቅም በማለቱ አሁንም ከሕግ ሥር መሆናችንን ገልጾ የለምን?» የሚል ጥያቄ ሊያነሣ ይችላል። ክርስቶስ ያለው (ሉቃስ 16፡16–17) ሕግ እንደማይለወጥ ነው። መጥምቁ ዮሐንስ አዲሱን ቃል ኪዳን መስበክ በጀመረ ጊዜ ሕግና ነቢያት ወደ ፍጻሜ ደርሰው ስለነበር፥ ክርስቶስ ሰዎች በፍጥነት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባታቸው አስፈላጊ በመሆኑ አሳብ ላይ አጽንኦት ሰጥቶ ተናግሯል። ምክንያቱም ይህ ካልሆነ ለመለወጥና ለማሻሻል የማይቻለውን አሮጌ ሕግ ለመጠበቅ የሚገደዱ መሆናቸው ነበር። ክርስቶስ አዲስ ሕግ ሰጥቷል። ይህ አዲሱ ሕግ አሮጌውን ፈጽመው እንጂ አላስወገደውም። አዲሱን ሕግ ወይም ቃል ኪዳን የሚጠብቁ አማኞች አሮጌውን ቃል ኪዳን አጥብቀው ይጠብቁ ከነበሩት ጸፎችና ፈሪሳውያን የበለጠ ጽድቅ ያገኛሉ። ክርስቶስ የብሉይ ኪዳን ሕግጋትን ሙሉ በሙሉ ጠብቆ ሲያበቃ አዲስ ሕግ ሰጥቷል። ይህም የፍቅር ሕግ ነው (ከታች ቁጥር 4ን አንብብ።)

4. *አሮጌው ቃል ኪዳን በአዲሱ ቃል ኪዳን ውስጥ በከፊል ታድሷል።* ይህንን ስንል የትኛውን ክፍል ማለታችን ነው? መልሱ አንዳንድ የብሉይ ኪዳን ሥነ ምግባራዊ ሕጎች አንዳንድ ገጽታዎች ለክርስቲያኖች እንደሚጠቅሙ ተደርገው በአዲስ ኪዳን ውስጥ እንደገና ተጽፈዋል የሚል ነው። እነዚህ የአሮጌው ሕግ ገጽታዎች እግዚአብሔር በሚመሠርተው አዲስ ኪዳን ውስጥ ለሕዝቡ እንደሚያገለግሉ ተደርገው የተነደፉ ናቸው። እንደ እውነቱ ከሆነ እነዚህ ሕግጋት በቀጣይነት ሊያገለግሉ የቻሉት ሕግና ነቢያት ሁሉ የተመሠረቱባቸውን ሁለት የአዲስ ኪዳን መሠረታዊ ሕግጋት የሚደግፉ በመሆናቸው ነው (ማቴ. 22፡40)። እነዚህም፥ «እግዚአብሔር አምላክህን በፍጹም ልብህ፥ በፍጹም ነፍስህና በፍጹም አሳብህ ውደድ» (ዘዳ. 6፡5) እና «ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ» (ዘሌ. 19፡18) የሚሉ ናቸው። ክርስቶስ አንዳንድ የብሉይ ኪዳን ሕግጋትን ወስዶ አዲስ አፈጻጸም ይሰጣቸዋል (ማቴ. 5፡21–48 አንብብ)። ይህንንም የሚያደርገው ከመጀመሪያው የበለጠ መጠነርእይ (ስችኮፕ ) እንዲኖራቸው አድርጎ በመበየን ነው። ስለሆነም ሕግጋት ራሳቸው ከብሉይ ኪዳን ወደ አዲሱ ኪዳን ታድሰዋል ከማለት ይልቅ የሕግጋቱ ገጽታዎች ታድሰዋል ማለቱን እንመርጣለን። ምክንያቱም በክርስቲያኖች ላይ ቀጣይነት ያለው ግዴታ የሚጥሉት እግዚአብሔርንና ባልንጀሮቻቸውን እንዲወዱ ከሚያዘው ትእዛዝ ሥር የሚገኙ የሕግጋት ገጽታዎች ናቸውና።

5. *ምንም እንኳ ለእኛ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ባይሆንም፥ የብሉይ ኪዳን ሕግ ሁሉ አሁንም የእግዚአብሔር ቃል ነው።* በቀጥታ ለእኛ ባይሰጡም እግዚአብሔር እንድናውቃቸው የሚፈልጋቸው ብዙ ትእዛዛት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሉ። ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን ክርስቶስ የምታዩትንና የምትሰሙትን ለዮሐንስ ሂዱና ንገሩ ሲል ያዘዘው ትእዛዝ ነው (ማቴዎስ 11፡4)። መጀመሪያ ይህ ትእዛዝ የተሰጠው ለዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ነበር። እኛ ስለዚህ ትእዛዝ እናነባለን እንጂ ትእዛዙ ለእኛ የተሰጠ አይደለም። እንደዚሁም የብሉይ ኪዳን ሕግ የተሰጠው ለጥንታዊቷ እስራኤል ነው። እኛ ስለዚያ ሕግ እናነባለን እንጂ ለእኛ የተሰጠ አይደለም።

6. *የአዲስ ኪዳን ሕግ «የክርስቶስ ሕግ» ነው ሊባል የሚችለው ከብሉይ ኪዳን ሕግ በግልጽ የታደሰው ብቻ ነው* (ገላ. 6፡2ን አንብብ)። በዚህ ምድብ ውስጥ የሚገቡት በአዲስ ኪዳን ውስጥ ክርስቲያኖች ሊጠብቋቸው እንደሚገቡ ተደርገው የተጠቀሱት አሥርቱ ትእዛዛት (ማቴ. 5፡21–37፤ ዮሐ. 7፡23 አንብብ) እና በዘዳግም 6፡5 እንዲሁም 19፡18 ላይ የሚገኙ ታላላቅ ሕግጋት ናቸው። ክርስቲያኖች ሕግጋትን ሁሉ ማወቃቸው ጠቃሚ ቢሆንም፥ ከላይ እንደተጠቀሱት ክርስቲያኖች እንዲጠብቋቸው የታዘዙት ሌሎች ሕግጋት የሉም።

## የሕግ ሚና በእስራኤልና በመጽሐፍ ቅዱስ

ከዚህ በላይ ካቀረብነው ገለጻ በመነሣት ሕግ ጠቃሚ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አይደለም ብሎ መደምደሙ ትልቅ ስሕተት ይሆናል። ጳውሎስ እንደሚለው፥ በደኅንነት ታሪክ ውስጥ እኛን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት እንደ ሞግዚት ሆኖ አገልግሏል (ገላ. 3፡24)። ይህንንም ያደረገው የእግዚአብሔር መመዘኛዎች ምን ያህል ከባዶች እንደሆኑና መለኮታዊ ድጋፍ ካልተሰጠው አንድ ሰው እነዚህን መመዘኛዎች ሊያሟላ እንደማይችል በማሳየት ነው። ለጥንታዊ እስራኤላውያንም ሕግ ያገለገለው በዚሁ ዓይነት ነበር። ሕግ ራሱ አላዳናቸውም። አድኗቸዋል ማለቱ ከፔንታቱክም ሆነ ከነቢያት መልእክቶች ጋር የማይጣጣም አመለካከት ይሆናል። እስራኤልን ያዳነው እግዚአብሔር ነው። ከግብጽ ባርነት ያወጣቸው፥ ወደ ከነዓን ምድር ያስገባቸውና የበረከቷ ተቋዳሾች ያደረጋቸው ራሱ እግዚአብሔር ብቻ ነበር። ሕግ ከእነዚህ አንዱንም አላደረገም። ሕግ ያደረገው ነገር ቢኖር እስራኤል ከእግዚአብሔር ጋር የነበራትን ግንኙነት መወከል ነበር።

በዚህ መልኩ ሕግ እንደ ሞዴል ይታያል። በጥንታዊቷ እስራኤል አንድ ሰው እግዚአብሔርን ለማስደሰት ሊያደርግ የሚችላቸው ወይም

የሚገባቸው ነገሮች ዝርዝር አይደለም። ይልቁንም ሕግ ለእግዚአብሔር ታማኝ የመሆንን ምሳሌዎች ወይም ናሙናዎች ያሳያል።

### አጠቃላይ ሕግ

ከላይ የቀረበውን አሳብ በመንተራስ የሚከተለውን ምንባብ አንብብ።

«የምድራችሁን መከር በምትሰበስቡበት ጊዜ፣ በእርሻችሁ ዳርና ዳር ያለውን አትጨዱ፤ ቃርሚያውንም አትልቀሙ። የወይንህን እርሻ አትቃርም፤ የወደቀውንም አትልቀም፤ ለድኾችና ለመጻተኞች ተውላቸው፤ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ--- ነኝ። አትስረቁ፤ አትዋሹ፤ ከእናንተ አንዱ ሌላውን አያታል። በስሜ በሐሰት አትማሉ፤ በዚህም የአምላካችሁን--- ስም አታርክሱ፤ እኔ እግዚአብሔር--- ነኝ። ባልንጀራህን አታጭበርብር፤ አትቀማውም፤ የሙያተኛውን ደመወዝ ሳትከፍል አታሳድር። ደንቆሮውን አትርገም፤ በዓይነ ስውሩም ፊት ዕንቅፋት አታኑር፤ ነገር ግን አምላክህን--- ፍራ፤ እኔ እግዚአብሔር--- ነኝ» (ዘሌ. 19፡9-14፥ ከአ.መ.ት.)።

እንደ እነዚህ «አድርግ፥ አታደርግ» የሚሉ ትእዛዛት አጠቃላይ ሕግጋት ይባላሉ። እነዚህ እስራኤላውያን ከእግዚአብሔር ጋር የገቡትን ቃል ኪዳን ለመፈጸም ሊያደርጓቸው የሚገቧቸውን ነገሮች የሚገልጹ ቀጥተኛና ተግባራዊ ትእዛዛት ናቸው። ነገር ግን እንዲህ ዓይነት ሕግጋት ሁሉን አቀፍ አለመሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል። ለምሳሌ፥ በቁጥር 9 እና 10 ያሉትን የመከር ሕግጋት ቀረብ ብለህ ተመልከት። በዚህ ትእዛዝ ሥር የሚካተቱት እንደ ስንዴና ገብስ የመሳሰሉ እህሎች እንደሆኑ ግልጽ ነው። ይህ ማለት ወይን ብትተክል ምርትህን ለድሀና ለመጻተኛ የማካፈል ግዴታ የለብህም ማለት ነው? አንተ ነፃ ሆነህ ሌሎች የብሉይ ኪዳንን የደኅንነት ሕግ ተግባራዊ ያደርጋሉ? አይደለም። ሕግ እንደ ሞዴል ነው። ሊሆን የሚችለውን ሁሉ ከመዘርዘር ይልቅ ምሳሌ በመስጠት መመዘኛን ይመሠርታል። አሁንም ቁጥር 13 እና 14ን አንብብ። የእነዚህ ዓረፍተ ነገሮች ዓላማ ለቀን ሠራተኞች ክፍያ ለማዘግየትና የአካል ጉዳተኞችን ለመበደል መሠረት የሚሆኑትን ነገሮች ማስወገድ ነው። የአንድን የቀን ሠራተኛ ገንዘብ ሳትከፍል አድረህ ነገ ጠዋት ብትሰጠውስ? በክርስቶስ ዘመን የነበሩት ጻፎችና ፈሪሳውያን «አታሳድር» (ሆ ርን ግህት) የሚለውን ቃል በመጠቀም እንዲህ ዓይነቱ ተግባር ትክክል ነው ብለው ሊከራከሩ ይችላሉ። ነገር ግን እንዲህ ዓይነቱ ጠባብና የራስ ወዳድነት ሕጋዊነት እግዚአብሔር የሰጠውን ያንኑ ሕግ ማዛባት ነው። በሕጉ ውስጥ

የሚገኙ ቃላት ሊታሰቡ የሚችሉ አማራጭ ሁኔታዎች ሁሉ የተካተቱባቸው ሙያዊ (ቴክኒካል) አገላለጾች ሳይሆኑ፥ አጠቃላይ ተዛማጅነት ያላቸው አስተማማኝ መመሪያዎች ናቸው። በተመሳሳይ ሁኔታ፥ ድዳውን፥ ሽባውን ወይም የአእምሮ ዘገምተኛውን ከጎዳህ የቁጥር 14ን ሕግ ታዝዣለሁ ልትል ትችላለህ? በፍጹም አልችልም። «ደንቆሮ» እና «ዓይነ ስውር» የአካል ጉዳተኞች በመሆናቸው ከመናቅ ይልቅ ሊከበሩ የሚገባቸውን ሰዎች ሁሉ ለማመልከት የተመረጡ ምሳሌዎች ናቸው።

ዘመናዊ ማኅበረሰቦችም ብዙውን ጊዜ አንጻራዊ ሕጎች አሏቸው። ለምሳሌ፥ የአሜሪካ የፌዴራልና የስቴት ሕጋዊ ደንቦች ስለ ሁሉም ነገሮች በሺዎች የሚቆጠሩ ድንጋጌዎች አሏቸው። ይህም ሆኖ ሁሉንም ሕግ በዝርዝር ማድረግ ስለማይቻል አንድ ተጠርጣሪ ተከስሶ በሚቀርብበት ጊዜ ወንጀለኛ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የዳኛን ብያኔ ይጠይቃል። ይህም የብሉይ ኪዳን ሕግ ከአሜሪካ ፌዴራል/ስቴት ደንቦች ይልቅ ሰፋ ሕግጋትን ካወጣ በኋላ የአገሪቱን የፍትሕና የነጻነት ባሕርያት ከሚደነግገው ሕገ መንግሥት ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ያሳየናል።

የብሉይ ኪዳን አጠቃላይ (ያልተዘረዘሩ) ሕግጋት ሞዴሎች (ውስን ሳይሆኑ ምሳሌዎች) ናቸው የሚለው ማብራሪያችን ለእነዚህ ሕግጋት የሚታዘዝበትን መንገድ ለማሳነስ ለሚፈልግ ሰው የሚሰጠው እገዛ እንደሌለ አስተውል። እነዚህ ሕግጋት ምንም እንኳ በተወሰኑ ቃላት ቢገለጹም፥ በመንፈስ የአጠቃላይነት ባሕርይ ያላቸው ናቸው። ስለሆነም አንድ ሰው የብሉይ ኪዳንን ሕግ መንፈስ ለመጠበቅ ከፈለገ የኋላ ኋላ መውደቁ አይቀርም። እንዲህ ያለውን ከፍተኛና የጠለቀ መመዘኛዎች አልፎ ባለማቋረጥ እግዚአብሔርን ሊያስደስት የሚችል ሰው የለም (ከሮሜ 8፥1–11 ጋር አነጻጽር)። ከፍተኛ የስኬት ዕድል ያለው ከሕጉ መንፈስ ይልቅ ፊደል የሚከበርበት የፈሪሳውያን አሠራር ብቻ ነው። ይህ ግን ሕጉን እግዚአብሔር እንዲጠበቅ በፈለገበት መንገድ መጠበቅ ሳይሆን፥ ዓለማዊ ስኬትን የመሻት መንገድ ብቻ ነው (ማቴ. 23፥23)።

ስለሆነም እዚህ ላይ መሠረታዊ ሥነ አፈታታዊ ምልከታ ማድረግ አለብን። ይኸውም *ሕጉ በራሳችን እግዚአብሔርን ማስደሰቱ ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ የሚያሳይ መሆኑ ነው*። ጳውሎስ በሮሜ 3፥20 ተመሳሳይ አሳብ ገልጾአል። ነገር ግን ነጥቡ ሥነ መለኮታዊ እውነት ብቻ ሳይሆን፥ ከሕግ አንባቢዎች ጋር የሚዛመድ ነው። የብሉይ ኪዳንን ሕግ በምናነብበት ጊዜ የእግዚአብሔር ሕዝብ ለመሆን ምን ያህል የማይገባን መሆናችንን በመገንዘብ ራሳችንን ልናዋርድ ይገባል።

የብሉይ ኪዳንን ሕግጋት ሳናሟላ በፊቱ ተቀባይነት እንድናገኝ ስላደረገ ልናመሰግነው ይገባል። ከዚያ ውጭ እግዚአብሔርን የምናስደስትበት ተስፋ የለንምና።

## *ተናጠላዊ ሕግ*

ይህ የአጠቃላይ ሕግ አቻ ሲሆን፥ ነገሮችን በተናጠል (case-by-case) የሚመለከት ነው። እስኪ የሚከተለውን ምንባብ አንብብ።

> «ወገንህ የሆነ ወንድን ወይም ሴትን ገዝተህ ስድስት ዓመት ካገለገለህ፤ በሰባተኛው ዓመት ዐርነት አውጣው። በምታሰናብተውም ጊዜ ባዶ እጁን አትስደደው። ከመንጋህ፤ ከዐውድማህና ወይን ከመጭመቂያህ በልግስና ስጠው፤ አምላክህ እግዚአብሔር--- በባረከህ መጠን ስጠው። አንተም ራስህ በግብፅ ባሪያ እንደነበርህና አምላክህ እግዚአብሔር--- እንደተቤዠህ አስታውስ፤ ይህን ትእዛዝ ዛሬ የምሰጥህም በዚሁ ምክንያት ነው። ነገር ግን አገልጋይህ፤ አንተንና ቤተሰብህን ከመውደዱና ከአንተም ጋር ደስተኛ ሆኖ ከመኖሩ የተነሣ፤ ሖከአንተ መለየት አልፈልግምደ ቢልህ፤ ጆሮውን ከቤትህ መዝጊያ ላይ በማስደገፍ በወስፌ ትበሳዋለህ፤ ከዚያም ዕድሜ ልኩን አገልጋይህ ይሆናል። በሴት አገልጋይህም ላይ እንደዚሁ አድርግ።» (ዘዳግ. 15፡12–17)።

እንደዚህ ባለው ሕግ ውስጥ የሚገኙ አላባውያን በቅድመ ሁኔታዎች ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ይህ ሕግ የሚሠራው (1) ቢያንስ አንድ ባሪያ ላለው እስራኤላዊ፥ ወይም (2) የባርነት ዘመኑ ካበቃ በኋላ ከእርሱ ጋር ለመኖር ወይም ላለመኖር የሚፈልግ ባሪያ ላለው እስራኤላዊ ነው። እስራኤላዊ ካልሆንህ ወይም እስራኤላዊ ሆነህ ባሪያዎች ከሌሉህ፥ ሕጉ ለአንተ አይሠራም። አንተ ባሪያ ብትሆን ሕጉ ወደ ጌታህ ያነጣጠረ በመሆኑ መብትህን በማስከበር በተዘዋዋሪ መንገድ በአንተ ሕይወት ውስጥ ይሠራል። ነገር ግን ሕጉ ለሁሉም የሚሠራ አይደለም። በአንድ ሰው ላይ በተወሰነ ጊዜ በሚሠራ ወይም በማይሠራ ቅድመ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ነው።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከሚገኙ ከስድስት መቶ በላይ ፔንታቱካል ሕግጋት እንዲህ ዓይነቱ ተናጠላዊ ሕግ ብዙውን ክፍል ይሸፍናል። የሚገርመው ከእነዚህ መካከል በአዲስ ኪዳን ውስጥ በግልጽ የሰፈረ አለመኖሩ ነው። ከባሕርያቸው ሳቢያ ከእስራኤል ማኅበራዊ፥ ሃይማኖታዊና ሥነ ምግባራዊ ሕይወት ጋር የሚዛመዱ በመሆናቸው ለክርስቲያን የሚያበረክቱት አገልግሎት የላቸውም። እንግዲህ፥

ክርስቲያን ከተናጠላዊ ሕግጋት ምን ምን አሁንዚያዊ መርሆችን ሊማር ይችላል? በዘዳግም 15፥12-17 አያሌ ነጥቦችን እናገኛለን።

በመጀመሪያ፥ በግለሰብ ደረጃ ባሪያዎችን ላናስተዳድር ብንችልም፥ በአሮጌው ቃል ኪዳን እግዚአብሔር ለባሮች የሰጠው ሕግ ያን ያህል ጭካኔ የተሞላበት አይደለም። አሜሪካን ጨምሮ በብዙ የዓለም ታሪክ እንዲህ ዓይነት የባርነት አገዛዝ እንደሌለ እንገነዘባለን። አንድ ባሪያ ከስድስት ዓመታት አገልግሎት በኋላ ነፃ መውጣቱ ራሱ የባሪያ አገዛዝ ከተገቢው በላይ እንዳይሄድ ያደርጋል።

ሁለተኛ፥ እግዚአብሔር ባሮችን እንደሚወድ እናውቃለን። ፍቅሩም በሕጉ ውስጥ በተካተቱ የደኅንነት ደንቦችና በቁጥር 14 እና 15 ሕዝቡ ቀደም ሲል ባሮች እንደነበሩና አሁንም ለባሮች በጎነት እንዲያደርጉ በጠየቀባቸው ክፍሎች ተገልጾአል።

ሦስተኛ፥ ለባሮች በጎነትን በመዋል ከነጻነታቸው ይልቅ በባርነት መኖርን እንዲመርጡ ማድረግ እንደሚቻል እንረዳለን። ይህም ማለት ባሪያ አሳዳሪው ለባሮቹ ምግብ፥ ልብስና መጠለያ በማቅረብ የሚያስፈልጋቸውን ያሟላላቸዋል። ነገር ግን በጥንታዊቷ ፍልስጥኤም በነበረው ደካማ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ከጌታቸው ከተለናበቱ በኋላ ራሳቸውን ሊያቋቁሙ ስለማይችሉ በረሃብ ሊሞቱ ይችላሉ።

አራተኛ፥ ባሪያ አሳዳሪው ሙሉ በሙሉ የባሮቹ ጌታ አይደለም። ባሮቹን የሚያስተዳድረው ብሉይ ኪዳን በሚሰጣቸው ብዙ ሕግጋት ላይ ተመሥርቶ ነው። እግዚአብሔር የባሪያውም የባሪያ አሳዳሪውም ጌታ ነው። ቁጥር 15 እንደሚለው፥ እግዚአብሔር ዕብራውያንን ሁሉ ከባርነት ነፃ ስላወጣቸው የነፃዎቹም ሆነ የባሮቹ ባለቤት ነው።

እነዚህ አራት ምልከታዎች ለእኛ ጠቃሚ ትምህርቶች ናቸው። የዘዳግም 15፥12-17 ሕግ ለእኛ ወይም ስለ እኛ በቀጥታ አለመነገሩ አሳሳቢ ጉዳይ አይደለም። ዋናው ነገር ስለ እግዚአብሔር፥ ስለ ትክክለኛነት ጥያቄዎች፥ ለእስራኤል ማኅበረሰብ ስለነበሩት የፍጹምነት አሳቦችና በተለይም ቤዛነትን አስመልክቶ ከሕዝቡ ጋር ስለነበረው ግንኙነት ከዚህ ሕግ ምን ያህል ልንማር እንደምንችል መገንዘቡ ነው። ስለሆነም፥ ይህ ሕግ (1) በአዲስ ኪዳን ስለ ቤዛነት ለሚቀርብ ትምህርት መልካም መሠረትን ይጥላል። (2) የብሉይ ኪዳን ባርነት ብዙውን ጊዜ ስለ ባርነት ከምናስበው እንዴት እንደሚለይ ግልጽ አሳብ ይሰጠናል። (3) ስለ እግዚአብሔር ፍቅር በሌላ መንገድ የማናገኘውን አመለካከት ይቀርጽልናል። በሌላ አባባል፥ ይህ የሕግ ምንባብ ምንም እንኳ ከእግዚአብሔር የሚመጣ ትእዛዝ ባይሆንም አሁንም ለእኛ ግሩም የእግዚአብሔር ቃል ነው።

ይህም ሆኖ፥ ስለ ጥንቷ እስራኤል ባርነት ሁሉንም ነገር ከዚህ ሕግ መማር አይቻልም። ለምሳሌ፥ እስራኤላዊ ላልሆኑ ባሮች የሚሰጡ አንዳንድ ደንቦች ለየት ያሉ ናቸው። በፔንታቱክ ስለ ባሮች የሚናገሩ ሕግጋት ሁሉ በአንድ ላይ ቢደረጉ እንኳ ሙሉውን ጉዳይ የሚያዳርሱ አይደሉም። በጥቂት መቶዎች የሚቆጠሩ ሕግጋት እንደ ሞዴሎች ብቻ እንደሚያገለግሉ መታወቅ አለበት። ይህም ማለት ሰዎች እንዴት ሊኖሩ እንደሚገባቸው በምሳሌነት የሚያሳዩ እንጂ፥ እያንዳንዱን የአኗኗር መስክ የሚዘረዝሩ አይደሉም። በሺዎች የሚቆጠሩ ደንቦች ያሉባቸው ዘመናዊ የወንጀለኛ ድንጋጌዎችና የሕዝብ ሕግጋት እንኳ ለማኅበረሰቡ ሙሉ በሙሉ መመሪያ ሊሰጡ እንደማይችሉ ስለምንገነዘብ፥ ብሉይ ኪዳንም ሁሉን አቀፍ ይሆናል ብለን አንጠብቅም። ይሁንና፥ እግዚአብሔር ለአሮጌው ቃል ኪዳን ሕዝቡ ያስፈራቸውን መመዘኛዎች ስለሚያካትት ፈቃዱን ለመፈጸም በምንፈልግበት ጊዜ ለእኛም ከፍተኛ ትምህርት ይሰጠናል።

## የብሉይ ኪዳን ሕግና ሌሎች ጥንታዊ ሕግጋት

እስራኤላውያን በሕግ ለመተዳደር የመጀመሪያዎቹ ሕዝቦች አልነበሩም። እግዚአብሔር በሙሴ (1440 ዓ.ዓ. ወይም ከዚያ በኋላ፥ ከግብጽ ከወጡበት ጊዜ አንጻር) በኩል ለእስራኤላውያን ሕግ ከመስጠቱ በፊት እንኳ አያሌ የሕግ ድንጋጌዎች ነበሩ። እነዚህ ቀደምት ሕግጋት ከብሉይ ኪዳን ሕግ ጋር በሚነጻጸሩበት ጊዜ፥ ብሉይ ኪዳን ከእነዚያ ሁሉ ልቆ ይገኛል። አንድ ሰው የብሉይ ኪዳን ሕግጋትን ሙሉ ለሙሉ ሊያደንቅ የሚችለው ያሻሻላቸውን ሌሎች ጥንታዊ ሕግጋት የተመለከተ እንደሆነ ብቻ ነው። ይህን ስንል ግን ብሉይ ኪዳን እጅግ የላቀ ሥነ ምግባራዊ ወይም ግብረ ገባዊ ትምህርቶችን ያስተላልፋል ማለታችን አይደለም። ይህንን የምንመለከተው ከአዲስ ኪዳኑ የክርስቶስ ትምህርት አንጻር ብቻ ነው። ይህም ሆኖ፥ ብሉይ ኪዳን ከእርሱ በፊት ከነበሩት የከበሩ መመዘኛዎችን አስፍሯል።

ለምሳሌ፥ የሚከተሉትን ሁለት የሕግጋት ምድቦች ተመልከት። የመጀመሪያው በ1800 ዓ.ዓ. አካባቢ የተጻፈ የአካዲያን ሕግ ሲሆን፥ የኤሽኑና ሕግጋት በመባል ይታወቃል።

> «አንድ ነፃ ሰው በሌላ ነፃ ሰው ላይ ቂም ባይኖርበትና ነገር ግን የሌላኛውን ነፃ ሰውዬ ሴት ባሪያ ቢገድል ለባሪያይቱ ጌታ ሁለት ሴት ባሮችን ካሳ መክፈል አለበት። ቂም ሳይኖርበት የበላይ መደብ አባል የሆነውን ሰው ሚስት ወይም ልጅ ቢገድል፥ ይህ ከፍተኛ ወንጀል ነው። ይህንን ያደረገ ሰው ሊገደል ይገባዋል።» ለተጨማሪ

መረጃ የሚከተለውን ተመልከት (Eshnunna, laws 23, 24, author's translation; cf. J. B. Pritchard, ed. Ancient Near Eastern Texts Relating to the Old Testament. 3d ed; Princeton: University Press, 1969, p. 162).

የሚከተለው ከዝነኛው የሀሙራቢ ሕግ የተወሰደ ሲሆን፥ አንድ የባቢሎን ንጉሥ በ1726 ዓ.ዓ. ያስተላለፈውን የመሬት ሕግ ይገልጻል።

«አንድ ነፃ የላይ መደብ አባል የሌላውን ነፃ የበላይ መደብ አባል ሴት ልጅ ቢመታትና ፅንሷ ቢጨናገፍ፥ ለፅንሱ አሥር ሰቅል ብር ሊከፍላት ይገባል። ልጂቱ ከሞተች የእርሱን ልጅ መግደል ያስፈልጋል። የተራውን ሰው ልጅ በጭካኔ መትቶ ፅንሷ እንዲጨናገፍ ቢያደርግ፥ አምስት ሰቅል ብር መክፈል አለበት። ያች ሴት ከሞተች ደግሞ ግማሽ የብር ሚና መክፈል አለበት። ነፃ የበላይ መደብን አባል ሴት ባሪያ ቢመታትና ፅንሷ ቢጨናገፍ፥ አምስት ሰቅል ብር መክፈል አለበት። ያች ሴት ብትሞት ደግሞ ግማሽ የብር ሚና መክፈል አለበት። ነፃ የበላይ መደብ አባል የሆነውን ሰው ሴት ባሪያ ቢመታና ፅንሷ ቢጨናገፍ፥ ሁለት የብር ሰቅል መክፈል አለበት። ያች ሴት ባሪያ ብትሞት ግማሽ የብር ሚና መክፈል አለበት።» (Hammurabi, Laws 209-14, author's translation; cf. J. B. Pritchard, ed. *Ancient Near Eastern Texts Relating to the Old Testament*. 3d ed.; Princeton: Universty Press, 1969, p. 175).

በእነዚህ ሕግጋት መካከል ትኩረትን የሚሹ አያሌ ጉዳዮች ሊኖሩ ቢችሉም፥ እኛ የመረጥነው ግን አንዱን ብቻ ነው። በእነዚህ ሕግጋት ውስጥ የመደብ ልዩነት ጎልቶ ይታያል። ባሪያን ወይም ተራ ሰው መግደል የገንዘብ ቅጣት ሲያስከፍል፥ የበላይ መደብ አባል የሆነን ሰው መግደል ግን ሞትን ያስከትላል። በተጨማሪም ወንድ የበላይ መደብ አባላት ሴትን በመጉዳታቸው እንደማይቀጡ እንመለከታለን። ስለሆነም በሁለተኛው የሕግጋት ቡድን ውስጥ (ሃሙራቢ ሕግጋት፥ 209–14)፥ አንድ የላይ መደብ አባል የሌላውን የላይ መደብ አባል ልጅ ቢገድል እርሱ ላይ የሚደርስ ጉዳት እንደሌለ እንገነዘባለን። ሕጉ የሚያየው የሴት ልጁን መገደል ብቻ ነው። በመጀመሪያዎቹ ሕግጋት ውስጥም እንደዚሁ (ኤሽኑና ሕግጋት፥ 23–24)፥ የባሪያ ሞት የሚካካሰው ሁለት ባሮችን በመስጠት ነው። ገዳዩ ምንም ጉዳት አይደርስበትም።

እንደዚህ ባሉት ሕግጋት ዘንድ ሴቶችና ባሮች እንደ ዕቃ ይቆጠራሉ። በእነዚህ ወገኖች ላይ የሚደርሰው ጉዳት በእነዚህ ሕግጋት ደንቦች የሚታየው በንብረት ላይ እንደ ደረሰ ጉዳት ነው።

በእንዲህ ዓይነት ደንቦች ላይ ብሉይ ኪዳን ያሳየው ሥነ ምግባራዊ ለውጥ እጅግ ከፍተኛ ነው። ብሉይ ኪዳን አንድ ሰው በቦታው ወይም በማኅበራዊ ደረጃው ምክንያት እንዲገደል አይፈቅድም፤ «አትግደል» (ዘጸ. 2፡13)። «ሰውን ደብድቦ የገደለ ሞት ይገባዋል» (ዘጸ. 21፡12)። ለባሮች ስለሚከፈል ካሳም ብሉይ ኪዳን ያመጣው ዕድገት እንዳለ እንመለከታለን። «የወንድ ወይም የሴት አገልጋዩን ጥርስ ቢሰብር፣ ስለ ጥርስ ካሣ አገልጋዩን ነፃ ይልቀቀው» (ዘጸ. 21፡27)። በአጠቃላይ ባሮች በብሉይ ኪዳን ውስጥ የነበራቸው ደረጃ ቀደም ሲል ከነበራቸው የተለየ ነበር። «አንድ ባሪያ ከአሳዳሪው ኮብልሎ ወደ አንተ ቢመጣ፤ ለአሳዳሪው አሳልፈህ አትስጠው። ደስ በሚያሰኘው ቦታና ራሱ በመረጠው ከተማ በመካከልህ ይኑር፤ አንተም አታስጨንቀው» (ዘዳግ. 23፡15–16)። የበላይ መደብ አባል የሆነ ሰው እርሱ ለፈጸመው የሞት ወንጀል ልጁን እንዲያስገድል ከሚያስገድደው የሃሙራቢ ሕግ በተቃራኒ ብሉይ ኪዳን የሚከተለውን ያዛል። «አባቶች ስለ ልጆቻቸው፣ ልጆችም ስለ አባቶቻቸው አይገደሉ። እያንዳንዱ በራሱ ኃጢአት ይገደል» (ዘዳግ. 24፡16)።

## የብሉይ ኪዳን ሕግ ለእስራኤል ያበረከተው ጥቅም

የዘላለምን ሕይወትና እውነተኛውን ጽድቅ በማጎናጸፉ ረገድ ሕጉ ፍጹም ደካማ ነበር። የተሰጠውም ለዚሁ ዓላማ አልነበረም። አንድ ሰው ሕግን ሙሉ በሙሉ ሊጠብቅ ስለማይችልና በሕይወት ዘመን ድንገት አንዱን መተላለፉ ስለማይቀር፥ በሕግ በኩል ደኅንነትንና በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት የሚፈልግ ሰው ተስፋ አልነበረውም (ሮሜ 2፡17–27፤ 3፡20)። አንዱን ሕግ መተላለፉ ራሱ «ሕግ ተላላፊ» ያሰኛል (ያዕ. 2፡10)።

ነገር ግን ሕግ የተሰጠበትን ዓላማ በግልጽ ከተረዳን ለእስራኤላውያን የእግዚአብሔር ምሕረትና ጸጋ ምሳሌ ሆኖ ከፍተኛ ጥቅም እንደሚያስገኝ እንገነዘባለን። እዚህ በናሙናነት ያቀረብናቸው ዓይነት ሕግጋት ሲያጋጥሙህ በዚህ ግንዛቤ አንብባቸው።

### *የምግብ ሕግጋት*

ለምሳሌ፥ «ዐሣማ ሰኮናው የተሰነጠቀ ቢሆንም ስለማያመሰኳ በእናንተ ዘንድ ርኩስ ይሁን» (ዘሌ. 11፡7)።

እንደዚህ ዓይነት የምግብ ሕግጋት በእስራኤላውያን የምግብ ፍላጎት ላይ ዘፈቀዳዊ ማዕቀብ ለመጣል የታሰቡ አይደሉም። ይልቁንም፥

ከፍተኛ የጥበቃ ዓላማ ነበራቸው። የተከለከሉት አብዛኞቹ የምግብ ዓይነቶች (1) በሲና ምድረ በዳና በከነዓን ምድር በሽታ ሊያመጡ የሚችሉ ወይም (2) በሲና በረሃ ወይም በከነዓን ምድር የእርሻ ሁኔታ ለማግኘት የሚያስቸግሩ ወይም (3) እስራኤላውያን ሊኮርጇቸው የማይገባቸው ግን ሌሎች ሕዝቦች ለሃይማኖታዊ መሥዋዕትነት የሚመርጧቸው ነበሩ። በአሁኑ ሰዓት የሕክምና ምርምሮች የምግብ አለርጂዎች ከአንዱ ወደ ሌላው የጎሳ ክፍል እንደሚለያዩ ስላብራሩ፥ ለእስራኤላውያን የተሰጡት የምግብ ሕግጋት ከተወሰኑ አለርጂዎች እንደታደጓቸው መረዳት ይቻላል። በረሃው የእስራኤላውያንን አተነፋፈስ የሚያዛቡ ብዙ የአበባ ብናኞች ባይኖሩትም፥ ነርቫቸውን የሚጎዱ አንዳንድ እንስሳት ነበሩት። የሚገርመው የእስራኤላውያን ዋንኛ የሥጋ ምንጭ የሆነው በግ ከሌሎች ትላልቅ እንስሳት ሁሉ ያነሰ አለርጂ እንደሚያስከትል የምግብ አለርጂ አጥኚዎች መግለጻቸው ነው።

*የደም ማፍሰስ ሕግጋት*

ለምሳሌ፡ «ወይፈኑን በመገናኛው ድንኳን ፊት ለፊት በማምጣት አሮንና ወንዶች ልጆቹ በራሱ ላይ እጆቻቸውን ይጫኑበት። በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ላይ በእግዚአብሔር--- ፊት እረደው። ከወይፈኑም ደም ወስደህ በመሠዊያው ቀንዶች ላይ በጣቶችህ አድርግበት፤ የቀረውንም ከመሠዊያው ሥር አፍስሰው» (ዘጸ. 29፡10-12)።

እንዲህ ዓይነት ሕግጋት ለእስራኤል ጠቃሚ መመዘኛዎችን ይሰጣሉ። ኃጢአት መቀጣት አለበት። እግዚአብሔር ለሕዝቡ ራሱን የገለጠው በእርሱ ላይ ኃጢአትን የሚሠራ ሰው በሕይወት ሊኖር እንደማይገባ በሚያስረዳ ሕግ አማካኝነት ነው። ነገር ግን ኃጢአተኛው ከሞት ሊያመልጥ የሚችልባቸውን ሂደቶችም አቅርቧል። የኃጢአተኛው ምትክ የሆነው እንስሳ ደም ከፈሰሰ በኋላ ኃጢአተኛው በሕይወት ሊኖር ይችል ነበር። ስለሆነም እግዚአብሔር ከሕዝቡ መካከል ኃጢአት የሠራው ሰው በሕይወት ይኖር ዘንድ የእንስሳን መሥዋዕትነት ለመቀበል ወሰነ። የሕጉ የመሥዋዕት ሥርዓት ይህንኑ ሂደት ወደ እስራኤላውያን ሕይወት አስገባው። ይህም የሕዝቡ ደኅንነት ወሳኝ ሥርዓት ነበር። «ደም ሳይፈስ ኃጢአት አይሰረየምና» (ዕብ. 9፡22)። በተጨማሪም፥ የምትክነትን የሚያዙ ሕግጋት ለክርስቶስ የቤዛነት ስርየት ምሳሌዎች ሆኑ። በዕብራውያን 9፡22 የተገለጸው መርሕ ሙሉ በሙሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው። የክርስቶስ ሞት ሕግ የሚጠይቀውን በማሟላት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘታችን መሠረት ይሆናል። የብሉይ ኪዳን ሕግ በታሪክ ታላቅ

ምዕራፍ ውስጥ ታላቅ ስፍራ ለተሰጠው ክስተት ሥረ መሠረት ሆኖ ያገለግላል።

### ያልተለመዱ እገዳዎች

ለምሳሌ፣ «የፍየልን ግልገል በእናቱ ወተት አትቀቅል» (ዘዳግ. 14፡21)።

«ምናለበት?» ብለህ ትጠይቅ ይሆናል። ይኼና፥ «የተለያዩ እንስሳትን አታዳቅል፤ በእርሻህ ላይ ሁለት ዓይነት ዘር አትዝራ፤ ከሁለት ዓይነት ነገር የተሠራ ልብስ አትልበስ» (ዘሌ. 19፡19) የሚሉ ሌሎች የብሉይ ኪዳን ሕግጋት የተሰጡት ለምንድን ነው?

እነዚህና ሌሎችም እገዳዎች የተደረጉበት ምክንያት፤ እስራኤላውያን ከነዓናውያን የሚያመልኳቸውን የልምላሜ ጣዖታት እንዳይከተሉ ለማድረግ ነው። ከነዓናውያን የኃዘኔታ ምትሐት፥ ማለትም ተምሳሌታዊ ተግባራት፥ አማልክትንና ተፈጥሮን ይለውጣሉ ብለው ያምኑ ነበር። የፍየልን ግልገል በእናቱ ወተት መቀቀል የመንጋውን ቀጣይነት ያረጋግጣል ብለው ያምኑ ነበር። እንስሳትን፥ የተለያዩ የእህል ዓይነቶችንና ማቴሪያሎችን ማዳቀል በምትሐታዊ መንገድ ትርፋማነትን ያስከትላል ብለው ያምኑ ነበር። እንደዚሁም እግዚአብሔር እንዲህ ዓይነት ምትሐታዊ መንገዶችን ቢከተሉ ሕዝቡን አይባርካቸውም ነበር። የእነዚህን ሕግጋት ዓላማ መረዳቱ (ማለትም ደኅንነት ወደሌለበት የከነዓናውያን ሃይማኖት እንዳይሄዱ መከላከሉ) እጅግ ጠቃሚና ወሳኝ መሆኑን ለመገንዘብ ያስችላል።

### ለሚጠብቋቸው በረከትን የሚሰጡ ሕግጋት

ለምሳሌ፡ «በየሦስት ዓመቱ መጨረሻ የዚያን ዓመት ሰብል አሥራት በሙሉ አውጥተህ በከተሞችህ ውስጥ አከማች። ይህን የምታደርገው የራሱ ድርሻ ወይም ርስት የሌለው ሌዋዊና መጻተኛ፤ በከተሞችህ የሚኖሩ አባት የሌላቸውና መበለቶች መጥተው እንዲበሉና እንዲጠግቡ፤ አንተንም አምላክህ እግዚአብሔር--- በእጆችህ ሥራ ሁሉ እንዲባርክህ ነው» (ዘዳግ. 14፡28-29)።

በመሠረቱ የእስራኤል ሕግጋት ሁሉ የተሰጡት ለእግዚአብሔር ሕዝብ የበረከት መንገዶች እንዲሆኑ ነበር (ዘሌ. 26፡3-13)። ነገር ግን እነርሱን መጠበቅ በረከትን እንደሚያስገኝ የሚናገሩ ሕግጋት ብዙዎች አይደሉም። በዘዳግም 14፡28-29 የሚገኘው የሦስተኛ ዓመት የአሥራት ሕግ የሚታዘዙት በረከትን እንደሚቀበሉ ያስረዳል። ሕዝቡ በመካከላቸው ላሉት ድሆች ማለትም (ዘሌዋውያን፥ እጓለማውታዎችና መበለቶች) ካላሰበላቸው፥ እግዚአብሔር በረከትን አይሰጣቸውም። አሥራት የእርሱ ድርሻ ሲሆን፥ ከሥራ ላይ ስለሚውልበት መንገድ

ውክልና ሰጥቷል። ይህን ትእዛዝ መተላለፍ ማለት የእግዚአብሔርን ገንዘብ እንደ መስረቅ ይቆጠር ነበር። ይህ ሕግ ለድሆች የሚጠቅም ሲሆን (የብሉይ ኪዳን የደኅንነት ሥርዓት በጥሩ ሁኔታ የተዘረጋ ነው)፥ ችግረኞችን ለሚረዱትም በረከትን ያስገኝል። እንዲህ ዓይነቱ ሕግ የሚከለክልም የሚቀጣም አይደለም። ይልቁንም እንዲህ ዓይነቱ ሕግ ለመልካም ተግባር የሚያነሣሣ ስለሆነ፥ ለጥንታውያን እስራኤላውያንም ሆነ ለእኛ ትምህርት ሰጭነቱ ከፍተኛ ነው።

## እንደ ማጠቃለያ፣ አንዳንድ የአድርግ አታድርግ መርሆዎች።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ካነሣናቸው አንዳንድ ነጥቦች በተጨማሪ፥ የብሉይ ኪዳንን ፔንታቱካል ሕግ በምታነብበት ጊዜ ይረዱሃል ብለን የምናስባቸውን አንዳንድ ሥነ አፈታታዊ መርሆዎች እንደሚከተለው በአጭሩ እናቀርባለን። እነዚህን መርሆዎች መጠበቁ የተሳሳተ የብሉይ ኪዳን ተዛምዶ በማስወገድ፥ የሕግን የማስተማርና እምነት–ገንቢ ባሕርያት እንድትከተል ይረዳሃል።

1. የብሉይ ኪዳንን ሕግ ሙሉ በሙሉ በእስትንፋስ–እግዚአብሔር በልጽጎ እንደ መጣልህ ቃል አስበው። የብሉይ ኪዳን ሕግን ለአንተ እንደ ተላከ ቀጥተኛ የእግዚአብሔር ትእዛዝ አትውሰደው።
2. የብሉይ ኪዳንን ሕግ የአሮጌው ኪዳን መሠረትና ከዚህም የተነሣ የእስራኤላውያን ታሪክ መሠረት አድርገህ ተመልከት። በግልጽ እስካልታደሰ ድረስ የብሉይ ኪዳንን ሕግ ለክርስቲያኖች እንደሚሠራ አድርገህ አትመልከት።
3. በብሉይ ኪዳን ሕግጋት ውስጥ የተገለጹትን የእግዚአብሔርን ፍትሕ፥ ፍቅርና ታላላቅ መመዘኛዎች በትኩረት አስተውላቸው። የእግዚአብሔር ምሕረት ከመመዘኛዎቹ ትክክለኛነት እኩል መሆኑን አትዘንጋ።
4. የብሉይ ኪዳንን ሕግጋት እንደ ሙሉ ሕግጋት አድርገህ አትመልከት። በሙያዊ መልኩ (ቴክኒካላዊ) ሙሉ አይደለም። የብሉይ ኪዳን ሕግጋትን የተፈለጉት ባሕርያት ምሳሌዎች የቀረቡበት ሞዴል አድርገህ ተመልከት።
5. የብሉይ ኪዳንን ሕግጋት በነቢያት ወይም በአዲስ ኪዳን በተደጋጋሚ እንዲጠቀስ አትጠብቅ። የሕጉ መሠረታዊ ባሕርይ (አሠርቱ ትእዛዛትና ሁለቱ ዋነኛ ሕግጋት) በነቢያት እንደ ተደገሙና በአዲስ ኪዳን እንደ ታደሱ አስታውስ።
6. የብሉይ ኪዳን ሕግጋት የእስራኤል ሕዝብ በሚታዘዙዋቸው ጊዜ በረከትን የሚያመጡ ለእስራኤል የተሰጡ መልካም ስጦታዎች እንደሆኑ አስብ። የብሉይ ኪዳንን ሕግጋት የሰዎችን ነጻነት እንደሚገድቡ ዘፈቀዳዊ ደንብ አድርገህ አታስብ።